

«ልጄን ትፈጥር ብዬ ተውኳት»

- እናት ጥሩ ማዕድ አስፋው

ገጽ 16

የሸንኮራ አገዳው ንግድ ጣፋጩ ፍሬዎች

ገጽ 13


# አዲስ ዘመን

ኢፕድ

82ኛ ዓመት ቁጥር 084 ኅዳር 24 ቀን 2015 ዓ.ም ዋጋ 10:00

ቅዳሜ

ብዕራችን ለኢትዮጵያ ህዳሴ ይተጋል!



ደርባ ሚድሮክ ሲሚንቶ ኃ/የተ/የግል ማህበር



በልዩ የደርባ ሲሚንቶ መስመር 8688 ወይም

- 0111 26 26 27 - 0922 11 53 24/26
- 0111 26 26 28 - 0922 72 74 48/49
- 0111 26 26 29 - 0922 72 38 70
- 0111 26 26 30 - 0922 72 38 72

ፋክስ:- 0111 26 23 45 እና 0111 26 23 18

ይዘዙን

ደረጃቸውን ጠብቀን የምናመርታቸውን ጥራት ያላቸው የሲሚንቶ ምርቶች ቤትዎ ወይም ፕሮጀክትዎ ደጃፍ ላይ ያለውጣ ውረድ በደርባ ትራንስፖርት ኃ.የተ.የግ.ማ አማካይነት እናቀርባለን።

ነገን ዛሬ እንሥራ




ፎቶ:- ፀሐይ ንጉሤ

አቶ ተመስገን ጥሩነህ እና ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ

# ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ጨምሮ በሙስና የተጠረጠሩ አካላት በቁጥጥር ሥር ዋሉ

## - ኮሚቴው በአንድ ሳምንት ውስጥ ከ250 በላይ ጥቆማዎችን ተቀብሏል

**ውብሸት ሰንደቁ**

አዲስ አበባ:- በቅርቡ የተቋቋመው ብሔራዊ የፀረ ሙስና ኮሚቴ ከፍተኛ የመንግሥት ባለሥልጣናትን ጨምሮ በሙስና የተጠረጠሩ አካላት በቁጥጥር ሥር መዋላቸውን አስታወቀ። እስካሁን ድረስም ከ250 በላይ ጥቆማዎችን ተቀብሎ እየመረመረ መሆኑንም አስታውቋል።

የኮሚቴው ሰብሳቢ አቶ ተመስገን ጥሩነህ እና የኮሚቴው አባል ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ ትናንት በጋራ በሰጡት መግለጫ እንደገለጹት፤ ብሔራዊ የፀረ

ከፍተኛ የመንግሥት ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል

# በጉባኤው የተነሱ ነጥቦች በበይነ መረብ አስተዳደር የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር የሚያስችሉ ናቸው

- ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር ደመቀ መኮንን

**ሞገስ ተስፋ**

አዲስ አበባ:- በ17ኛው በይነመረብ አስተዳደር ጉባኤ የተነሱ ነጥቦች በቀጣይ የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር የሚያስችሉ ናቸው ሲሉ የኢፌዴሪ ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር እና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትሩ አቶ ደመቀ መኮንን ገለጹ። በበይነመረብ አጠቃቀም ዙሪያ ያሉ ችግሮችን ለመቅረፍ ዓለም አቀፍ የበይነመረብ አስተዳደር ሊኖር እንደሚገባም በጉባኤው ተመላክቷል።

አቶ ደመቀ መኮንን በ17ኛው ዓለም አቀፍ የበይነመረብ ጉባኤ ማጠቃለያ ላይ ባደረጉት ንግግር፤ ኢትዮጵያ ለሁለት ዓመት ያህል በሰሜኑ የአገሪቱ ክፍል የነበረውን ግጭት በውይይት በፈታችበት ማግስት እና ያልተገደበ የሰብአዊ አቅርቦትና የተጎዱ መሰረተ ልማቶችን በምትጠግንበት ወቅት ስኬታማ ዓለም አቀፍ ጉባኤ አስተናግዳለች።

አቶ ደመቀ፤ "የጉባኤው ተሳታፊዎች በአዲስ አበባ በነበራቸው ቆይታ በጥሩ ሁኔታ እንደቆዩ እገምታለሁ። ለቀጣይ የበይነመረብ አስተዳደር ግብአት የሚሆን ሃሳብ የተለዋወጡበት ነው። በቀጣይም ዓለም አቀፍ የበይነመረብ አስተዳደር ሊኖር እንደሚገባ የሃሳብ ልውውጥ የተደረገበት ነው" ብለዋል።

ኢትዮጵያ የዲጂታል ኢኮኖሚን በመገንባት ላይ እንደምትገኝ የገለጹት ሚኒስትሩ፤ ለእድገትና ለውጥ በይነመረብ አስፈላጊ ነው፣ ለዚህም ኢትዮጵያ በቁርጠኝነት እየሰራች ነው ብለዋል።

ጉባኤው የጋራ የሆነ የቀጣይ ግብን ለማሳካት ወሳኝ ነው ያሉት አቶ ደመቀ፤ የተነሱት ሃሳቦች ለሁሉም አገራት ጠቃሚ ናቸው ብለዋል። የዲጂታል ሚዲያና በይነመረብ ለብልጽግና አስፈላጊ ናቸው። በኢትዮጵያ በበይነመረብ አስተዳደር የተነሱ ነጥቦች የጋራ ግንዛቤ እንዲኖር የሚያስችሉ ናቸው ሲሉም ጠቅሰዋል። አቶ ደመቀ መኮንን ስኬታማ

በጉባኤው የተነሱ ... ወደ ገጽ 4 ዞሯል



ፎቶ:- ፀሐይ ንጉሤ






# ስምምነቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ተቀባይነትና ተደማጭነት ይበልጥ ያሳድጋል

- ኢጋድን ለማጠናከር አባል አገራት ድጋፍ እንዲያደርጉም ኢትዮጵያ ጠይቃለች

ገጽ 4



ፎቶ:- ሐዱሽ አብርሃ

«የኢትዮጵያ ህልውና የሚረጋገጠው ሰላም በማስከበር ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚዋን ከሌቦች ስንታደግ ጭምር ነው»


- መጋቢ ብሉይ አብርሃም ሃይማኖት የኢሕአፓ ተቀዳሚ ፕሬዚዳንት

ገጽ 4









## «የሰላም ስምምነቱ ፈጥነን ወደ መልሶ ግንባታና ማቋቋም እንድንገባ አስችሎናል»

- የአማራ ክልል ርዕሰ መስተዳድር ይልቃል ከፋለ (ዶክተር)

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- በፌደራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት ፈጥነን ወደ መልሶ ግንባታና ማቋቋም ስራ እንድንገባ አስችሎናል ሲሉ የአማራ ክልል ርእሰ መስተዳድር ዶክተር ይልቃል ከፋለ አስታወቁ።

የክልሉ መልሶ ማቋቋም ግንባታና ገቢ ማሰባሰቢያ ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ትናንት በራያ ቆቦ ወረዳ ወርቄ ቀበሌ ሲካሄድ እንደገለጹት፤ በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት ፈጥነው ወደ መልሶ ግንባታና ማቋቋም ስራ እንዲገቡ ያስቻላቸው ሲሆን ክልሉ በጦርነት የተጎዱ አካባቢዎችን መልሶ ለመገንባት ለዚህ ዓመት ብቻ አንድ ቢሊዮን ብር በጀት መድቧል። በመደበው ገንዘብ በስምንት ዞኖች ውስጥ የመልሶ ግንባታ ስራ ይጀመራል።

"በፌዴራል መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተደረሰው የሰላም ስምምነት ፈጥነን ወደ መልሶ ግንባታና ማቋቋም ስራዎች ፊታችንን እንድናዞር ያደረገን በመሆኑ ለተግባራዊነቱ ክልሉ በሙሉ ልብ ይሰራል" ሲሉ ርእሰ መስተዳድሩ አስታውቀዋል።

በዞኖቹ የፈረሱ የግለሰብ ቤቶችና የአገልግሎት መስጫ ተቋማት የመልሶ ግንባታ እንደሚካሄድ ጠቁመው ፤ አገልግሎት መስጫዎች ፈጥነው ወደ ስራ እንዲገቡ እንደሚደረግ አመልክተዋል። በክልሉ ለሚካሄደው የመልሶ ማቋቋምና ግንባታ መርሃ ግብር የሀገሪቱ ሕዝቦች፣ ረጅ ድርጅቶችና ባለሀብቶች አስፈላጊውን ድጋፍ እንዲያደርጉም ጥሪ አቅርበዋል።

በጦርነቱ የወደሙ የማህበራዊ አገልግሎት ሰጪና ሌሎች ተቋማትን መልሶ ለመገንባትና ለማቋቋም በክልል ደረጃ ፅህፈት ቤት ተቋቁሞ ድርጅቶችን፣ ባለሀብቶችንና ማህበረሰቡን እያስተባበረ እንደሚገኝ የገለጹት ደግሞ በምክትል ርእሰ መስተዳድር ማእረግ የክልሉ የማህበራዊ ክላስተር አስተባባሪ አቶ ስዩም መኮንን ናቸው።

ለዘንድሮ ዓመት መልሶ ግንባታ ስራ ብቻ 12 ቢሊዮን ብር ለማሰባሰብ ልዩ ትኩረት ተሰጥቶ እየተሰራ መሆኑን ተናግረዋል።

በሚሰበሰበው ገንዘብ ጉዳት በደረሰባቸው አካባቢዎች የጤና ተቋማት፣ ትምህርት ቤቶች፣ የንፁህ መጠጥ ውሃ ተቋማት፣ የመስኖ ፕሮጀክቶችና የሌሎች አገልግሎት መስጫዎች የመልሶ ግንባታ ስራ እንደሚከናወን አመልክተዋል።

በሰሜን ወሎ ዞን ራያ ቆቦ ወረዳ ወርቄ ቀበሌ የሙሉ 1ኛ ደረጃ ትምህርት ቤት፣ የጤና ጣቢያ፣ የእንስሳት ክሊኒክና የመልሶ ግንባታ ማስጀመሪያ መርሃ ግብር ትናንት ተከናውኗል።

በማስጀመሪያ መርሃ ግብሩ የክልልና የዞኑ የስራ ሃላፊዎች እንዲሁም ሌሎች ባለድርሻ አካላትና የአካባቢው ነዋሪዎች ተሳትፈዋል።



ዶክተር ብርሃነመስቀል ጠና እና ዶክተር ደረጄ እንግዳ

# ምሁራን በአገራዊ ጉዳይ የሚመክሩበት ጉባኤ ሊካሄድ ነው

ጌትነት ተስፋማርያም

አዲስ አበባ፡- በከፍተኛ የትምህርትና በምርምር ተቋማት የሚገኙ ምሁራን በአገራዊ ጉዳይ የሚመክሩበት ጉባኤ ህዳር 26 ቀን 2015 ዓ.ም እንደሚካሄድ የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ አስታወቁ።

መድረኩን አስመልክቶ የኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ብርሐነመስቀል ጠና እና የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ደረጄ እንግዳ በጋራ በሰጡት መግለጫ ፤ ጉባኤው "ለኢትዮጵያ ልዕልና የምሁራን ሚና" በሚል መሪ ሃሳብ በአዲስ አበባ እንደሚካሄድ ተናግረዋል።

ዶክተር ብርሐነመስቀል ጠና እንደገለጹት፤ በተለያዩ መንግሥታት የምሁራን የአገራዊ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ላይ ተሳትፎ ዝቅተኛ ነበር። አገራዊ ክፍተቱን በመረዳትና የምሁራንን ተሳትፎ ለማሳደግ የሚረዳ ጉባኤ ተዘጋጅቷል።

በመድረኩ ከተለያዩ የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ ከምርምር ማዕከላትና ከሴክተር ተቋማት የተውጣጡ 300 ምሁራን እንደሚሳተፉ ይጠበቃል ሲሉ ዶክተር ብርሐነመስቀል አስታውቀዋል።

ምሁራንም እርስ በእርስ ከመከፋፈልና ከመሻኮት ወጥተው ለአገራቸው ሰላምና ሉዓላዊነት ገንቢ ሚና የሚጫወቱበት ዕድልን መፍጠር የጉባኤው ዓላማ መሆኑን ተናግረዋል።

ዶክተር ብርሐነመስቀል እንዳስታወቁት፤ ምሁራን በነጻነት የሚመክሩበትና የሃሳብ ልዕልና የሚሰፍንበት መድረክ እንዲሆን ለሁለት ወራት ዝግጅት ተደርጓል። ለውይይት መነሻ የሚሆኑ ጥናታዊ ጽሁፎችም ይቀርባሉ።

የአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ ፕሬዚዳንት ዶክተር ደረጄ እንግዳ በበኩላቸው፤ መድረኩ ምሁራን በአገራዊ ጉዳዮች ላይ ያላቸውን ሃሳብ የሚያንጸባርቁበትና ለችግሮቻችንም መፍትሄ ይሆናሉ የሚሏቸውን ሃሳቦች በምክረሃሳብነት የሚያቀርቡበት ይሆናል ብለዋል።

በጉባኤው ላይ የሚሳተፉ ምሁራን የሚነሱትን ጉዳዮች ይዘው የሚሄዱ ብቻ ሳይሆን ሃሳቦችን በማዳበር ለተሻለ ውጤት የሚጥሩ መሆን አለባቸው ሲሉ ገልጸዋል።

በኮተቤ ትምህርት ዩኒቨርሲቲ እና በአዲስ አበባ ሳይንስና ቴክኖሎጂ ዩኒቨርሲቲ አዘጋጅነት የሚካሄደው የምሁራን መድረክ፤ በቀጣይነት በሌሎች የከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ዘንድ እንዲሰፋ ይደረጋል። ለዚህም ዩኒቨርሲቲዎች ቀጣይ ሃላፊነታቸውን ይወጣሉ ተብሎ ይጠበቃል ብለዋል።

በተለያዩ የአገሪቷ ክፍል የሚገኙ ምሁራን በኢትዮጵያ ሁለንተናዊ ፖለቲካዊና ኢኮኖሚያዊ ተሳትፎ ውስጥ ያላቸውን ሚና በማሳደግ አበርክቷቸውን ከፍ ማድረግ ይገባቸዋል ሲሉ ተናግረዋል።

ለዚህም የሚረዳ የምክክርና የሃሳብ ማፍለቂያ መድረክ ተዘጋጅቷል በጉባኤው የሚሳተፉ ምሁራንም ንቁ ተሳትፎ እንዲያደርጉ ይጠበቃል ሲሉ ዶክተር ደረጄ ጥሪ አቅርበዋል።

ከተለያዩ ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት፣ የምርምር ማዕከላትና ከሴክተር መስሪያ ቤቶች ተለይተው በጉባኤው የሚሳተፉ ምሁራን በመድረኩ ሁለት አጀንዳዎች ላይ የሙሉቀን ውይይት እንደሚያደርጉ አዘጋጅ ዩኒቨርሲቲዎቹ አስታውቀዋል።

# በትግራይ ክልል በርካታ አካባቢዎች በቅርቡ አገልግሎት እንደሚያገኙ ኢትዮ ቴሌኮም አስታወቀ

በጋዜጣው ሪፖርተር


አዲስ አበባ፡- የሽረ ኮር ሳይት ጥገና ሲጠናቀቅ በርካታ የትግራይ ክልል አካባቢዎች አገልግሎት እንደሚያገኙ የኢትዮ - ቴሌኮ አስታወቀ።

የኢትዮ - ቴሌኮም ዋና ሥራ አስፈፃሚ ፍሬህይወት ታምሩ እንደተናገሩት፤ የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ መግባት እስከተቻለባቸው አካባቢዎች ድረስ የጥገና ሰራተኞቻቸውን መላካቸውን ጠቁመው፤ በዚህም የሽረ ኮር ሳይት ጥገና ሲጠናቀቅ በርካታ የትግራይ ክልል አካባቢዎች የቴሌኮም አገልግሎት ያገኛሉ ብለዋል።

በሰሜኑ የሀገሪቱ ክፍል በነበረው ጦርነት በቴሌኮም መሰረተ ልማቶች ላይ ምን ያህል ውድመት እንደደረሰ ለማወቅ ዳሰሳ ያስፈልጋል ያሉት ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ፤ ቀደም ብሎ ጥገና ማድረግ የሚያስችል ዝግጅት ሲደረግ በመቆየቱ በአጭር ጊዜ ውስጥ በሙሉ አቅም ባይሆንም አገልግሎት ማስጀመር መቻሉን ተናግረዋል።

እንደ ዋና ሥራ አስፈፃሚዋ ገለፃ፤ ማይፀብሪ፣ አላማጣ፣ ኮረም እና ዓዲ አርቃይ ከተሞች በሞባይል አማካኝነት በድምፅ የሚገናኙበት እድል ተፈጥሯል።

በሌላ በኩል ደግሞ ሽረ የሚገኘውን ኮር ሳይት አገልግሎት እንዲሰጥ ለማድረግ የሚያስችል ቅኝት ተደርጓል፤ ሳይቱ ለሁለት ዓመታት አገልግሎት ሳይሰጥ በመቆየቱ የጎደሉ እቃዎችን ማሟላትና ሌሎች ስራዎች ሲሰሩ መቆየታቸውን ገልፀዋል።




እስካሁን በርብርብ በተከናወነው ስራም 266 ኪሎ ሜትር የፋይበር ጥገና ማከናወን መቻሉን ጠቁመው፤ ጥገናውን ለማጠናቀቅ 6 ኪሎ ሜትር ይቀረናል ብለዋል። የጥገና ስራው ሲጠናቀቅ ከአስቸኳይ የቴሌኮም አገልግሎት በዘለለ ሰፊው ማህበረሰብ አገልግሎት እንዲያገኝ ያስችላል ብለዋል።

ከሽረ ቀጥሎ አክሱም እና አድዋም አካባቢዎች አገልግሎት እንዲያገኙ የማስተላለፊያ መስመር ፍተሻ ጀምረናል። በቅርቡም በርካታ ከተሞች የቴሌኮም አገልግሎት ያገኛሉ፤ ለዚህም ኢትዮ ቴሌኮም ከባለድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት እየተሰራ ነው ሲሉም ዋና ስራ አስፈጻሚዋ ተናግረዋል።


ወይዘሪት ሓዳስ ኪዱ


አቶ ጎይቶኦም በርሀ


ወይዘሮ አበባ በርሀ

# የሰላም ስምምነቱን በፍጥነት ተግባራዊ በማድረግ የትግራይን ሕዝብ መታደግ ይገባል ሲሉ የትግራይ ተወላጆች ገለጹ

**መሰረት ገ/ዮሃንስ**

አዲስ አበባ፡- በደቡብ አፍሪካ የተካሄደውን የሰላም ስምምነት ወደ ተግባር በመቀየር መላውን የትግራይ ሕዝብ ከችግር መታደግ እንደሚገባ በተለያዩ የስራ ሃላፊነት ላይ የሚሰሩ የትግራይ ተወላጆች ተናገሩ።

በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የከንቲባዋ አማካሪ ጥናትና ምርምር አማካሪ ወይዘሪት ሓዳስ ኪዱ እንዳሉት፣ በፌዴራል መንግሥትና ሕወሓት መካከል የተደረገው የሰላም ስምምነት በፍጥነት ተግባራዊ መሆን ይገባዋል።

በአንዲት ሀገር ሰላም ከሌለ ኢኮኖሚያዊ፣ ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ጫና በመፍጠር እድገትን ወደ ኋላ የሚጎትት ነው ያሉት ወይዘሪት ሓዳስ፤ ይህ እንዳይሆን በተለይ የትግራይ ሕዝብ ይህን ስምምነት ተፈፃሚ እንዲሆን ያሳየው ተነሳሽነት የሚደነቅ ነው ብለዋል።

ለትግራይ ሕዝብ ትራክተር በማቅረብ ኢኮኖሚውን የሚያሰፋበት እድል መፍጠር እንጂ ብረት ተሸክሞ እንዲኖር ማድረግ ተገቢ አይደለም ያሉት ወይዘሪት ሓዳስ፤ ባለፈው ሁለት ዓመታት አምራች ሃይል አስፈላጊ ላልሆነ ጦርነት ዋጋ ከፍሏል፤ ይህ እንዳይመለስ የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊ ሊሆን ይገባል ሲሉ ገልጸዋል።

የትግራይ ብልጽግና የፖለቲካ ዘርፍ ሃላፊ አቶ ጎይቶኦም በርሀ በበኩላቸው ፣ ይህ የሰላም ሰምምነት ወደ መሬት ወርዶ ተግባራዊ እንዲሆን ሕዝብ እየጠበቀ ነው።

ከዚህ በፊት ዓለም ላይ እያየነው የመጣነው የሰላም ንግግር የነበረና የተለመደ ነው ያሉት አቶ ጎይቶኦም፤ ከግጭት በኋላ ለሰላም ፊርማቸውን የሚያኖሩበት አጋጣሚ ብዙ ነው፤ ነገር ግን ታች ወርዶ ካልተጠቀመበት ዳግም ወደ ጦርነት የሚገባበት የዓለም ታሪክ አይተናል። ይህ እንዳይሆን የሰላም ስምምነቱ ተግባራዊ ማድረግ የግድ ነው ብለዋል።

የትግራይ ሕዝብ የሰላም ስምምነቱ በፍጥነት ተግባራዊ እንዲሆን ፍላጎት እንዳለው በተለያዩ ሚዲያዎች እየገለፀ ነው ያሉት አቶ ጎይቶኦም ፣ ቅድምያ መሰጠት ያለበት ደግሞ የሕዝብ ደህንነት እና ፍላጎት ነው፤ ስለሆነም የሕዝብ ድምጽ መሰማት አለበት ብለዋል።

የትግራይ ብልጽግና የሴቶች ሊግ ሃላፊ ወይዘሮ አበባ በርሀ ፣ ይህ የተገኘው የሰላም እድል በችግር ውስጥ ያለውን የትግራይ ሕዝብ መድሃኒት ፣ ምግብ ፣ መሰረታዊ ግልጋሎት የሚያገኝበት እንዲሁም ከቤተሰቡ ጋር የሚገናኝበት ትልቅ ዕድል ነው፤ ስለዚህ ተግባራዊነቱ ግድ ነው ብለዋል።

በውጭ የሚኖሩ የትግራይ ተወላጆች ይህ የተገኘውን የሰላም ዕድል በመጠቀም የትግራይን ሕዝብ ኑሮ ለመቀየር ንቁ ተሳትፎ ማድረግ አለባቸው ያሉት ወይዘሮ አበባ፣ ይህንን ትውልድ የመቀየር ሃላፊነት ያለብን እኛ ነን ብለዋል።

የትግራይ ሕዝብም ሊካስ የሚችለው በዚህ ሁኔታ ነው ያሉት ወይዘሮ አበባ፤ በመተባበርና አንድነት በመፍጠር ወደ ተሻለ ደረጃ ለመድረስ እውነታውን ተቀብለን ሕዝባችንን ይዘን ወደፊት መራመድ አለብን ሲሉም ተናግረዋል።

# የአገር ውስጥ ኩባንያዎችን በዓለም አቀፍ ገበያዎች ተወዳዳሪ ለማድረግ እየተሰራ ነው

## - ለ540 ሰዎች የስራ እድል የሚፈጥሩ ሶስት ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርክ ገብተዋል

**አዲሱ ገረመው**



አዲስ አበባ፡- የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች እንደ አንዱ ሆኖ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ የአገር ውስጥ ኩባንያዎች የኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ዓለም አቀፍ ተወዳዳሪ እንዲሆኑ እያበረታታ እንደሆነ አስታወቀ። ኮርፖሬሽኑ ከ448 ሚሊዮን ብር በላይ ኢንቨስትመንት ካስመዘገቡና ከ540 በላይ ቋሚ የስራ እድል ከሚፈጥሩ ሶስት ኩባንያዎች ጋር ተፈራርሟል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ዋና ስራ አስፈጻሚ አቶ አክሊሉ ታደሰ ስምምነቱን በተፈራረሙበት ወቅት እንደገለጹት፤ የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን ከመንግሥት የልማት ድርጅቶች እንደ አንዱ ሆኖ ከተቋቋመበት ጊዜ ጀምሮ በመላ ሀገሪቱ 13 ኢንዱስትሪ ፓርኮችን በመገንባትና የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶችን በማስገንባት የስራ እድሎችን በመፍጠርና የውጭ ምንዛሬን እንዲሁም በቴክኖሎጂ ሽግግር በኩል የበኩሉን ሚና በመወጣት ላይ ይገኛል ብለዋል።

መንግሥት አቅም ያላቸው የሀገር ውስጥና የውጭ ባለሀብቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው እንዲሰሩ ለማድረግ በተሰራው የተቀናጀ ስራ በትናንትናው እለት ሦስት የሀገር ውስጥና የውጭ ድርጅቶች በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ለመስራት የሚያስችላቸውን የስምምነት ሰነድ ተፈራርመዋል።

የኢንዱስትሪ ፓርኮች ልማት ኮርፖሬሽን የአገር ውስጥ ኩባንያዎች ይበልጥ ተወዳዳሪና ተመራጭ እንዲሆኑ የሚያደርገውን ድጋፍ አጠናክሮ እንደሚቀጥልና ለስራቸው ስኬታማነትም አስፈላጊውን ድጋፍና ክትትል የሚያደርግ መሆኑንም አቶ አክሊሉ ገልፀዋል።

በኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው ለመስራት ስምምነት ከተፈራረሙት መካከል ሎንግ ማርች ኤሌክትሪካል ኢኩፕመንት ማኑፋክቸሪንግ ፒኤልሲ የተሰኘ የውጭ ኩባንያ አንዱ ሲሆን፤ በአዳማ ኢንዱስትሪ ፓርክ ሦስት ሺህ ካሬ ሜትር ሼድ በመከራየት በ240 ሚሊዮን ብር በላይ ኢንቨስመንት የኤሌክትሪክ መሳሪያዎችን በማምረት የሚሰማራ እንደሆነ አቶ አክሊሉ ጠቁመዋል። ምርቶቹንም ለሀገር ውስጥና ለውጭ ገበያ በማቅረብ ለ250 ዜጎች በቋሚነት የስራ እድልን እንደሚፈጥር ጠቅሰዋል።

እንደ አቶ አክሊሉ ገለጻ፤ ዋርቃ ትሬዲንግ ፒኤልሲ የተሰኘ የሀገር ውስጥ ኩባንያ ሌላኛው ስምምነት ያደረገ ኩባንያ ሲሆን፤ በሃዋሳ ኢንዱስትሪ ፓርክ አምስት ሺህ 500 ካሬ ሜትር ሼድ በመከራየትና ከ240 ሚሊዮን ብር በላይ ኢንቨስት በማድረግ የተለያየ አይነት የክር ምርቶችን የሚያመርት እንዲሁም ለ80 ዜጎች የስራ እድልን የሚፈጥር ነው።

ሌላኛው በቂሊንጦ ኢንዱስትሪ ፓርክ አንድ ሄክታር የለማ መሬት በመረከብ ከ205 ሚሊዮን ብር በላይ ኢንቨስት በማድረግ አላቂ የህክምና ቁሳቁሶችን ለማምረት የሚሰማራው ኤንኬ ዎርልድ ሜዲካል ኢኩፕመንት ማኑፋክቸሪንግ ፒኤልሲ ሲሆን፤ ለ210 ዜጎች የስራ እድል እንደሚፈጥር ገልጸዋል። ኩባንያው ሀገሪቱ በከፍተኛ የውጭ ምንዛሬ ከውጭ የምታስገባቸውን ምርቶች በሀገር ውስጥ በማምረቱ ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬን የሚያድን መሆኑን ጠቁመዋል።

በትናንትናው እለት የውል የስምምነት ሰነድ የተፈራረሙት ሦስቱ ድርጅቶች በጠቅላላው ከ448 ሚሊዮን ብር በላይ ኢንቨስትመንት ያስመዘገቡ ሲሆን፤ ለ540 ዜጎች ቋሚና ጊዜያዊ የስራ እድልን ከፍጠር በተጨማሪ ተኪ ምርት በማምረት የውጭ ምንዛሪ በማዳን፤ ምርቶቻቸውን ወደ ውጭ በመላክ የወጪ ንግድ ፍሰቱን በማሳደግ ረገድ ሚናቸው የጎላ ይሆናል።

በመላ ሀገሪቱ በሚገኙ 13 ኢንዱስትሪ ፓርኮች ከ125 በላይ የውጭና የሀገር ውስጥ አምራች ኩባንያዎች ወደ ኢንዱስትሪ ፓርኮች ገብተው እየሰሩ ሲሆን፤ ከ81ሺ በላይ ለሚሆኑ ዜጎች የስራ እድል በመፍጠር ከአንድ ቢሊዮን የአሜሪካን ዶላር በላይ ገቢ ማግኘት እንደተቻለ ተገልጿል።




# ኦሮሚያ ክልል የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ዋዜማን በተለያዩ ኩነቶች እያከበረ ነው

**ዋቅሹም ፍቃዱ**

አዲስ አበባ፡- የኦሮሚያ ክልል 17ኛውን የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ዋዜማ ከሕዳር 1 ቀን 2015 ዓ.ም ጀምሮ በተለያዩ ማህበረሰብ ተኮር ሥራዎች እየተከበረ መሆኑን ጨፌው አስታወቀ።

የጨፌ ኦሮሚያ አፈ ጉባዔ ወይዘሮ ሰዓዳ አብዱራህማን ጉዳዩን አስመልክተው ትናንት ጋዜጣዊ መግለጫ በሰጡበት ወቅት፣ እንደ አገር ሕዳር 29 ቀን በሐዋሳ ከተማ በሚከበረው የብሔሮች፣ ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ቀን ለመታደም ወደ ሥፍራው ለሚሄዱ እንግዶች በሞጆ፣ በአዳማ፣ በባቱ፣ በሻሸመኔ፣ ቢሻን ጉራቻና በጅማ አቀባበል ለማድረግ ዝግጅት መጠናቀቁንም ገልጸዋል።

እንደ ወይዘሮ ሰዓዳ ማብራሪያ፣ ክልሉ ክብረ በዓሉን ቀን በክልል ደረጃ በደማቅ ብሎም በአገር ደረጃ በደማቅ ሁኔታ ለማክበር የተለያዩ ዝግጅቶች እያደረገ ይገኛል። በክልሉ በአገር ደረጃ በዓሉ የሚከበርበት ቀን ክልሉን የሚወክሉ የባህል ቡድንን ከመላክ ጨምሮ የተለያዩ ዝግጅቶችን እያደረገ ነው።

ቀኑ በክልሉ ከሕዳር 1 ጀምሮ በበጎ አገልግሎት ሥራዎች፣ በችግኝ ተከላ፣ በሕዝባዊ ውይይቶች ፣ ለዓባይ ግድብ ድጋፍ በማሰባሰብ፣ የተለያዩ የልማት ሥራዎች በመጎብኘት እና በተለያዩ ስፖርታዊ እንቅስቃሴ እየተከበረ መሆኑን አፈ ጉባዔዋ አብራርተዋል።

ጥንታዊ የኦሮሞ ሕዝብ ባህልና እሴት መሰረት በማድረግ ጨፌ ኦሮሚያ የዜግነት አገልግሎት አዋጅን በማውጣት ሥራ ላይ እንዲውል በማድረግ በክልሉ መላውን ሕብረተሰብ በማሳተፍ በሰራው ሥራ አመርቂ ውጤት ማስገኘቱን የገለጹት አፈ ጉባዔዋ፤ ከዚህ አንጻር በዓሉን መሰረት ያደረገው በሉሜ ወረዳ የተተከሉ ችግኞች የመንከባከብ ሥራና ሌሎች የዜግነት አገልግሎቶች ሕዳር 1 ማስጀመሩንን አንስተዋል።

ቀኑን አስመልክቶ “ሕብረ-ብሔራዊ ፌዴራሊዝም ሥርዓት እና ዘላቂ ሰላም ግንባታ” እንዲሁም ‘የኦሮሞ ሕዝብ ከሌሎች ብሔሮች፣ ብሔረሰቦች እና ሕዝቦች ጋር በሰላም የሚኖርበት እሴት” በሚሉ ሁለት ርዕሰ ጉዳዮች ላይ ሰፋፊ ሕዝባዊ መድረኮች መደረጋቸውን የጠቆሙት ወይዘሮ ሰዓዳ፤ የኦሮሞ ሕዝብ ከወንድም ሕዝቦች ጋር ትናንት የነበረውን አብሮነት፣ ወንድማማችነት፣ አንድነት፣ ፍቅር እና አቃፊነት በበይበልጥ ለማጎልበት እንግዶችን ተቀብሎ ለማስተናገድ ዝግጅት ማድረጉን አመልክተዋል።

መልካም ጉርብትናና የአብሮነት እሴቶች ላይ ያጠነጠነ ዶክመንተሪ ፊልም ተዘጋጅቶ በኦቢን እየተላለፈ መሆኑን የተናገሩት አፈ ጉባኤዋ፤ በክልል ደረጃ በዓሉ ሕዳር 25 በሻሸመኔ ከተማ በፓናል ውይይት የሚከበር ሲሆን ሕዳር 26 ደግሞ የክብረ በዓሉ ማጠቃለያ እንደሚደረግም አክለው ገልጸዋል።

ዜና

# ስምምነቱ በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ተቀባይነትና ተደማጭነት ይበልጥ ያሳድጋል

## - ኢጋድን ለማጠናከር አባል አገራት ድጋፍ እንዲያደርጉም ኢትዮጵያ ጠይቃለች

**ሞገስ ጸጋዬ**



አዲስ አበባ፡- በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተፈረመው የሰላም ስምምነት በዓለም አቀፍ ደረጃ የኢትዮጵያን ተቀባይነትና ተደማጭነት ይበልጥ እንደሚያሳድግ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር አስታወቀ። ኢጋድ እንዲጠናከር አባል ሀገራት ድጋፋቸውን አጠናክረው እንዲቀጥሉም ኢትዮጵያ ጥሪ አቅርባለች።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ቃል አቀባይ አምባሳደር መለስ ዓለም ትናንት ለጋዜጠኞች እንደገለጹት፤ በኢትዮጵያ መንግሥትና በሕወሓት መካከል የተፈረመው የሰላም ስምምነት ዓለም አቀፍ ተቀባይነትና ድጋፍ እያገኘ ነው። ለኢትዮጵያ ሰላም ብቻ ሳይሆን ለአካባቢው ሰላምም ትልቅ ፋይዳ እንዳለውም እየተገለጸ ነው። በዓለም አቀፍ ደረጃም የኢትዮጵያን ተቀባይነትና ተደማጭነት ይበልጥ ያሳድጋል ተብሎ ይታመናል።

እንደ አምባሳደሩ ማብራሪያ፤ በኢትዮጵያና በሕወሓተ መካከል የተፈረመው ስምምነት ተግባራዊ እንዲሆን የአውሮፓ ሕብረት የገንዘብ ድጋፍ አድርጓል። በርካታ የመካከለኛው ምስራቅና የኤስያ አገሮች ድጋፋቸውን እየገለጹ ነው። የሰላም አየር መምጣቱን ተከትሎ ዓለም አቀፍ ኮንፈረንሶች ወደ ኢትዮጵያ እየመጡ ነው። ሰላም በመምጣቱ ምክንያት ተቀባይነቷ እየጨመረ መሆኑን የሚያሳዩ ናቸው። በዚህ ስምምነት አፍሪካ ችግሯን መፍታት መቻሏ ለሌሎች አገራትም ልምድ ሊሆን የሚችል ነው የሚል ሃሳብ በብዙ የአፍሪካ አገራት እየተነገረ ስለመሆኑም ገልጸዋል።

ኢትዮጵያ ወደ መደበኛና ተለምዷዊ ወደ ሆነ ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ተመልሳለች። ይህን ጉዳይ ይበልጥ በማስፋትና በማሳደግ ወዳጅ የማብዛት ስራ ይሰራል። የሱዳን ሽግግር ምክር ቤት ፕሬዚዳንት ለስምምነቱ ተግባራዊነት ሱዳን ሁሉን አቀፍ ድጋፍ እንደምትሰጥ መግለጿንም ተናግረዋል።

ኢትዮጵያ ባለፉት ሁለት ዓመታት ውስጥ ብዙ ፈተናዎችን አልፋለች ያሉት አምባሳደሩ፤ በዚህ ጊዜ የተገኙ የዲፕሎማሲያዊ ድሎችን የበለጠ ለማስፋትና ለማጽናት የሚያስችሉ ስራዎችን ለማከናወን ታስቧል ብለዋል። ከገጽታ ግንባታ አንጻር ባለፉት ሁለት ዓመታት በጦርነቱና ተያያዥ በሆኑ ጉዳዮች ላይ የነበሩ የገጽታ ችግሮችን ለማደስ ትልቅ ስራ ይሰራል ብለዋል።

በነበሩ ችግሮች ዲያስፖራው አገሩን ታድጓል ያሉት አምባሳደር መለስ፤ በቀጣይም መንግሥት ዜጎች በአገራቸው ጉዳይ አስተዋጽኦ እንዲኖራቸው እና የዜጎች ደህንነትና ክብር እንዲጠበቅም በትኩረት ይሰራል ብለዋል።

በድህረ ጦርነት የዳግም ግንባታ ጉዳይ በትኩረት የሚሰራ ይሆናል ያሉት ቃል አቀባዩ፤ ለዚህ የሚሆን በዓለም አቀፍ ደረጃ ገንዘብ የማሰባሰብ ስራ ትኩረት ከሚሰጣቸው ጉዳዮች መካከል አንዱ ነው ሲሉም ጠቅሰዋል።

በሰሜን ኢትዮጵያ ጦርነት ምክንያት ጉዳት የደረሰባቸው ቦታዎች ዳግም መገንባት፣ የተፈናቀሉትን ማቋቋምና ወደ ቀየአቸው እንዲመለሱ ማድረግ በትኩረት ከሚሰሩ ስራዎች ውስጥ ዋናዎቹ ናቸው። በ2023 በፈረንጆች አዲሱ ዓመት የኢትዮጵያን ዲፕሎማሲያዊ ግንኙነት ለማሳደግ ይሰራል። አምባሳደሮችም ለአገር የሚበጅ ስራ ይሰራሉ ተብሎ ታስቧል ብለዋል።

እንደ ቃል አቀባዩ ገለጻ፤ ከሶስት ዓመት ወዲህ በአካል በሱዳን መዲና የተካሄደው 48ኛው የኢጋድ የሚኒስትሮች መደበኛ ስብሰባ በዋናነት በቀጠናው ወቅታዊ ጉዳች ዙሪያ ያተኮረ ነበር። በሰላምና ጸጥታ፣ በሰው ሰራሽና በተፈጥሮ የደረሱ አደጋዎችን እንዴት በጋራ መከላከል እንደሚቻል ውይይት ተደርጓል።

ኢትዮጵያ ኢጋድ የተጠናከረና ችግር ፈቺ ተቋም እንዲሆን ሁሉም አባል አገራት ጠንካራ ድጋፍ እንዲያደርጉና የራሳቸውን ሚና እንዲወጡም መጠየቋን አምባሳደር መለስ ተናግረዋል። ከስብሰባው ጎን ለጎን ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትርና የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር አቶ ደመቀ መኮንን ከኬንያ ከፍተኛ ባለሥልጣን ጋር ኢትዮጵያና ኬንያ ግንኙነታቸውን ማጠናከር በሚችሉበትና በአፍሪካ ቀንድ ዘለቂ ሰላም በሚመጣበት ዙሪያ በጋራ ለመስራት ውይይት ስለማድረጋቸውም አብራርተዋል።

# «የኢትዮጵያ ህልውና የሚረጋገጠው ሰላም በማስከበር ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚዋን ከሌቦች ስንታደግ ጭምር ነው»

- መጋቢ ብሉይ አብርሃም ሃይማኖት
የኢሕአፓ ተቀዳሚ ፕሬዚዳንት

አዲስ አበባ፡- የኢትዮጵያን ህልውና ለማረጋገጥ ሰላም ለማስከበር ከሚደረገው ርብርብ ባሻገር የሃገርና የሕዝብ ሀብት በመበዝበዝ የሀገሪቱን ኢኮኖሚ እያዳከሙ ያሉትን ሌቦች በመከላከልና በማጋለጥ ሊሆን እንደሚገባ የኢሕአፓ ተቀዳሚ ፕሬዚዳንት መጋቢ ብሉይ አብርሃም ሃይማኖት አስታወቁ።

የኢሕአፓ ተቀዳሚ ፕሬዚዳንት መጋቢ ብሉይ አብርሃም ሃይማኖት ለአዲስ ዘመን እንዳስታወቁት፤ መንግሥታዊ ሌብነት ወይም ሙስና እንደሀገር ብዙ ዋጋ እያስከፈለ ያለ ጉዳይ ነው። በተለይም በአሁኑ ወቅት በከፍተኛ ደረጃ ተስፋፍቶና አቅሙን አደራጅቶ የሀገሪቱን ልማትና እድገት አንቆ የያዘበት ደረጃ ላይ ደርሷል።

«እስካሁን ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ ሁላችንም በሀገር ህልውና ጉዳይ ላይ ተጠምደን ስንቆይ ሌቦቹ ደግሞ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም የኢትዮጵያ ገጸ-በረከቶችን በመዝረፍ ላይ ተጠምደው ነበር» ሲሉ የተናገሩት መጋቢ ብሉይ አብርሃም አሁን ላይ አንጻራዊ የሚባል ሰላም በመስፈኑ የሕዝቡም ሆነ የመንግሥት ትኩረት እነዚህን ሌቦች በማጋለጥና በሕግ ተጠያቂ ማድረጉ ላይ ሊሆን እንደሚገባ አስገንዝበዋል።

«በአሁኑ ወቅት ሌብነት በሁሉም ተቋማት ተንሰራፍቶ ይገኛል። በእምነት ተቋማት ሳይቀር ስንሰለቱ ረዝሞ ሲታይ ያስደነግጣል። ሕዝቡም ደግሞ ሙስና ካልሰጠ የሚፈለገው ነገር የሚፈፀምለት ወደማይመስለው ደረጃ ላይ ደርሷል» በማለት የችግሩን አሳሳቢነት ገልፀዋል።

በእኔ እምነት ይህንን የፈጠረው ራሱ ማህበረሰቡ ነው ያሉት ተቀዳሚ ፕሬዚዳንቱ ፤ በተለይም ህብረተሰቡ የማይገባውን ሰው ስፍራ በመስጠቱ እንዲሁም ከዚህ ቀደም ሕዝብ ሲያስነቡ የነበሩ አንዳንድ ሰዎች ዳግሞ ሾልከው በመሾማቸው የሕዝብ ብሶት ምንጭ መሆናቸውን አስረድተዋል።

«ለሌብነቱ መስፋፋት ሕዝቡም ተጠያቂ ነው። እኛ መርጠን የሾምነው መልካም አስተዳደር ካላሰፈነና በሚገባ ካላገለገለን መልሰን የማውረድ መብታችንን ተግባራዊ ልናደርገው ይገባል» ያሉት መጋቢ ብሉይ አብርሃም፤ ሕዝቡ መንግሥት ርምጃ እስከሚወስድ መጠበቅ እንደሌለበትና ሌቦቹን በቃ ሊላቸው እንደሚገባ አስገንዝበዋል። ሁሉም በአካባቢው ያለውን የመንግሥት ሌባም ሆነ ግብረአባሮቹን ማጋለጥ እንደሚገባውም ተናግረዋል።

ተቀዳሚ ፕሬዚዳንቱ ሌቦቹን የማጋለጥና ለሕግ አሳልፎ የመስጠቱን ስራ ህብረተሰቡ ካላገዘ መንግሥት ብቻውን ሚናውን ሊወጣ እንደማይችል አመልክተዋል። ሙስናን ማፅዳትና የሙሰኞቹን ሰንሰለት መበጠስ የሚቻለውም የህብረተሰቡ ተሳትፎ ሲኖር ብቻ እንደሆነም ገልፀዋል። በአጠቃላይ ሙስና እንደፓርቲም የምንታገለው ጉዳይ ነው። መንግሥት ሌቦቹን ለሕግ አጋልጦ የመስጠቱን ሃላፊነት አጠናክሮ እንዲሄድ እንፈልጋለን» ብለዋል።

በዚህ ረገድ እስካሁን ከታች ያሉትን ሌቦችን በማጋለጥና በሕግ ተጠያቂ የማድረጉ ጥረት የሚደነቅ ቢሆንም መንግሥት በከፍተኛ መንግሥታዊ ሃላፊነት ላይ ተቀምጠው ሰንሰለት ዘርግተው ሀገር እየመዘበሩ ያሉትንም ላይ እርምጃ ሊወስድ እንደሚገባ አስገንዝበዋል። «ይህንን ማድረግ ከቻለ ሕዝቡ ራሱ ከመንግሥት ጎን ይሰለፋል፤ ያለፍርሃትም ያጋልጣል። ይህንን ማድረግ ካልቻለ ግን ራሱ መንግሥትንም አደጋ ውስጥ ነው የሚጥሉት» ሲሉ አሳስበዋል።

እንደእርሳቸው ገለጻ፤ ከኢህአዴግ ጊዜ ጀምሮ አሁንም ጃኬታቸውን ቀይረው የመጡ ሌቦች አሉ። እነዚህ ደግሞ ተራ ሙሰኞች አይደሉም፤ አሁን ኢትዮጵያ ላለችበት የኢኮኖሚ ቀውስ የዳረጉ ናቸው። አሁንም ሰንሰለታቸው አልተበጠሰም፤ እንደልባቸው እየፈነጩ ነው የሚገኙት። ኢትዮጵያ በውጭ ምንዛሬ እጥረት እየተፈተነች ባለችበት ወቅት እነሱ ግን ምንዛሬውን እንዳሻቸው እያንቀሳቀሱ ነው ያሉት። ከላይ ጀምሮ በደህንነት መዋቅር ውስጥ ሁሉ ገብተው በሰፊው እየሰሩ ያሉ ሌቦችንም ያለአንዳች መከልከል ለሕግ አሳልፎ መስጠት ይገባል።

# ከፍተኛ የመንግሥት...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ሙስና ኮሚቴ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ በቀለን ጨምሮ የተለያዩ በሙስና እና በብልሹ አሠራር ተሳትፈዋል ተብለው የተጠረጠሩ ግለሰቦችን በቁጥጥር ሥር በማዋል ሥራውን መጀመሩን አስታውቀዋል።

የኮሚቴው ሰብሳቢ እና የብሔራዊ መረጃና ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ተመስገን ጥሩነህ፣ ሙስና ከኑሮ ውድነትና ሥራ አጥነት ቀጥሎ የሀገር ደህንነት ሥጋት መሆኑን ገልጸው፤ በተደረገ ጥናት የሙስናና የብልሹ አሠራር ተግባራት በብዛት የተስተዋሉባቸውን ዘርፎች ዘርዝረዋል።

በተለይ በመንግሥት አገልግሎት አሰጣጥ በፋይናንስ ዘርፍ፣ በፍትህና በፀጥታ ዘርፎች፣ በሸያጭና ግዢ በተለይም ከመሬት ጋር በተያያዘ እንዲሁም በብድር አሰጣጥ ላይ እና እጥረት ባለባቸው የፍጆታ እቃዎች አቅርቦት ሰፋ ያለ ያለአግባብ የመበልጸግ እና የሌብነት ተግባራት የሚታዩ መሆኑን ጠቅሰዋል።

የሙስና ተግባራቱ ኅብረተሰቡን ያማረሩ ችግሮች መሆናቸውንና በአገር ዕድገትና የብልፅግና ጉዞ ትልቅ እንቅፋት እየሆኑ መምጣታቸውን ገልፀው፣ ችግሩን ለመቅረፍ ሙሰኞችን ተጠያቂ በማድረግ እየተሠራ መሆኑን ተናግረዋል። እስካሁን ባለው ሂደትም የኅብረተሰቡ ተሳትፎ እያደረገ መሆኑን ጠቅሰው፤ ይህም ተጠናክሮ እንዲቀጥል ጥሪ አቅርበዋል።

የብሔራዊ ኮሚቴው አባልና የፍትህ ሚኒስቴር ሚኒስትር ዶክተር ጌዲዮን ጢሞቲዎስ በበኩላቸው የመሬት አስተዳደር፣ የፀጥታና ፍትህ፣ ጉምሩክ፣ አገልግሎት አሰጣጥ ቅድሚያ ትኩረት ከተሰጣቸው ዘርፎች መካከል መሆናቸውን ገልፀው፤ በተለይ የመሬት አስተዳደር እና በፍትህና ፀጥታ ተቋማት ላይ እርምጃ እየተወሰደ ነው ብለዋል።

በልማት ተነሺ ስም በሀሰተኛ ሰነድ መሬት የሰጡ እንዳሉ የጠቀሱት ዶክተር ጌዲዮን፤ ለአብነት በአዲስ አበባ ከተማ 175 ሺህ ካሬ መሬትና ከፍተኛ መጠን ያለው ሀብት እንዲሁም የኮንዶሚኒየም ቤት የመዘበሩ ተጠርጣሪዎች በቁጥጥር ሥር እየዋሉ መሆኑን ገልፀዋል።

በፍትህና ፀጥታ ዘርፍ ሥልጣናቸውን አላግባብ በመጠቀም ከግለሰቦችና ድርጅቶች ገንዘብ የተቀበሉ አካላትም በተመሳሳይ በቁጥጥር ሥር እየዋሉ ነው ብለው፤ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት ዋና ዳይሬክተር አቶ ቴዎድሮስ በቀለን ጨምሮ የተለያዩ የፍትህና ፀጥታ የሥራ ኃላፊዎች በቁጥጥር ሥር መዋላቸውንና የክስ ምስረታ ሂደት ላይም መሆኑን ገልፀዋል። እርምጃ የመውሰዱ ተግባር ተጠናክሮ ይቀጥላልም ሲሉ አክለዋል።

በአንድ ሳምንት ውስጥ ከ250 በላይ ጥቆማዎች በተለያዩ መንገዶች ቀርበው ማጣራት እየተከናወነባቸው መሆኑን የገለጹት ዶክተር ጌዲዮን፤ በክልሎችም ከትንሽ እስከ ከፍተኛ የተደራጀ ሌብነት ተሳታፊዎች ተጠያቂነት የማስፈኑ ሥራ ተጠናክሮ እንደሚቀጥል ገልጸዋል።

# በጉባኤው የተነሱ...

ከ1ኛው ገጽ የዞረ

ጉባኤ እንዲካሄድ ላደረጉ ባለድርሻ አካላትም ምስጋና አቅርበዋል።

የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስትር ዶኤታ ሁሪያ አሊ በበኩላቸው፤ በጉባኤው ከ170 በላይ አገራት የተሳተፉ መሆናቸውን ጠቅሰው፤ በተለይም ያልተቆራረጠ የኢንተርኔት ተደራሽነት እንዲኖር በርካታ ሃሳቦች ተንሸራሸረዋል ብለዋል።

ሚኒስትር ዴኤታዋ እንዳሉት፤ ከ300 በላይ ውይይቶች የተካሄደ ሲሆን በዚህም ከ2 ነጥብ 7 ቢሊዮን በላይ ከኢንተርኔት ውጭ የሆነውን ሕዝብ ተጠቃሚ ለማድረግ መስራት እንደሚገባ የቤት ስራ የሰጠ ጉባኤ ነው። ስኬታማ የሆነውን ጉባኤ ለማጠናቀቅ ያለእረፍት የበኩላቸውን ድርሻ ለተወጡ ባለድርሻ አካላትም ምስጋና ይገባል።

በተባበሩት መንግሥታት የአፍሪካ ኢኮኖሚክ ኮሚሽን ተጠባባቂ ዋና ሥራ አስፈፃሚ አንቶኔዮ ፔድሮ፤ አፍሪካውያን ግልጽና አካታች የዲጂታል ስትራቴጂ በመንደፍ በይነመረብን ተደራሽ ለማድረግ መስራት አለባት ብለዋል። ጉባኤው በስኬት እንዲጠናቀቅ ላደረጉ የተባበሩት መንግሥታት ድርጅት፣ ለፎረሙ አዘጋጆችና ለኢትዮጵያ ሕዝብ ምስጋና አቅርበዋል።

የኢንተርኔት አባት በመባል የሚታወቁት ቬንት ሰርፍ በበኩላቸው ኢትዮጵያ ጉባኤውን በሚገባ አስተናግዳለች፤ በቀጣይም ወደ ኢትዮጵያ መጥቼ ጉብኝት አደርጋለሁ፤ ጉባኤው በቀጣይ በኢንተርኔት አስተዳደርና አጠቃቀም ላይ ለሚሰሩ ስራዎች ትልቅ ግብአት የተገኘበት ነው ሲሉ ገልጸዋል።

በርካታ የጉባኤው ተሳታፊዎች በሰጡት አስተያየት ሕዝቦችን በተለይም ህጻናትን ከጥቃት መከላከል፣ መረጃን በአግባቡ ማስተዳደር፣ የግል መረጃን መጠበቅ፣ የተቆራረጠ የበይነ መረብ አገልግሎትን በመቅረፍ ከበይነመረብ ውጭ የሆኑ ሕዝቦችን ማገናኘት፣ ደህንነትን ማረጋገጥ፣ ጥበቃ ማድረግና ከበይነ መረብ ውጭ የሆኑ ህዝቦችን ማገናኘትና መሰል የኢንተርኔት ደህንነትን በተመለከተ ለሚከናወኑ ተግባራት ሰፊ ግብአት የተገኘበት ነው።

በአዲስ አበባ ኢትዮጵያ ምቹ የሆቴል መስተንግዶና አዝናኝ ጊዜ እንደነበራቸውም በመግለጽ ለተደረገላቸው መስተንግዶ አመስግነዋል።

የቀያሚ መጽሔት

# አገልግል



«ኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ሊኖራት የሚችለው አገር አቀፍ ምክክሩ ሲሳካ ነው»

- መጋቢብሉይ አብርሃም ሃይማኖት
የኢህአፓ ተቀዳሚ ፕሬዚዳንት

ገጽ 6

የአረፍት ቀናትና የአዕምሮ ሰዓት

ገጽ 11



«ልጄን ትፈጠር ብዬ ተውኳት»

- እናት ጥሩ ማዕድ አስፋው

ገጽ 16



# የዘመን እንግዳ

## ‹‹ኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ሲኖራት የሚችለው አገር አቀፍ ምክክሩ ሲሳካ ነው››

- መጋቢብሉይ አብርሃም ሃይማኖት
የኢህአፓ ተቀዳሚ ፕሬዚዳንት

ማህሌት አብዱል

**የመጀመሪያ ደረጃ ትምህርታቸውን በአዳማ አፄ ገላውዲዮስ ትምህርት ቤት የተማሩ ሲሆን በዳግማዊ ምኒልክ ትምህርት ቤት ደግሞ የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን ተከታትለዋል። ጎን ለጎንም ደብረሊባኖስ በአብነት ትምህርት ሲከታተሉም ቆይተዋል። አስተዳደጋቸው ከኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ጋር በእጅጉ የተቆራኘው እንግዳችን በተለይም ወላጅ አባታቸውም የቤተክርስቲያን አገልጋይ ከመሆናቸው ጋር ተያይዞ መንፈሳዊውን ዓለም የበለጠ ለማወቅ ልባቸው ወደ መንፈሳዊው ትምህርት አዘነበለ። እናም በስነ-መለኮት በአገር ውስጥና በግሪክ ተምረው ከመጀመሪያ ዲግሪ እስከ ዶክትሬት ዲግሪያቸውን አገኝተዋል።**

**በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያ ውስጥ በተለያዩ መንፈሳዊ አገልግሎቶች ላይ የቆዩት እኚሁ ሰው በተለያዩ አገራት በሚገኙ አብያተ ቤተክርስቲያናት በመዘዋወር መንፈሳዊ አገልግሎታቸውን በትጋት መወጣታቸው ይነገራል። እንግዳችን በውጭ በነበሩበት ጊዜ ከበርካታ ፖለቲከኞች ጋር የመገናኘቱ እድል ስለነበራቸው በማህበራዊ፤ በመንፈሳዊ ጉዳዮች ላይ በመምከር ስለፖለቲካውም ያላቸውን እውቀት አጎልብተዋል። በተለይም በስደት ላይ ይገኙ ከነበሩ የኢህአፓ አባላት ጋር ይበልጥ በመቀራረባቸው በፖለቲካ አሳቤያቸው ተማረኩ። ቀድሞውንም ደግሞ የ€€ሶሻል ዲሞክራሲ« ርዕዮተ ዓለም ደጋፊ በመሆናቸው ልባቸው ወደ ኢህአፓ አዘነበለ።**

**ለውጡ ሲመጣም በውጭ ሳሉ ፖለቲከኞች ጥሪ ሲቀርብ አሳቸውም ድርጅቱ ውስጥ ተቀሳቀሉ። በድርጅቱ ውስጥ በተለያዩ ከፍተኛ ኃላፊነቶች ላይ ሲሰሩ ቆይተው በአሁኑ ወቅት የኢህአፓ ተቀዳሚ ፕሬዚዳንት ሆነው እንዲሁም ዋናው የጋራ ምክር ቤት አቅም ግንባታ ሰብሳቢ በመሆን በማገልገል ላይ ይገኛሉ። አዲስ ዘመን ጋዜጣ የኢህአፓን ተቀዳሚ ፕሬዚዳንት መጋቢ ህሩይ አብርሃም ሃይማኖትን €€የዘመን እንግዳ« አድርጓቸዋል።**



ፎቶ፡ ሀዱሽ አብርሃ

**አዲስ ዘመን፡- የመንፈሳዊ አገልጋይ ሆነው ሳለ ወደ ፖለቲካ ሲገቡበት የቻሉበትን ምክንያት ያብራሩልና ውይይታችንን እንጀምር?**

**መጋቢብሉይ አብርሃም፡-** በነገራችን ላይ ‹‹ፖለቲካ›› የሚለው የግሪክ ቃል የመፍትሔ ሃሳብ ማለት ነው። ደግሞም የመፍትሔ ሃሳብ የሌለው ፍጡር የለም። እኔም የራሴን አስተዋፅኦ በአገሬ ላይ ለማበርከት አስቤ ነው የገባሁት። ስለዚህ ከመንፈሳዊ አገልግሎት ወደ ፖለቲካው ስገባ ብዙ አልከበደኝም። በእርግጥ የመንፈሳዊው ዓለም ብዙ መልካም ትምህርቶችና መልካም በጎ ጎኖች አሉት። በተለይ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን የብዙ እውቀቶችና ፀጋዎች ባለቤት እንደመሆንዋ ከቤተክርስቲያኒቷ የቀስምኩት እውቀት ቀላል የሚባል አይደለም። ያንን እውቀት በመጠቀም የራሴን አስተዋፅኦ ማበርከት እንደምችል ስለተሰማኝ እንዲሁም ኢህአፓ ታሪካዊ ድርጅት በመሆኑ፤ በዚህ ድርጅት ውስጥ ደግሞ ብዙ አቅም የነበራቸው ሰዎች ያሉበት በመሆኑ በጋራ መስራት እንደምችል አምኜ ነው ድርጅቱን የተቀላቀልኩት። እንዳሰብኩትም ፓርቲው ውስጥ በመግባቴ የተሻለ ግንዛቤና እውቀት እንዲኖረኝ አድርጎኛል።

**አዲስ ዘመን፡- ፓርቲውም ሆነ አባላቶቹ አንጋፋ እንደመሆናቸው እንደእርሶ ሳለ ወጣት ፖለቲከኛ ተግባብቶ መስራት ያስቸግራል የሚል ስጋት አላደረቦትም?**

**መጋቢብሉይ አብርሃም፡-** እንዳልሽው ፓርቲው አንጋፋ ድርጅት ነው፤ በተለይ በዚያ ጊዜ የነበሩትና የ60ዎቹ ትውልድ የሚባሉት በኢትዮጵያ ታሪክ ውስጥ ብዙ በጎ ነገሮችን አበርክተዋል። የዚያኑ ያህል ብዙ ክፉ ነገሮች አሉት ይሄ ደግሞ አጠያያቂ አይደለም። በመሰረቱ እኔ ያ ትውልድ ፍፁም ነው ብዬ የማምን ሰው አይደለሁም። ነገር ግን ከዚያ ትውልድ ጋር ተያይዞ ሁሉንም ነገር አጣጥሎ መሄድ የለበትም። መልካሙን ነገር ከትውልድ ትውልድ መሸጋገር ይገባዋል ብዬ ስለማምን ነው ፓርቲው ውስጥ ገብቼ የራሴን በጎ አሻራ ለማሳረፍ እየሰራሁ ያለሁት። በነገራችን ላይ ነሃሴ ወር ላይ የፓርቲውን 50ኛ ዓመት ስናከበር በርካታ የመንግስት ከፍተኛ አመራሮችና የፖለቲካ መሪዎች በተገኙበት የዚያ ትውልድ አባላት በይፋ ይቅርታ ጠይቀዋል።

እኔ እንደአዲስ የፓርቲው መሪ ያ ትውልድ ክፉውን ነገር በይቅርታ በማለፍ፤ በጎውን ነገር ደግሞ ማስቀጠል ይቻላል ብዬ አምናለሁ። በነገራችን ላይ የዚያ ትውልድ አካል የሆነው አክራሪ ብሔርተኛ በመሆን እርስ በርስ ሲያባላን እንደቆየ የማንክደው ሃቅ ነው። ይህ አካል ከአንድነት ኃይሉ ጋር ለመተባበሩና በጥበብ አለመዳዙ ከዚያም በላይ ደግሞ የደርግ አምባገነንት ሕብረ-ብሔራዊ አንድነት የሚያቀነቅነውን ኃይል እንዲጠፋ አድርጎታል። እርስበርስ በጥላቻ የፖለቲካ ምህዳር ያለመስፋቱ ክፉው ኃይል እንዲበረታ አድርጎታል። በተለይ ደግሞ የፅንፈኛ አካል በውጭ ኃይሉ ይደገፍ ስለነበር፤ እርስበርስ በማፋጀት በተለያዩ ቦታ ላይ የእነሱን አጀንዳ የሚያስፈፅሙ አካላትን ሲያደራጁና ሲደግፉ ነው የኖሩት።

በመሆኑም የውጭ ጠላቶቻችን ያንን ትውልድ ታሪካዊ ምድር የሆነችውን ሃገራችንን ለመበጥበጥ እንደመሳሪያ ተጥቀመውበታል። አሁን ያለው ትውልድም ቢሆን ታሪኩን እንዲረሳና ማንነቱን እንዲጠላ በማድረግ የእጅ አዙር ቀኝ ግዛት ዓላማቸውን ሲያስፈፅሙ ነው የኖሩት። ያም ቢሆን ግን በጎ ነገሩን ከማንሳት ይልቅ ክፉውን ነገር ብቻ ይዞ ያንን ትውልድ በደፈናው የማይረባ አድርጎ መቁጠሩ ትክክል አይደለም። በተለይ ኢህአፓን ካነሳሽ ኢትዮጵያን ለማዳን የተከፈለውን መስዋዕትነት መዘንጋት አይቻልም፤ ስለሆነም ከዚያ ትውልድ በጎ ነገሩን ይዘን እኛ ደግሞ መቀጠል አለብን የሚል እምነት ስላለኝ ነው ኢህአፓ ውስጥ በድፍረትም በደስታም የገባሁት።

**አዲስ ዘመን፡- አገሪቱ ከሁለት ዓመት ሳላነሰ ጊዜ በጦርነት ቆይታ በቅርቡ የሰላም ስምምነት መፈፀሙ በግሉት ምን አይነት ስሜት ፈጠረቦት?**

**መጋቢብሉይ አብርሃም፡-** በነገራችን ላይ ቀደም ሲል ጦርነቱ እንዲያበቃና የትግራይ ህዝብ ነፃ እንዲወጣ ደጋግመን ስናሳስብ ቆይተናል። ከነበረው ሁኔታ አንፃር ስምምነቱ እውን ይሆናል ብሎ ማሰብ ከባድ ነበር። የፖለቲካ ኃይሎቹ ፅንፍ የያዘ አቋም ለድርድር የማይመች ስለነበር እንደማኛውም ዜጋ አሳስቦኝ ነበር። የሚሆንም አልመሰለኝም ነበር። ነገር ግን የህግ የበላይነት እንዲረጋገጥ ለመንግስት አስፈላጊውን ድጋፍ ስናደርግ ቆይተናል። በዚህ አጋጣሚ የኢትዮጵያ ተፎካካሪ ፓርቲዎች ዲሞክራሲያዊ የሆነ የፖለቲካ ጅምር እንዳለ ማሳያ ከምርጫው ጊዜ ጀምሮ አኩሪ ተግባር መፈጸማቸው ሳላደንቅ አላልፍም። ደግሞም ሌላው የፖለቲካ ኃይል ተጨምሮ ቢሆን ኖሮ ኢትዮጵያ እንደአገር ትፈተንና አደጋ ውስጥ ትውድቅ እንደነበር ግልፅ ነው። ሆኖም እኛ የበለጠ በሰለጠነ የፖለቲካ አካሄድ በመመራትና አገርን በማስቀደም፤ በአገር ጉዳይ ላይ ባለመደራደር፤ ኢትዮጵያ የሁላችንም ናት የሚል እምነትን በማሳደር መረባረባችን ጠቅሞናል የሚል እምነት አለኝ።

በመሰረቱ የጋራ አገራችንን ኢትዮጵያ ለገዢው ብልፅግና ፓርቲ ብቻ የምንተዋት አይደለችም፤ በዚህ መንፈስ ሁሉም ፓርቲዎች በጋራ መደጋገፍ አለብን የሚለውን ቁርጠኝነት ይዘን ህዝቡን በጋራ በማስተባበር ስንሰራ ቆይተናል። ፓርቲያችን ደግሞ እንደሚታወቀው በስደት የሚኖሩ በርካታ አባላት ያሉት በመሆኑ በ ‹‹No more›› እንቅስቃሴው ከፍተኛ ሚናቸውን እንዲወጡ ፓርቲው አስፈላጊውን ነገር አድርጓል። ከዚያም በተጨማሪ ደግሞ እንደአገር የገጠመንን ችግር በጋራ የሰው ኃይልንም ጭምር በማቅረብ ሚናችንን ተወጥተናል። ለምሳሌ የቀድሞ የኢህአፓ ሰራዊት ተዋጊ የነበሩትን ጭምር ተሳትፈው የተሰውም አሉ።

በዚህ ልክ በአገራዊ ጉዳይ መተባበራችን የውጭ ኃይሎችን አስጨንቋል፤ ጠላቶቻችንንም አሳፍሯል። እንደአገር ደግሞ አኩሪ ተግባር ተፈፅሟል ባይ ነኝ። የኢትዮጵያ መንግስትም ለሰላም ቅድሚያ በመስጠቱ የሃሳብ ልዩነትን በጥላቻ ሳይሆን በመቀራረብ እንዲፈታ ጥረት አድርጓል። ስለዚህ ይሄ ሁሉ ተደማምሮ ኃይል ሆኗል። በዚህ ምክንያት ችግር ፈጣሪዎችም ሆነ የውጭ ኃይሉ የሚገቡበትና የህዝቡን አንድነት የሚሸረሽሩበት እድል ጠፍቷል። ስምምነቱ የውጪ ኃይሎች ጭምር እጃቸውን እንዲሰበስቡ ምክንያት ሆኗል። በነገራችን ላይ በውጪ ጣልቃ ገብነት የፈረሱ ሊቢያንም ሆነ ኢራቅን አብነት አድርገን መጥቀስ እንችላለን። በአህጉራችንም ሴንትራል አፍሪካ ዛሬ ምንላይ እንዳለች ማየት በቂ ነው።

በዚህ ሁሉ ሴራና ውስብስብ ችግር ውስጥ ሆኖ ለሰላም መቀመጡ በራሱ ትልቅ ድል ነው። የመላው ኢትዮጵያዊ አንድነትና የጥምር ኃይሉ እንዲሁም የአገር መከላከያ ቆራጥነት ለሠላም መሠረት እንደሆነ ግልፅ ነው። ያም ቢሆን ግን ለሰላም አማራጭ ተስማምተው መሄዳቸው ለእኛ ድርብ ድል ነው ብለን ነው የምናምነው። በአጠቃላይ ለሰላም እድል መስጠቱን እናደንቃለን። በተጨማሪም ለዚህ ሰላም ስምምነት እውን መሆን የትግራይ ህዝብ ቆራጥነትም ሊዘነጋ አይገባም። አሁን ላይ እንደምንሰማውም በተለይ የአገር መከላከያ ሰራዊት በተቆጣጠረባቸው አካባቢዎች የትግራይ ህዝብ ከፍተኛ ድጋፍ እየሰጠ ነው ያለው። ይህ ደግሞ ለሰላም ያለው ቁርጠኝነት ማሳያ ነው።

**አዲስ ዘመን፡- ስምምነቱ በተጨባጭ ወደ መሬት እንዲወርድ በመንግስት በኩል እየተደረገ ያለውን ጥረት እንዴት አዩት? ምንስ ይቀራል?**

**መጋቢብሉይ አብርሃም፡-** መንግስት በተለይ ለተጎዳው የትግራይ ህዝብና ከፍተኛ ጦርነት ማረፊያ የሰሜኑ አካባቢ የሰብአዊ ድጋፍ እንዲዳረስ እያደረገ ያለው ጅምር ጥረት የሚበረታታ ነው። ይሄ ጦርነት እንደሚታወቀው መላውን ህዝብ ጠባቂ ያደረገ፤ የአገራችንንም ኢኮኖሚ ለከፋ ጉዳት ያጋለጠ ሆኗል። እንደመንግስት እየወሰዳቸው ያላቸውን አማራጮችን ስንመለከት በእውነት ለመናገር የሚደነቅ ነው። ትላንትና ብዙ ሲሉ የነበሩ የውጭ ኃይሎችም አስፈላጊውን ድጋፍ ሲያደርጉ አልታዩም። በዚህ አጋጣሚ መንግስት ግን ያለውን አቅም በመጠቀምና ከጥቂት በጎ አድራጊ ወዳጅ አገራት ጋር በመሆን እየሰራቸው ያላቸው ስራዎች የሚበረታቱ ናቸው። የበለጠ ተደራሽ እንዲሆኑ መስራት ያስፈልጋል። እኛም ብንሆን ይሄ የመንግስት ስራ ብቻ አይደለም ብለን ፓርቲዎች ሰፊ ስራ እየሰራን ነው የምንገኘው። አሁን አስፈላጊውን ድጋፍ ለማድረግ ተዘጋጅተናል።

ለዚህ ደግሞ የትግራይ ህዝብ ያለምንም ማመንታት

ወቅታዊ እና ቃለ ምልልሶች

# የዘመን እንግዳ



**በአጠቃላይ ሙስና እንደፓርቲም የምንታገለው ጉዳይ ነው። መንግስት ሌቦቹን ለህግ አጋልጦ የመስጠቱን ኃላፊነት አጠናክሮ እንዲሄድ እንፈልጋለን። እስካሁን ከታች ያሉትን ሌቦች የማጋለጥ ነገር አይተናል፤ ግን ደግሞ በከፍተኛ የመንግስታዊ ኃላፊነት ላይ ተቀምጠው ሰንሰለት ዘርግተው አገር እየመዘበሩ ያሉትንም ላይ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል። ይህንን ማድረግ ከቻለ ህዝቡ ራሱ ከእሱ ጎን ይሰለፋል፤ ያለፍርሃትም ያጋልጣል**

ከሰላም ስምምነቱ የሚያፈነግጠውን አካል መቃወምና ማጋለጥ ይገባዋል። በህዝብና በመንግስት መሃል ጥርጣሬ እንዲፈጠር የሚያደርጉትንም መከላከል አለበት። አንዳንድ ጊዜ እንደምንሰማው በድርድሩ ያልተነሱ ኃሳቦችን ጭምር በማንሳት ህዝብ ከህዝብ ጋር ለማጋጨትና ሌላ ቀውስ ለመፍጠር እየተደረጉ ያሉ ሴራዎች አሉ። እንዲሁም የሰላም ስምምነቱን በተለያየ መንገድ በመተርጎም መፈፀም ከሚገባው ጊዜ በላይ እንዳይወስድ መንግስት ሚናውን ሊወጣ ይገባል። አስፈላጊውን ዝግጅት ማድረግ ይጠበቅበታል። እኛም ፓርቲዎች በዚህ ጉዳይ ላይ ድጋፍ ልናደርግ ይገባል። በአጠቃላይ ይህ የሰላም ስምምነት ለትግራይም ሆነ ሌላው የኢትዮጵያ ህዝብ በጣም አስፈላጊ በመሆኑ ይህንን ስምምነት አለመደገፍ አንችልም።

በግሌ ኢትዮጵያ ከዚህ ሰላም ስምምነት ብዙ ነገር ታተርፋለች የሚል እምነት አለኝ። ተገደን የገባንበትን የህልውና ዘመቻ ደግሞ አሁን ወደኋላ እንዲመለስ መፍቀድ የለብንም።

**አዲስ ዘመን፡- የምክክር ኮሚሽኑ በአገሪቱ ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ ምን ይጠበቅበታል ብለው ያምናሉ?**

**መጋቢ ብሉይ አብርሃም፡-** ኢትዮጵያ ዘላቂ ሰላም ሊኖራት የሚችለው አገር አቀፍ ምክክሩ ሲሳካ ነው ብዬ አምናለሁ። የኢትዮጵያ ህዝብ የተለያዩ ጥያቄዎች አሉት እንዲሁም እንደአገር ደግሞ የምንጠይቀው አለ። በእርግጥ ጥያቄዎች እንደየአካባቢው ይለያያሉ። በዚህ ረገድ የኮሚሽኑ መቋቋሙም ሆነ ተቋሙን የሚመሩ አካላት ምርጫ ላይ እንደ ኢህአፓ ቅሬታ የለንም። የተመረጡት ሰዎች ይህንን አገራዊ ኃላፊነት በብቃት ሊወጡ እንደሚችሉ እምነት አለን። ይሁንና ህዝቡ የኮሚሽነሮቹን ሚና በቅጡ ተረድቷል ብዬ አላምንም። የእነሱ ዋነኛ ሚና አጀንዳ መሰብሰብ ነው። ለምሳሌ የህገ-መንግስት ጥያቄ አለ፤ የሰንደቅ አላማ ጥያቄ አለ፣ የፌዴራሊዝሙ ጉዳይ አለ። አጀንዳ ከታች ነው የሚነሳው። ስለዚህ ሁሉም በእኩልነት የሚስተናገድበት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይገባል።

እንደሚታወቀው የህዝቡ ጥያቄ እንደአገር ያልተግባባንባቸው፤ ልዩነት የፈጠርንባቸው፤ ኢትዮጵያ የታመመችባቸው ችግሮች አሉ። ይህንን መንግስት አልፈፅምም እንኳን ቢል በአደባባይ ይጋለጣል። አለመፈፀም ራሱ አይችልም። ባይፈፅመው ህዝብ ይታገለዋል። ሆኖም ጊዜ እንደሚፈጅ ይታወቃል። ስጋቴ ግን አጀንዳ የመሰብሰቡን ሂደት የፖለቲካ ካድሬዎች ብቻ እንደልባቸው የሚፈነጩበት እንዳይሆን ነው። ስለዚህ ጥንቃቄ ማድረግ ያስፈልጋል። ተፎካካሪ ፓርቲዎችም ሆነ ሁሉም አካል ሊሳተፍበት ይገባል። በአጠቃላይ አጀንዳዎቹ ሲሰበሰቡ በእኩልነት የሚቀርብ ሃሳብ ወይም አናሳ ተብሎ እንዳይኖር ማድረግ ያስፈልጋል። ምክንያቱም የሁሉም ሃሳብ ለኢትዮጵያ ያስፈልጋታል። የሁሉንም ጥያቄ ስትመልስ ነው ኢትዮጵያ የሁላችንም የምትሆነው። ሁሉንም ጥያቄ ደግሞ በፍቅር ማየት አለብን።

በመሰረቱ በርካታ የአለም አገራት ወደ ሰላም የመጡት በአገራዊ ምክክር ነው። ጀርመኖች ከሂትለር አስከፊ ጭፍጨፋ በኋላ ልዩነቶቻቸውን የፈቱት አስቀድመን የጠቀስናቸው የህግ ተጠያቂነትን በማስፈንና ህዝባዊ ውይይት በማድረግ ነው። በተመሳሳይ ደቡብ አፍሪካ ላይም ከዚያ ሁሉ የአፓርታይድ ጭፍጨፋ በኋላ ነጩም ሆነ ጥቁሩ በፍቅርና በሰላም መኖር የጀመረው አገር አቀፍ ምክክር በመደረጉ ነው። እርግጥ ነው አካታችነት ከሌለ ልክ እንደደቡብ ሱዳን ምክክሩ የከሸፈ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ የእኛም አገር አቀፍ ምክክር እንዲከሽፍ አንፈልግም። ነገር ግን አሁን ባለው ነባራዊ ሁኔታ የሚከሽፍ ነገር እንደሌለ እርግጠኛ ነኝ።

ተፎካካሪ የፖለቲካ ፓርቲዎች በሚቻለው መጠን መሰባሰባችን አስፈላጊ ነው ብለን ስለወሰድን ትልቅ ስራ ጀምረናል። ሰብሰብ ብለን ኃይል ፈጥረን አገራችንን ማዳን አለብን ወደሚል ድምዳሜ ላይ መጥተናል። እንደአገር ደግሞ የእኛን አስተዋፅኦ ኢትዮጵያ ትፈልጋለች፤ ምክንያቱም ኢትዮጵያ የአንድ ግለሰብ ወይም የጥቂት ሰዎች ስብስብ ብቻ አይደለችም። የእኔ፣ የአንቺ፣ የሁላችንም ናት። ስለዚህ እንደህዝብ በአገር ጉዳይ ላይ ንቁ ተሳታፊ መሆን ያስፈልጋል። የምንችለውን አስተዋፅኦ ማድረግ መቻል አለብን። ሃሳቦቻችንን ያለከልካይ ልናቀርብ ይገባል። ይህንን ካደረግን የማይሳካ ነገር የለም። በግሌ በዚህ በአገር አቀፍ ምክክሩ ተስፈኛ ነኝ። በተለይ ህገ-መንግስቱ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች ቀርበው መፍትሔ ይሰጣቸዋል ብዬ አምናለሁ። በነገራችን ላይ ኢህአፓ ሃገርአቀፍ ውይይት እንዲደረግ 40 ዓመት ጮኋል። ግን ሰሚ ሳያገኝ ነው የቆየሁ። አሁን ደግሞ ያለው መንግስት የምክክርን አስፈላጊነት ተገንዝቦ ምህዳሩን ማመቻቸቱ በራሱ ልናመሰግነው እንወዳለን። በቀጣይም ምክክሩ ሁሉንም እንዲያሳትፍ፤ ሃሳቦች ያለገደብ እንዲንሸራሸሩ የበኩሉን ጥረት ማድረግ ይገባዋል።

**አዲስ ዘመን፡- አሁን ላይ ህዝብን በከፍተኛ ደረጃ እያማረረ ያለው ሙስናን ለመከላከል በመንግስት የተጀመረውን ጥረት እንዴት ያዩታል? ከችግሩ ስፋት አንፃር ምን ሊሰራ ይገባል ይላሉ?**

**መጋቢ ብሉይ አብርሃም፡-** ሙስና እንደአገር ብዙ ዋጋ እያስከፈለን ያለ ጉዳይ ነው። አሁን ላይ እጅግ በሚገርም ሁኔታ ተስፋፍቶና አቅሙን አደራጅቶ የአገሪቱን ሁሉ ነገር አንቆ የያዘበት ደረጃ ላይ ደርሰናል። በአጠቃላይ ሌብነት በሁሉም ተቋማት ተንሰራፍቶ ይገኛል። በእምነት ተቋማት ሳይቀር ሰንሰለቱ ረዝሞ ሲታይ ያስደነግጣል። ህዝቡም ደግሞ ሙስና ካልሰጠ የሚፈለገው ነገር የሚፈፀምለት ወደማይመስለው ደረጃ ላይ ደርሷል። በእኔ እምነት ይህንን የፈጠረው ራሱ ማህበረሰቡ ነው። በነገራችን ላይ የማይገባውን ሰው ስፍራ መስጠት ለራስም ሆነ ለአገር አደጋ አለው። የኢትዮጵያ ህዝብ እንደሚታወቀው ‹‹ከሰው መርጦ ለሹመት፤ ከእንጨት መርጦ ለታቦት›› እንደሚባለው ከዚህ ቀደም ስንት ህዝብ ሲያስነቡ የነበሩ ሰዎች ዳግም ተሹመው የህዝብ ብሶት ምንጭ ሆነዋል።

እኔ በበኩሌ ለሌብነቱ መስፋፋት ህዝቡም ተጠያቂ ነው ባይ ነኝ። እኛ መርጠን የሾምነው መልካም አስተዳደር ካላሰፈነና በሚገባ ካላገለገለን መልሰን የማውረድ መብታችንን ተግባራዊ ልናደርገው ይገባል። መንግስት ርምጃ እስከሚወስድ መጠበቅ የለብንም፤ ህዝቡ ራሱ ሌቦቹን በቃ ሊላቸው ይገባል። ያ ማለት አመፅ መቀስቀስ ማለት አይደለም። ሁሉም በአካባቢው ያለውን የመንግስት ሌባንም ሆነ ግብረአበሮቹን ማጋለጥ አለበት። ይህንን ማድረግ ካልተቻለ መንግስት ብቻውን ሚናውን ሊወጣ አይችልም። ሙስናን ማፅዳት የምንችለው የህብረተሰቡ ተሳትፎ ሲኖር ነው። የኢትዮጵያ ህልውና የሚረጋገጠው ሰላም በማስከበር ብቻ ሳይሆን ኢኮኖሚዋን ከሌቦች ስንታደግ ነው። እስካሁን ከሰሜኑ ጦርነት ጋር ተያይዞ ሁላችንም በአገር ህልውና ጉዳይ ላይ ተጠምደን ስንቆይ ሌቦቹ ደግሞ ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም የኢትዮጵያ ገጸ-በረከቶች በመዝረፍ ላይ ተጠምደው ነበር። ስለዚህ አሁን ላይ አንጻራዊ የሚባል ሰላም በመስፈኑ ትኩረታችን እነዚህን ሌቦች በማጋለጥና በህግ ተጠያቂ ማድረጉ ላይ ሊሆን ይገባል።

በአጠቃላይ ሙስና እንደፓርቲም የምንታገለው ጉዳይ ነው። መንግስት ሌቦቹን ለህግ አጋልጦ የመስጠቱን ኃላፊነት አጠናክሮ እንዲሄድ እንፈልጋለን። እስካሁን ከታች ያሉትን ሌቦች የማጋለጥ ነገር አይተናል፤ ግን ደግሞ በከፍተኛ የመንግስታዊ ኃላፊነት ላይ ተቀመጠው ሰንሰለት ዘርግተው አገር እየመዘበሩ ያሉትንም ላይ እርምጃ ሊወሰድ ይገባል። ይህንን ማድረግ ከቻለ ህዝቡ ራሱ ከእሱ ጎን ይሰለፋል፤ ያለፍርሃትም ያጋልጣል። ይህንን ማድረግ ካልተቻለ ግን ራሱ መንግስትንም አደጋ ውስጥ ነው የሚጥሉት። ከኢህአዴግ ጊዜ ጀምሮ አሁንም ጃኬታቸውን ቀይረው የመጡ ሌቦች አሉ። እነዚህ ደግሞ ተራ ሙሰኞች አይደሉም፤ አሁን ኢትዮጵያ ላለችበት የኢኮኖሚ ቀውስ የዳረጉ ናቸው።

አሁንም ሰንሰለታቸው አልተበጠሰም፤ እንደልባቸው እየፈነጩ ነው ያሉት። ኢትዮጵያ እንዲህ በውጭ ምንዛሬ እጥረት እየተፈተነች ባለችበት ጊዜ እነሱ ግን ምንዛሬውን እንዳሻቸው እያንቀሳቀሱ ነው ያሉት። በህሊናቢስነት ኢኮኖሚውን የሚዘውሩ ኃይሎች አሉ። ከላይ ጀምሮ በደህንነት መዋቅር ውስጥ ሁሉ ገብተው በሰፊው እየሰሩ ያሉ ሌቦችንም ያለአንዳች መከላከል ለህግ አሳልፈን ልንሰጣቸው ይገባል። መፍትሔው ህዝቡና መንግስት እጅ ላይ ነው ያለው። እኛም ካለስስት ለማገዝ ዝግጁ ነን።

**አዲስ ዘመን፡- ለሰጡን ሰፊ ማብራሪያ በአንባቢዎችና በዝግጅት ክፍሉ ስም ከልብ አመሰግናለሁ።**

**መጋቢ ብሉይ አብርሃም፡-** እኔም እድሉን ስለሰጣችሁኝ አመሰግናለሁ።

# ማህደረ ጤና

# የህክምና አገልግሎቱን ከፈተና ወደ ተስፋ የማሻገር ትልም

**እፀገነት አክሊሉ**

«...አስናቀች አለሙ እባላለሁ። የመጣሁት ከሚዛን ቴፒ ነው። ሕመሜ የደም ካንሰር ነው። ሕክምናው በአንድ ወይንም በሁለት ቀን የሚቋጭ አይደለም። ሁልጊዜም ክትትል ይፈልጋል። ስለዚህ እኔ አልጋ መያዝ የማልችል አቅመ ደካማ ስለሆንኩ እዚያው ጥቁር አንበሳ ሆስፒታል አግዳሚ ወንበሮች ላይ ተኝቼ አድር ነበር። የብርዱ ነገር አይወራም። በዚህ ሁኔታ ከበሽታው በላይ በሁኔታው ስሰቃይ ቆየሁ። ... በፊት በፊት መድህኒቱ ለሶስት ወር ስለሚሰጠኝ የሶስት ወሩን ይዤ ወደ አገሬ እሄድ ነበር። አሁን ግን እጥረት አለ ተብሎ መድህኒት የሚሰጠኝ የአስራ አምስት ቀን ነው። የትራንስፖርቱ አልጋና ምግብ ሳይጨምር አንድ ሺህ አምስት መቶ ብር ነው። ደርሶ መልሱ ሶስት ሺህ ብር ይፈልጋል። በየአስራ አምስት ቀኑ ይህ ገንዘብ ከየት ይመጣል? ይህ ሕመም ከጀመረኝ አስር ዓመት ሆነው።

በፊት ልጆቼንም ቤቴንም የምደግፈው ጠጅ እየነገድኩ ነበር። አሁን ካንሰር ከያዘኝ ጀምሮ ይሄው አስር ዓመት ሆነኝ፤ ምንም ሰርቼ አላውቅም። ልጆቼን እንደእናትነቴ ከዳር ለማድረስ አልቻልኩም። አባታቸው ብቻውን እየተንገላታ ነው። እኔ እስከአሁን እየታመምኩ ነው። በእርግጥ አብረውኝ የሚታከሙ እየሞቱ ነው...... የእኔን መጨረሻ አላውቅም....» ይላሉ በአንድ ወቅት ለአዲስ አድማስ ጋዜጣ በህክምና አገልግሎቱ ምክንያት እየደረሰባቸው ያለውን እንግልት የተናገሩ እናት ።

የወይዘሮዋ ታሪክ በህክምናው ዘርፍ ያለው የአገልግሎት አሰጣጥ የደረሰበትን አስከፊነት የሚያሳይ ነው። በአገልግሎቱ ውስንነት የተነሳ ፈውስን ፈልገው የሚመጡ ህሙማን ግን በሚፈልጉት ልክ አገልግሎቱን አግኝተው አይሄዱም። ምክንያቱም የሕዝብ ቁጥሩና መሰረተ ልማቱ እንዲሁም የአገልግሎት አይነቱና መድህኒቱ ብዙ ችግር አለበት።

አብዛኞቹ ሪፈራል ተብለው የሚጠሩት የመንግስት ትልልቅ ሆስፒታሎችም ሲታዩ ብዙ ነገር የሚጎላቸው ናቸው። ለምሳሌ በቂ ባለሙያም ላይኖራቸው ይችላል። በተለይ አሁን እየጨመረ ያለውን የሕዝብ ቁጥር የሚመጥን ቦታና ባለሙያ ማግኘት ፈተና ነው። በዚህም ሰዎች በሄዱበት ፍጥነት አገልግሎትን ሳያገኙ ቀርተው ይሞታሉ፤ አለያም የአካል ጉዳተኛ ይሆናሉ። የአገልግሎት አሰጣጥና የህብረተሰብ አለመመጣጠንም ተኝተው መታከም ያለባቸውን ሰዎች በየኮሪደሩ እንዲወድቁ ያደርጋቸዋል። ለዚህም እንደአገር የተለያዩ መፍትሄዎች በመስጠት ላይ ነው። ከእነዚህም ውስጥ አንዱ ሆስፒታሎችን ለሕዝብ አገልግሎት ክፍት ማድረግ ሲሆን፤ የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ይህንን መሰረት አድርገው ከተቋቋሙት መካከል ይጠቀሳል።

አመሰራረቱ በዝቅተኛ የኑሮ ደረጃ ላይ ለሚገኙ የኅብረተሰብ ክፍሎች በነፃ እንዲሁም በዝቅተኛ ዋጋ የሕክምና አገልግሎት ለመስጠት ነው። በዚህም በአዲስ ከተማ ክፍለ ከተማ በሚገኘው የአሁኑ የአውቶብስ ተራ (መናኸሪያ) ቅጥር ግቢ ውስጥ በ1939 ዓ.ም ተጀምሮ ይህንን አገልግሎቱን ለ24 ዓመታት ሲሰጥ ቆይቷል። ከዚያም አገልግሎቱ ዘመናዊ እንዲሆን በመወሰኑ በጉለሌ ክፍለ ከተማ ማለትም አሁን ባለበት ቦታ ላይ ባለ አራት ወለል ሕንፃ ተገንብቶለት በ1963 ዓ.ም ሥራውን እንዲጀምር ሆነ።

በአሁኑ ወቅትም ቅዱስ ጳውሎስ ሚሊኒየም ሜዲካል ኮሌጅ በሚል ስሙን ቀይሮ ከአንገት በላይ ህክምና ጨምሮ የውስጥ ደዌ ፤ የማህጸንና ጽንስ፣ የህጻናት ህክምና፣ የአስክሬን ምርመራ ህክምና፣ የህብለ ሰረሰር ቀዶ ህክምና፣ የቃጠሎ አደጋ ህክምና፣ የኩላሊት ህክምና፣ የፊኛና የሽንት ትቦ መስመር ህክምና እና ያለ ቀዶ ህክምና ጠጠሮችን የሚያስወግዱ ህክምናዎችን በመስጠት ላይ ይገኛል። ከዚህ ሁሉ በላይ ደግሞ በቅርብ ዓመታት ውስጥ የጀመረው የፊርቲሊቲና የስነ ተዋልዶ ህክምና ማዕከል ሆስፒታሉን አንድ እርምጃ ከፍ ካደረጉለት ተግባራት የሚጠቀሱ ናቸው።




በሌላ በኩልም የህክምና ኮሌጁ በ104 ሚሊዮን ብር ወጪ የአፍንጫ፣ የጆሮ፣ የጉሮሮ እና ተመሳሳይ ከአንገት በላይ ህክምናዎች ዘመኑ በደረሰበት የቴክኖሎጂ ደረጃ መስጠት የሚያስችሉ ዘመናዊ መሳሪያዎችን ከውጭ አገራት በማስገባት አገልግሎት የሚሰጥ ሆኗል። ይህንን አገልግሎት መጀመሩ ደግሞ ታማሚዎችን ከማገልገል ባሻገር ከአንገት በላይ ህክምና ድህረ ምረቃ መርሃ ግብር ትምህርታቸውን የሚከታተሉ ሰልጣኞች ከዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች ጋር በማስተዋወቅና የሥራ ላይ ልምምድን በስፋት እንዲያገኙ ያስችላቸዋል።

እነዚህንና መሰል መልካም ሥራዎችን በህክምናው መስክ ሲያከናውን አለም የደረሰበት ደረጃ ላይ ሊያደርሱን የሚችሉ በርካታ ልምዶችንም ለአገር ያመጣል። በእርግጥ ሥራዎቹ በዚህ ደረጃ ቢሰፉም በቦታ ጥበት ምክንያት ታካሚዎች በቀልጣፋና በምቹ ሁኔታ ማገልገል ተስኖት ቆይቷል። ስለዚህም ይህንን ችግር ለመፍታት አሁን ላይ ሆስፒታሉ በሁለት ቢሊየን 768 ሚሊየን 21 ሺህ ብር ጠቅላላ በጀት ከሦስት ኮንትራክተሮች ጋር በመፈራረም የሚያስገነባው (2B+G+8) የካንሰር ህክምና ማዕከል እና (B+G+8) የልብ ህክምና ማዕከል በአገልግሎቱ ላይ የሚታየውን የተደራሽነት ችግር በማቅለል የማይተካ ሚና ይኖረዋል። ታካሚዎች በምቹና ቀልጣፋ ሁኔታ እንዲገለገሉም ያደርጋል።

ግንባታው አሁን ላይ የሲቪል ስራ ፊዚካል አፈፃፀም 80 በመቶ መድረሱን ደግሞ የሆስፒታሉ የምህንድስናና ግንባታ ዳይሬክተር ኢንጂነር አማኑኤል ሕይወት ይገልጻሉ። ሆስፒታሉ ተጨማሪ የድንገተኛ አደጋ ህክምና ማዕከል ፕሮጀክት በአቤት ሆስፒታል ለመገንባትም 8ሺ600 ካሬ ቦታ ተረክቦ በዝግጅት ላይ ስለመሆኑም ያነሳሉ።

ሆስፒታሉ እያስገነባ የሚገኘው ከ1ሺህ በላይ አልጋ ያለው ብሔራዊ የካንሰር፤ የልብ እና ከሆድ ዕቃ ጋር ተያያዥ (የአንጀት፣ ጨጓራ፣ ጉበት) ህክምና ማዕከል ሲሆን፤ በ6ሺህ 800 ካሬ በላይ ያረፈው ብሔራዊ የካንሰር ህክምና ማዕከል በየክልሉ ከሚገኙት የካንሰር ማዕከላት የገዘፈና ለጨረር ህክምና የሚሆን 5 ባንከር ያለው ነው። በጨረር ህክምና ለካንሰር ህክምና አገልግሎት የሚውለው ባንከር ጣሪያ ማልበስ ብቻ ነው የቀረው። የካንሰር ህክምና ማዕከሉ ከ337 በላይ አልጋ ያለው ሲሆን፤ ከኖርማል ራድዮሎጂ ዩኒት፣ ኤም አርአይ፣ ሲቲ ስካን በተጨማሪም ኒውክላር ሜዲሰን ያለው መሆኑን አብራርተዋል። በሌላ በኩልም በመደበኛ ኢሜጂንግ የማይታዩ የካንሰር ዓይነቶችን በግልጽ ለማየት የሚያስችሉ በኮንክሪት የተሰሩና የተለየ ቦታ የሚቀመጡ ቴክኖሎጂዎች መካተታቸውም ታውቋል።

እንደ ኢንጂነር አማኑኤል ማብራሪያ፤ በ1ሺህ 900 ካሬ ላይ ያረፈው ባለ ስምንት ወለል ህንጻ የልብ ህክምና ማዕከል ፕሮጀክትም እራሱን ችሎ ከ316 በላይ አልጋ፤ 15 አይሲዩ እና 15 ሲሲዩ አልጋዎች እንዲሁም አራት የቀዶ ጥገና፤ ሁለት ካትላብ እና 10 የማገገሚያ ክፍሎች አሉት። ምድር ቤት ( ቤዝመንት) እና ባለ ስምንት ወለል ያለው ህንጻም ይገኝበታል።

በ1ሺህ 400 ካሬ ላይ ያረፈውና የአንጀት፣ ጨጓራ፣ ጉበትና ተያያዥ ህክምና ማዕከል የሆነው ደግሞ 184 አልጋዎች፣ ስድስት የጨጓራ ምርመራ (ኢንዶስኮፒ) ክፍል አለው። ይህም በተመሳሳይ ምድር ቤት (ቤዝመንት) እና ስምንት ወለል የያዘ ህንጻ ነው። ሙሉ ከአንገት በላይ ህክምና ከቦታ ችግር ጋር ተያይዞ ራሱን ችሎ ሊገነባ ባለመቻሉም 115 አልጋዎች ያሉት የራሱ የቀዶ ጥገና ክፍል (ኦፕሬሽን ሩም) ያለው፣ በአንዱ ብሎክ ተተክቷልም ብለዋል ኢንጅነሩ።

ፕሮጀክቱ ከሦስት ኮንትራክተሮች ጋር በተደረገ ስምምነት እየተገነባ የሚገኝ ሲሆን፤ ከዋና ሲቪል ኮንትራክተሩ ጋር በአንድ ቢሊየን 689 ሚሊየን በላይ ገንዘብ ተፈራርሞ የተጀመረ ነው። ከአለፈው ሰኔ ወር ጀምሮ ደግሞ የአንድ ዓመት ኮንትራት ከባማኮን ኢንጂነሪንግ ጋር በመፈራረም ከካንሰር ህክምና ጋር የተያያዙ ዘመናዊ የኔትወርክ ዝርጋታ፣ በኔትወርክ የተደገፈ የህንፃ ማኔጅመንት ሲስተም፣ ነርስ ኮል ሲስተም፣ አጠቃላይ የኤሌክትሪክ ሥራዎችን እና የማጠናቀቂያ ሥራዎችን ጨምሮ በ789 ሚሊየን ብር እየሰራ ይገኛል።

ከሐምሌ 2013 እስከ ሚያዝያ 2015 ዓ.ም ለማጠናቀቅ 289 ሚሊየን 773 ሺህ ብር የፈረመው ደግሞ ኪቢሽ ኮንስትራክሽን ሲሆን፤ የኤሌክትሮ መካኒካል ሥራውን እየሰራ ይገኛል። ፕሮጀክቱ ከዋጋ ንረት አንጻር የሲሚንቶና የብረት ችግር በመጠኑ ተግዳሮት ሆኖበታል። በተለይም ጨረር ለመከላከል የሚሰራው ባንከር ግንባታ ጣራ የማልበስ ሥራ ተቆራርጦ የማይሞላና እስከ 5ሺህ ኩንታል ሲሚንቶ የሚፈጅ ኮንክሪት በአንድ ጊዜ መሙላት ስለሚያስፈልገው ለዚህ የሚሆን ግብዓት ያስፈልጋል። በዋናነት ግን የመጨረሻ ሥራዎችን ለማጠናቀቅ ከ700 ሚሊየን ብር በላይ የሚገመቱ ዕቃዎች ሙሉ በሙሉ ከውጭ የሚገቡ በመሆናቸው በጤና ሚኒስቴር በኩል ከሶስት ወር በፊት 15 ሚሊየን ዶላር ለብሔራዊ ባንክ የድጋፍ ደብዳቤ ተጽፎ በመጠባበቅ ላይ እንደሆኑም አስረድተዋል ኢንጅነሩ።

በሌላ በኩልም በአሁኑ ወቅት የድንገተኛ አደጋ ህክምና ማዕከል የቅዱስ ጳውሎስ ሆስፒታል ሜዲካል ኮሌጅ አካል በሆነው አቤት ሆስፒታል በአነስተኛ ህንጻ በኪራይ ትልቅ አገልግሎት እየተሰጠ የሚገኝ ሲሆን፤ በቀጣይ ግን 8ሺ 600 ካሬ ከጉለሌ ክፍለ ከተማ መሬት በመረከብ የድንገተኛ አደጋዎች ህክምና ማዕከል ሜጋ ፕሮጀክት ግንባታ ዲዛይን ተጠናቆ ከሶስት ወር በኋላ ግንባታው የሚጀመር ይሆናልም ብለውናል።

ዛሬ ላይ የደረስንበት የህዝብ ቁጥር በተገቢው ሁኔታ ለማገልገል እንደዚህ አይነት ግንባታዎች እጅግ በጣም ወሳኝ ናቸው፡፡ ነገር ግን ከግንባታው ባሻገር የባለሙያው ሙያዊ ብቃት ላይ መሰል ሥራዎች መስራትም ያስፈልጋል። እናም ሆስፒታሉ ይህንን በማድረግ በኩል ትልቅ አቅም ያሉት ኢንጅነሩ፤ ዓለም የደረሰበትን ዘመናዊ ቴክኖሎጂ ታሳቢ ያደረጉ ዘመናዊ የህክምና መሳሪያዎችና ግብዓቶች ላይ ትኩረት አድርጎ መስራትም እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ አስገንዝበዋል።

# ነፃ ሃሳብ

የሥነ ጽሑፍና የኮሙዩኒኬሽን ባለሙያ ናቸው። የኢትዮጵያ ደራስያን ማኅበርን ለዘጠኝ ዓመታት ያህል በፕሬዚዳንትነት መርተዋል። ከ1977 ዓ.ም ጀምሮ በአዲስ ዘመንና የዛሬይቱ ኢትዮጵያ ጋዜጣ፤ በሀገር ውስጥና በውጭ ሀገራት ታትመው በሚሠራጩ የተለያዩ የኅትመት ውጤቶች ላይ (ዳግላስ ጴጥሮስ) በሚል የብዕር ስሙ በርካታ ጽሑፎችን አስነብበውናል። በግላቸው 12፣ ከሌሎች ጸሐፍት ጋር በርካታ መጻሕፍትን ለአንባብያን አቅርበዋል።

## ታሪክ፣ ትዝታና ነባራዊ እውነታ



(በጌታቸው በለጠ /ዳግላስ ጴጥሮስ)
gechoseni@gmail.com

### አስማሚ ትርጉም፤

**ትዝታ፡-** በስሜት የሸመጥ ግልቢያ ነበርን ማስታወስ፣ ትናንትን እያሰቡ መብከንከን፣ ቀድሞ የተፈጸመን ድርጊት እያስታወሱ በስሜት ሃሴት ማድረግ፣ መባባት ወይንም ሆድ መባስ ወዘተ. ይሉት ብጤ የስሜት ቁርኝት ነው። "ትዝታ ነው የሚርበን፤ ላናገኘው ላያጠግበን" እንደተባለው መሆኑ ነው። ታዋቂው ነፍስ ሄር ፖለቲከኛ አሰፋ ጫቦ በግለ ታሪክ መጽሐፋቸው ውስጥ "ለመሆኑ ትዝታ ምንድን ነው?" ብለው ከጠየቁ በኋላ መልሱን እንዲህ በማለት ከማይመለሱ ጥያቄዎች ጋር በመሸረብ ለማብራራት ሞክረዋል።

"ትዝታ ዘፈን ነው? እንጉርጉሮ? ወይንስ ማላዘን?... ትዝታ ልጓም የለውምና እንዳሻው ወደ ላይ፣ ወደ ታች፣ ወደ ውስጥ፣ ወደ ውጭ፣ ወደ ፊት፣ ወደ ኋላ ወደሚታይ፣ ወይ ሊታይ ወደማይችል፣ ይሄዳል፣ ይኳዛል፣ ይተናል፣ ይበናል፣ ይመላለሳል፣ ይመለሳልም። ‹ማን አለኝ ከልካይ!› እንዲሉ መሆኑ ነው።" ብለዋል። ስንቋጨው፡- ትዝታ መጥቶ ሂያጅ ተመላላሽ የስሜት መንገድ ነው።

**ታሪክ፡-** በቃል፣ በጽሑፍ ወይንም በተለያዩ የማስታወሻ ምልክቶች ትናንትን የሚተርክ፣ የነበር ኩነቶችንና ክስተቶችን የሚያመለክትንና የሚያጠና ንብርብር ማስረጃ ነው። ታሪክ በባህርይው ባለፉ ጉዳዮች ላይ ትኩረት ስለሚያደርግ አንዳንዴ የተፈጸመው እውነታ ከባህርይውና ከድርጊቱ እየተለጠጠ መኀላመስ፣ አንዳንዴም መበረዝ፣ መከለስ፣ መቅጠንና መድበስበስም ሊስተዋልበት ይችላል።

የሰው ልጅ ከሌሎች ፍጡራን የሚለየው መሠረታዊ የህልውናው ጉዳዮች (መብሉ፣ መጠጡ፣ አልባሳቱና መጠለያዎቹ) ስለተሟሉለት ብቻም ሳይሆን ትዝታና ታሪክም ዋነኛ ጉዳዮቹ ናቸው። ትዝታና ታሪክ ባይኖር የሰው ልጅ ዜና መዋዕል ምን ሊመስል እንደሚችል መገመቱ አይከብድም። በአጭሩ "ተኖረና ተሞተ" ብጤ ሳይሆን አይቀርም።

**ነባራዊ እውነታ፡-** ያለፉትን ትዝታና ታሪኮች ከዛሬ እውነታዎች ጋር እያዛመዱ መኖር ማለት ነው። "ነበር ባያኮራም" - ለዛሬ መሠረቱ ነውና በቅራኔም ሆነ በስምምነት አብሮ መኖር ግድ ይሏል። ትዝታና ታሪክ ከሰው ልጅ ነባቢት ነፍስ ጋር የተቆራኙ መሆኑም በሚገባ ይታወቃል።

### አገሬ እያስፈተችበት ያለው መራራ ጉዞ፤

አብዛኛው አገራዊ ታሪካችን በጦርነትና በድል ድርና ማግ እና በትዝታ የተሸመነ መሆኑ ተደጋግሞ ተብሏል። መቼም የተመዘዘ ሰይፍ ለበጎነት አይሰነዘርምና፤ አንዱን ወገን በለስ ሲቀናው ሌላኛው ደመኛ መሸነፉ፣ የተሸነፈው ሲበረታም የአሸናፊው ጉልበት ዝሎ መድከሙ የታወቀ ነው። ይህንን መሰሉን ወታደራዊ ስልትና ታክቲክ አፍታቶ ለመዘርዘር ሙያዊ ብቃታችን (Mandate) ስለማይፈቅድልን የማይነካውን ጉዳይ አንዳፈርም።

መሠረታዊው እውነታ ከላይ የጠቀስነውን ይምሰል እንጂ የሩቆቹም ሆኑ የቅርቦቹ ታሪካዊ ክስተቶችና አገራዊ ፈተናዎች ጥለውብን ያለፉት [በአብዛኛው] መራራ ጠባሳዎችና ክፉ ትዝታዎች ዛሬም ድረስ እንዳስነቡን፣ ጥቁር ማቅ አስለብሰው እንዳስቆዘሙንና ቅስማችንን ሰብረው እንዳስጎነበሱን የሚዘነጋ አይደለም። ይዘንጋ ቢባልስ መች ይሞከራል?

አገራዊ ታሪኮቻችንን ባልተዛቡ ማጣቀሻዎች በመዘከርና በትዝታ መስታወት መለስ ቀለስ በማለት ትናንትን ለመቃኘት መሞከሩ ተገቢም፣ አግባብም ነው የምንለው ያለ ብልሃት አይደለም። "ምክንያቱስ?" ቢባል ከዛሬ እውነታችን ጋር "ነበርን" ጎን ለጎን እያስታወሱ በነፃው ዐምዳችን ላይ ነፃ ሃሳባችንን መሰንዘሩ "ኢትዮጵያ ሆይ!" ለሚለው የውስጥ ጩኸታችን ማስታገሻ ስለሚሆን ብቻም ሳይሆን ትውልድ የሚማረውም በዚሁ መልክ ስለሆነ ጭምር ነው።

ታሪካችን የጦርነት ዐውድማ የበዛበት ነበር የምንለው በቂ ምክንያት ስላለን ነው። ኢትዮጵያ በታሪኳ ውስጥ "ዘገር ነቅንቃ፣ ሠራዊት አሰልፋና ድንበር ጥሳ" የሌላውን አገር ሉዓላዊነት ለመዳፈር ከቶውንም ቢሆን "ጀብደኝነት ተናንቋት"፣ "ወደፊት በሉልኝ ይለይልኝ!" ብላ ፎክራም ሆነ ተግብራ አታውቅም።

በአንጻሩ ግን የሩቅና የቅርብ ተስፋፊና እብሪተኛ ጠላቶቿ ለአንድም ዘመን ዐይናቸውን ከእርሷ ላይ ነቅለው አያውቁም። ዕይታቸውም በርቀትና በቅርበት ከመመልከት እያለፈ ምን ያህል ጊዜ እንደዘመቱባት በታሪካችን ሰነዶች ውስጥ በሚገባ ታጭቆ ተሰንዷል። "የዱባ ጥጋብ ያለ ስንቅ ያዘምታል" እንዲሉ፤ እየተመሙ የወረሯት ጠላቶቿ በሙሉ አፍረው የተመለሱት እጃቸውን አፋቸው ላይ ጭነውና በእፍረት ክንብንብ ተሸፍነው ስለመሆኑም አንጸባራቂውን የታሪካችንን የዘመናት ፈለግ ቆም ብለን በመመርመር ከጫፍ እስከ መዳረሻው መተረክ እንችላለን።

"ላም እሳት ወለደች እንዳትልሰው ፈጀት እንዳትተወው ልጅ ሆነባት" እንዲሉም የውጭ ባዕዳን ተስፋፊና ወራሪ ጠላቶቿ ብቻም ሳይሆኑ "የቤት ውላጅ ሞገደኛና ምናምንቴ" ልጆቿ ተብዬዎችም ሳይቀሩ በጓዳዋ ውስጥ እያንጎዳጎዱ እንደምን ሰላም ሲነሷት እንደኖሩ በታሪክና በትዝታ ብቻ ሳይሆን ነባራዊው የዛሬ እውነታ ጭምር ጥሩ ማሳያ ሊሆን ይችላል።

ኢትዮጵያ የግዛት ሉዓላዊነቷን ለማስከበር ከዋለችባቸው የጦርነት ዐውድማዎችና ከድል አድራጊነቷ መለስ ከባዕዳን ጋር "አትድረሱብኝ አልደርስባችሁም" በማለት በሰላም ቋንቋ ለመነጋገር ካደረገችው ጥረት በላቀ ሁኔታ ለሰላም ድርድርና ስምምነት ወንበር ስባ በመቀመጥ "ጥያቄያቸውን ለማድመጥና መፍትሔ ለመስጠት" ስትተጋ የኖረችው የራሴ ከምትላቸው "የቤት ውላጅ ልጆች" ጋር ነበር/ነውም።

ታሪክንንም ሆነ ትዝታችንን እየጠቃቀስን ጥቂት ዳሰሳ ለማድረግ ወደ ኋለኛው ዘመን ጥቂት አናፈግፍግ። የኢትዮጵያ ዘመነ መሣፍንት እየተባለ በአብዛኞቹ የታሪክ ሰነዶች የሚጠቀሰው ከ18ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ እስከ 19ኛው ክፍለ ዘመን አጋማሽ ያሉት ዓመታት ናቸው። ወቅቱ አንዱ ብሔር ከአንደኛው ጋር፣ አንዱ መስፍን ከሌላኛው ጋር የሚቆራቆሱበት፣ የሚተነኳኮሱበትና አልፎም ተርፎ በጦርነት እስከ መፋለም የደረሱበት ወቅት ነበር።

አብዛኞቹ የታሪክ ምሁራን እንደሚስማሙት "የዘመነ መሣፍንት የታሪክ ጅማሬና መነሻ ራስ ሚካኤል ሥዑል ዳግማዊ ዓፄ ኢዮአስን ሚያዝያ ወር 1761 ዓ.ም ያስገደሉበት ቀን ሲሆን መጠናቀቂያውም ዳግማዊ ዓፄ ቴዎድሮስ የካቲት ወር 1847 ዓ.ም ሥልጣን ላይ ከወጡ በኋላ ነበር" እየተባለ ይታመናል። የዘመን አቆጣጠሩ አልፎ አልፎ የቀን፣ የወርና የዓመት መፋለስ ስለሚስተዋልበት በዋናነት ታሪካዊ ኩነቱ ላይ ማተኮሩ ይበጃል።

ይህ "የቤት ልጆች" እኔ እበልጥ፤ እኔ እበልጥ ፉክክር የተስተዋለበት ታሪካችን መልኩና አተገባበሩ ይለያይ ካልሆነ በስተቀር ምንም የዓላማ ለውጥ ሳይኖረው ዛሬም እየተሳበ እኛ ዘመን ስለመድረሱ መጠራጠር አይቻልም። የሩቁን ታሪካችንን እዚያው በርቀት እንዲሰነብት ትተነው ወደ ቅርቦቹ ታሪካችንና ትዝታችን መመለሱ ስለሚሻል የመንደርደሪያ ሃሳባችንን የጋዜጣው የዐምድ ስፋት ስለማይፈቅድልን አልፎ አልፎ ምሳሌዎችን ለመጠቃቀስ እንሞክር።

በግርማዊ ቀዳማዊ ኃይለ ሥላሴ ዘመነ መንግሥት እ.ኤ.አ በ1960 ዓ.ም ግብጽ ውስጥ ተመሥርቶ ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለመገንጠል (በወቅቱ ኤርትራ አንዷ የኢትዮጵያ ጠቅላይ ግዛት መሆኗ ይታወሳል) ይንቀሳቀስ ከነበረው ቡድን ጋር እ.ኤ.አ በ1972 በንጉሠ ነገሥቱ ፈቃድ የሰላም ንግግር ለማድረግ ተሞክሮ እንደነበር የመረጃና ደኅንነት ከፍተኛ ባለሙያ የነበሩት በላይ ገብረ ጻድቅ በቅርቡ ባሳተሙት መጽሐፍ ውስጥ ዝርዝሩን አስፍረዋል። (የመረጃና ደኅንነት ሙያ እና የኢትዮጵያ ገጽታው - 2014 ዓ.ም)።

> ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአገሪቱ ላይ የዘነበው መከራና መቅሰፍት ሲታሰብ የደረሰው የሕይወት፣ የአካል፣ የሥነ ልቦና ቀውሱና የቁስ ውድመቱ በኢትዮጵያ ምድር የእስካሁኑ ታሪክ ተፈጽሞ ስለመመዝገቡ እርግጠኛ ስለመሆን ጥልቅ ፍተሻ ማድረግን ይጠይቃል

የወታደራዊው ደርግ ሊቀመንበርና በኋላም የኢሕዴሪ ፕሬዚዳንት የነበሩት ኮሎኔል መንግሥቱ ኃይለ ማርያም በጻፉት ቅጽ አንድ "ትግላችን" መጽሐፋቸው ውስጥ በንጉሱ ዘመን ከኤርትራ አማፂያን ጋር የተጀመረው የሰላም ንግግር በእርሳቸውም ዘመነ ሥልጣን ተጠናክሮ መቀጠሉን እንዲህ በማለት ገልጸዋል።

"የኤርትራን ክፍለ አገር ከኢትዮጵያ አስተዳደር ለመነጠል ወይንም ለመገንጠል መንስዔ ስለሆኑት ምክንያቶች፤ ችግሩ ከተከሰተበት ጊዜ ጀምሮ በገንጣዮቹና በኢትዮጵያ አንድነት ኃይሎች መካከል...በቅድመ አብዮት ኢትዮጵያ ለ13 ዓመታት [እና ከዚያም በኋላ] በኢትዮጵያውያን ወንድማማቾች መካከል የሚፈሰውን ደም በአስቸኳይ ለማቆምና ችግሩን በጦር ሜዳ ሳይሆን በጠረጴዛ ዙሪያ በሰላም ለመፍታት በአብዮቱ የመጀመሪያ ዓመታት...እስኪሰለቹን ድረስ ደግመን ደጋግመን ጠይቀናል" (ገጽ 316)።

ችግሩ ከጊዜ ወደ ጊዜ እየተባባሰ መሄዱን ያስተዋሉት የውጭ አገር መንግሥታትም ልክ ዛሬ እየተደረገ እንዳለው በአሜሪካው ፕሬዚዳንት በሚ/ር ጂሚ ካርተርና በወቅቱ የሶቪዬት መሪ በፕሬዚዳንት ሚኻኤል ጎርባቾቭ አማካይነት በኤርትራ አማጽያንና በኢትዮጵያ መንግሥት መካከል ዕርቀ ሰላም እንዲወርድ ሙከራ መደረጉን ሌ/ጄ አዲስ ተድላ ባሳተሙት የግለ ታሪክ መጽሐፋቸው ውስጥ ሂደቱን በዝርዝር ተርከዋል (በገጠመኞች የታጀበ የሕይወት ጉዞ፤ ገጽ 492 - 495)።

ኢህአዴግን ለሥልጣን ያበቃው በሕዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይ (ሕወሓት)፣ በኦሮሞ ነፃነት ግንባር (ኦነግ)፣ እና በኤርትራ ሕዝብ ነፃ አውጭ ግንባር (ህግሓኤ) መካከል በግንቦት 1983 ተደጋግሞ ተሞክሮ የከሸፈው የለንደኑ የሰላም ውይይትም በታሪካችን ውስጥ በፀፀትና በቁጭት ሲተረክ የሚኖር የትዝታችን አንዱ ገጽታ ነው።

"የከፉ ዘመን ስህተት ፈጥኖ ከውል አይደርስ" እንዲሉ፤ ኢትዮጵያ የራሴ በምትላቸው ሲፈጸምባት የኖረውና እየተፈጸመባት ያለው አበሳ ገና ተዝቆ ያለቀ አይመስልም። የግዛት አንድነቴን አላስነካም በማለት ከውጭ ወራሪዎች ጋር ስትፋለም ዘመናት መግፋቷ ያነሰ ይመስል፤ በውስጥ መከራዋ እየተናጠችም ቢሆን አንገቷን ሳትደፋ መኖሯ አንድም የፈጣሪዋ ልዩ እርዳታና ጥበቃ ስላልተለያት ሲሆን ሁለትም አናብስት የመከላከያ ጀግኖቿ፣ የሕዝባዊ ሠራዊቶቿና የጸጥታ ኃይሏ እየከፈሉ ባለው የደምና የመስዋዕትነት ውጤት መሆኑ ለአፍታም ቢሆን ሊዘነጋ አይገባም። የሕዝቧ የደጀንነት ሚናና ተግባርም እጅግ ደምቆ ማሸብረቁን የምንገልጸው የትናንት ወዲያውን ታሪክ በማስታወስ ብቻም ሳይሆን የበቀደሙ ትዝታችንም ለምስክርነት የሚደበዝዝ አይደለም።

በቅርቡ የኢትዮጵያ መንግሥት ከሕወሓት ጋር በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ ከተማና በኬኒያ ናይሮቢ ያደረጋቸው የሰላም ንግግሮችና ስምምነት ያለፉት ተከታታይ ታሪኮቻችን ዛሬም እልባት ያለማግኘታቸውን የሚያመለክት ብቻ ሳይሆን የአገሬ "የሰላም ጥማት" ገና እንዳልረካ ጭምር የሚያሳይና የልብ ስፋቷንም መጠን በግልጽ የሚያረጋግጥላት ጽኑ ማስረጃዋ ነው።

በመነሻችን ላይ የተጠቀምንባቸውን የመንደርደሪያ ሃሳቦች እንደገና አስታወሰን ርዕሰ ጉዳያችንን ለመደምደም እንሞክር። አገር በባዕድ ወራሪ ሲደፈር መደበኛ የአገር ሠራዊት ብቻ ሳይሆን ሕዝቡ ራሱ በነቂስ ሆ! ብሎ በመዝመት በደምና በመስዋዕትነት ለሉዓላዊነታችን ክብር ዘብ በመቆም "አገሬን አላስደፍርም" ብሎ በነፍስና በስጋ መወራረድ የተለመደና የሚቀጥል የዜግነት አደራና ግዴታ ነው።

እንዲህ እንደዛሬው የመሰለ መከራ ሲገጥመንና መራር ትዝታውም ከልብ አልጠፋ ብሎ እየተፈታተነ ሲታገለን፤ በሰላምና በጥበብ ችግሮችን ተጋፍጦ ማሸነፍ ብልህነት ብቻም ሳይሆን "ላም እሳት ወለደች..." ብሂልን የሚያስታውስ ስለሆነ ጉዳትን ለሰላም መስዋዕት አድርጎ ማቅረብ ምን ያህል የልብ ስፋት እንደሚጠይቅ ለመረዳት የሚከብድ አይሆንም።

በተለይም ባለፉት ጥቂት ዓመታት በአገሪቱ ላይ የዘነበው መከራና መቅሰፍት ሲታሰብ የደረሰው የሕይወት፣ የአካል፣ የሥነ ልቦና ቀውሱና የቁስ ውድመቱ በኢትዮጵያ ምድር የእስካሁኑ ታሪክ ተፈጽሞ ስለመመዝገቡ እርግጠኛ ለመሆን ጥልቅ ፍተሻ ማድረግን ይጠይቃል። ቢሆንም ግን ለሰላም ሲባል የቆሰሉ እጆችንና ልብን ከፍቶ በከንቱ የሚፈስ የደም ምንጭን ለማድረቅ መወሰን መራራና የሚያንገሸግሽ ቢሆንም የነባር ታሪክሽ ወግ ነውና የእናትነት ግዴታሽን ጨክነሽ ለመወጣት ኢትዮጵያ ሆይ ጽናቱን ይስጥሽ።

**"ትዝታዬ ይረፍ፤ ታሪኬም ይተኛ፣**
**ካሰብኩት እስኪደርስ የሩቅ መንገደኛ።"**

አለች ይባላል፤ መከራዋ እንደ ዕንቆቅ መርሮባት ፈተናው ያንገዳገዳት ብሶተኛ እናት። ሰላም ይሁን።

# ተናጋሪው ዶሴ

# ‹‹ዶክተር›› ነኝ ባዩ ሀሰተኛ

አስመረት ብስራት

ወይዘሮ አምሳለ ተገኑ ወልዶ የመሳም ፀጋን ለመጎናፀፍ ቀናትን እየቆጠረች ነው። እርግዝናዋን ካወቀችበት ቀን አንስቶ  የመጨረሻው ቀን ልጇን የምትታቀፍበት ቀን እስኪደርስ ያሉትን ቀናት እያንዳንዱን የስሜቷን ልክ እየለየች በፍፁም የእናትነት ስሜት በጉጉትና በስጋት መካከል ሆና እዚህ ደርሳለች። ጠዋት ከመኝታዋ ስትነሳ ጀምሮ ባልተለመደ መልኩ ቁርጠት እያጣደፋት ነው። ግራ ሲገባት ጎረቤት ሄዳ ስታማክር ምጥ እንደሆነ ነግራው በአቅራቢያዋ  ወደሚገኝ የጤና ተቋም ወሰዷት።

ብዙም ምጥ ያልጠናባት ወይዘሮ አጋጊ ወንድ ልጇን ለመታቀፍ ከግማሽ ቀን በላይ ማማጥ አልተጠበቀባትም ነበር። ወንድ ልጅ ከነቃጭሉ ታቀፈች። በስስት የምታየው የበኩር ልጇ ፍፁም ጤነኛና ደስተኛ ነበር። አንድ ቀን ግን ህፃኑ ከባድ ትኩሳት አጋጠመው። ቀዝቃዛ ውሃ በፎጣ ብታደርግ፤ የትኩሳት መድሃኒት ብትሰጠው ለውጥ ማግኘት አልቻለችም። የስስት ልጇ ህመምን ማየት የከበዳት እናት ልጇ ፈጥኖ መፍትሄ ያገኝ ዘንድ ወደ ጤና ተቋም ይዛው በረረች።

## ያልታሰበው ክስተት

በአዊ ብሔረሰብ  ዞን የጃዊ ሆስፒታል ልጇን ይዛ የሄደችው እናት እርዳታን ጠይቃ ሊሰጣት ልጇን የተቀበላትን ሀኪም በተማፅኖ አይን እየተመለከተች “ ዶክተር እባክህ በፈጣሪ ይዤህለሁ ልጄን አድንልኝ  .....” እያለች በመማፀን ተከትላው ወደ ህክምና መስጫው ክፍል ገባች።

‹‹ዶክተር›› የተባለው ሰውም ልጁን በማዳመጫና በእጁ ሲነካካ ቆይቶ ‹‹ጉንፋን ነው ምንም አይለውም›› በማለት የትኩሳትና ለጉንፋን የሚሰጥ ሽሮፕ ሰጥቶ ወደ ቤቱ መለሰው። የሰባት ወሩ ህፃን ግን ከህመሙ ከመፈወስ ይልቅ እየደከመ ሄደ። መልሰው ወደ ጤና ተቋሙ ሲወስዱት የሳንባ ምች እንደሆነና ወደ የከፋ ደረጃ እንደተቀየረ ነግራው አልጋ አስያዙት። ቀድሞ የመረመረው ሀኪም ባለመኖሩ ተደውሎለት እንዲመጣ ተደረገ። ልጁ ተዳክሞ ሲያየው በድንጋጤ ይሆናል ያለውን መርፌ ለህፃኑ ይሰጠዋል። ተወዳጁ የአምሳለ ልጅ በዚህ አይነት ሁኔታ ህይወቱ አለፈ።

የስስት ልጇን ያለአግባብ የተነጠቀችው ሴትም ጉዳዩን ይዛ ህግ ዘንድ ቀረበች፡፡ ያን ጊዜ ዶክተር ነው የተባለው ጌትነት ወንድአወቅ ምርመራ እንዲደረግበት ታዞ ጉዳዩን ፖሊስ ያዘው። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ‹‹ዶክተሩ›› ከስራ ገበታው አልታገደም ነበር።

## ሴላኛው አሳዛኝ ክስተት

የግሌ ያለው በአዲስ ተስፋ ህይወትን ለመጀመር አንድ ብላ ስትነሳ ነገን በተስፋና በጉጉት የምትመለከት ፍልቅልቅ ወጣት ነች። የ25 ዓመት ወጣት የሆነችው የግሌ ከዩኒቨርሲቲ ከተመረቀች ዓመት አልሞላትም፡፡ በምርቃቷ ማግስት ስራ ማግኘቷ ሁሉንም አስደስቷል፡ ፡ ስራ አጥታ ባለመቀመጧ እንደ እድለኛ እየታየች ኑሮን ማጣጣሟን ቀጠለች። አልፎ አልፎ ከሚያስቸግራት የጨጓራ ህመም ውጪ  ፍፁም ጤነኛ ነበረች።

አንድ ቀን ‹‹ጨጓራዬን አመመኝ›› ብላ ከስራ ቀረች፡፡ ብታርፍም ምንም አልተሻላትም፡፡ ለውጥ አለመምጣቱን የተመለከቱት ወላጆቿ በአቅራቢያዋ ወደ ሚገኘው በአዊ ብሔረሰብ  ዞን የጃዊ ሆስፒታል ይዘዋት ጎራ አሉ። ሰአቱ መሽቶ ስለነበር የምሽት ተረኛ የሆነውን ‹‹ዶክተር›› አነጋግረው እርዳታ ሊያደርግላት ይዟት ገባ። ወደ ህክምና ተቋሙ የገባችው ወጣት የግሌ ግን በእግሯ ከመጣችበት ሆስፒታል በሬሳ ሳጥን መመለስ እጣዋ ሆነ።

ለከፉ ይሰጣል ያልተባለው በሽታ ምን ትሁን ምን ሳይታወቅ ለዘላለም አንድታሸልብ አደረጋት። ህመሟ ለሞት ያለማድረሱ ነገር አልዋጥ ያላቸው ቤተሰቦቿ ጉዳዩን ወደ ህግ ይዘውት ሄዱ። ያን ጊዜ ምርመራ ሊያደርግ የመጣው የፖሊስ ቡድን ከዚህ ቀደም ክስ የነበረበት የሆስፒታሉ ሰራተኛ ጌትነት ወንድአወቅ ህክምናውን እንደሰጣት ሲታወቅ የአስከሬን ምርመራ እንዲደረግ ታዘዘ።

ልጅቷም በተሳሳተ መድሃኒት የተነሳ ህይወቷ ማለፉን ፖሊስ ደረሰበት። ጉዳዩ ጊዜ እንደማይሰጥና ‹‹ዶክተር›› ተብዬው ስራ ላይ ቢቆይ የባሰ ጥፋት እንደሚያደርስ የተገነዘበው ፖሊስም ‹‹ዶክተር›› ነው የተባለውን ግለሰብ በቁጥጥር ስር በማዋል ምርመራውን አጠናክሮ ቀጠለ።

## ‹‹ አስመሳዩ ዶክተር››

ግለሰቡ ጌትነት ወንድአወቅ ይባላል። ከልጅነት ጀምሮ ህልሙ የህከምና ሰው መሆን ነበር። በልጅነቱ ‹‹ዶክተር መሆን እፈልጋለሁ›› እያለ ቢያድግም ‹‹ዶክተር›› እንዲሆን ሊያደርገው የሚችል ምንም አይነት ጥረት ሲያደርግ አይታይም ነበር። በትምህርቱ ሰነፍ ከሚባሉት ተማሪዎች ተርታ የተሰለፈ ለመምህራኑ የማይታዘዝ አስቸጋሪ ልጅ ነበር።

እየወደቀና እየተነሳ አስረኛ ክፍል የደረሰው ይህ ሰው እንደ ምንም የቴክኒክና ሞያ ትምህርት ሊያገኝ የሚችልበትን ነጥብ አግኝቶ በአንድ የሙያ ትምህርት ቤት 12+4 ወረቀት ይዟል። ምንም እንኳን የትምህርት ደረጃው እዚህ ላይ ቢሆንም የህክምና ፍቅርና ምኞቱ ከውስጡ አልወጣለት ብሏል።

በህልሙም በእውኑም የሚታየው ሀኪም መሆን ብቻ ነበር። ይህን ህልሙን ለማሳካት በአንድ የግል አነስተኛ ክሊኒክ ውስጥ የካርድ ክፍል ባለሙያ ሆኖ ተቀጠረ። ያኔ ነጩን ገዋን ለብሶ ሰዎችን ሲያስተናግድ ‹‹ዶክተር›› የመሆን ህልሙን ሊያሳካ የሚችል ቦታ ላይ መቆሙን አሰበ። ከዛ ቀስ በማለት በመለሳለስ ከነርሶቹም ከሀኪሞቹም ጋር ጠጋ በማለት ጨዋታቸውንም ስራቸውንም ይሸመድድ ገባ።

ከዕለታት አንድ ቀን እሱና የምሽት ተረኛው ሀኪም ብቻ በጤና ተቋሙ ውስጥ ያድራሉ። ሌሊት አካባቢ አንድ የታመመ ሰው ይመጣል፤ ተረኛውን ሀኪም ሊጠራው  ሲሄድ በር ዘግቶ በመተኛቱ የተነሳ ሊያዳምጠው አልቻለም።

ይሄኔ የዘላለም ምኞቱ የሆነውን ህክምና የሚለማመድበት ሰአት እንደደረሰ በማመን በመመርመሪያ ክፍል ውስጥ ገብቶ እንደ ዶክተር በመሆን መዘጋግቦ መረመርኩ ብሎ ሲያበቃ ማስታገሻ በማዘዝ በሽተኛውን ይሸኛል። እንደዚህ ብሎ የጀመረውን ስራ በየአጋጣሚው በመደጋገም ውሸቱን ተላምዶት እውነተኛ ዶክተር የሆነ መስሎት ቆየ። ዶክተር የመሆን ህልሙንም ማንም ሰው የማያውቀው ቦታ በመሄድ በህክምና ለመቀጠር የሀሰት የትምህርት ማስረጃ አዘጋጀ።

ግለሰቡ ካዘጋጀው የሀሰተኛ ትምህርት ማስረጃ በተጨማሪ በአብክመ ጤና ቢሮ ከ4/2/2014 - 4/2/2019 የሚያገለግል የሚል የሀሰት የሙያ ፈቃድ በመያዝ በአብክመ ጤና ቢሮ ሥር ባሉት ሆስፒታሎች በማችንግ ፈንድ ፕሮግራም የቋሚ ቅጥር ማስታወቂያ ተወዳድሮ 50 በመቶ  በማምጣት በደረጃ 14 ብር 9056 እየተከፈለው እንዲሰራ ይደረጋል።

በዚህ ሂደት ነው አንግዲህ ያለምንም እውቀት በድፍረት የሰዎች ህይወትን የሚያስከፍል ሞያ ላይ ተሰማርቶ ከተጠየቀባቸው ሰዎች በተጨማሪ በሱ ስህተት የተበላሹና ህይወታቸውን ያጡ ሰዎችን ሐኪም መስሎ አታለለ። ይህ የቅጥፈት ተግባሩን ሲያከናውን የነበረው ግለሰብ የሰዎች ህይወት በመጥፋቱ የተነሳ በቁጥጥር ስር ሆኖ ምርመራ ይደረግበት ጀመር።

## የፖሊስ ምርመራ

ግለሰቡ እድሜው 35 መሆኑና የትምህርት ደረጃውም 12+4 መሆኑ ታወቀ። የጃዊ ሆስፒታል ቅጥር ሰራተኛ ሆኖ ሲያገለግል የነበረው ጌትነት ወንድአወቅ የተባለ ተከሳሽ በድሬዳዋ ዩኒቨርሲቲ ሳይማር በሜዲስን የዶክትሬት ዲግሪ እንደተማረ በማስመሰል በሀሰት በተዘጋጀ የዶክትሬት ሰርተፊኬት የትምህርት ማስረጃ ያቀረበ መሆኑም ታወቀ።

ከዚህም በተጨማሪ ግለሰቡ በአብክመ ጤና ቢሮ ከ4/2/2014 - 4/2/2019 የሚያገለግል የሚል የሀሰት የሙያ ፈቃድ በመያዝ በአብክመ ጤና ቢሮ ሥር ባሉት ሆስፒታሎች በማችንግ ፈንድ ፕሮግራም የቋሚ ቅጥር ማስታወቂያ ተወዳድሮ 50 በመቶ በማምጣት በደረጃ 14 ብር 9056 እየተከፈለው ሲሰራ እንደነበር ተደረሰበት።

ፖሊሶችም ግለሰቡ እድሜው 35 መሆኑና የትምህርት ደረጃውም 12+4 መሆኑን፤ እንዴት ግለሰቡ " ዶክተር " ተብሎ ሊጠራ ቻለ? እንዴት ፈተናውን አለፈ? ግለሰቡ ይሄን ያህል ርቀት ሲጓዝ ከጀርባው ማን ነበር? የሚሉ ጥያቄዎችን አስነሳ። እዚህ ጋር በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ‹‹ዶክተር ነኝ›› ያለው ግለሰብ እንዴት የተሰጠውን ፈተና 50 በመቶ ሊያልፍ እንደቻለ የተገኘ ማስረጃ የለም።

የእነዚህን ጥያቄዎች መልስ ለማግኘት ተጨማሪ ምርመራዎች እያደረገ ቢሆንም በዚህ ልክ በድፍረት በሰው ህይወት ላይ ጉዳት ያደረሰው ሰው ግን በህክምና የእውቀት ችግር ምክንያት በተፈጠረ ስህተት አንድ የ7 ወር ህፃን እና አንዲት የ25 ዓመት ወጣት ለሞት መዳረጉ ተረጋገጠ።



ፖሊስ ሲመረመር ቆይቶ፤ አንድ በሀሰተኛ የትምህርት ማስረጃ ‹‹ዶክተር ነኝ›› ብሎ ሲሰራ የነበረ ግለሠብ ለፍረድ እንዲቀርብ ስራውን ቀጠለ። ፖሊስ የምስክሮችን ቃል የታክቲክና የቴክኒክ ማስረጃዎችን በማጠናከር ተጠርጣሪውን ለአዊ ዞን ብሄረሰብ ዞን ፍትህ መምሪያ አቃቤ ህግ በማድረስ ጉዳዩ ለፍርድ እንዲቀርብ አመቻቸ።

አቃቤ ህግም የምርመራውን ውጤት በመያዝ ክስ የመሰረተ ሲሆን፤ በፍርድ ቤቱ ተጠርጣሪው ቀርቦ የእምነት ክህደት ቃሉን በመስጠት ጉዳዩ ሲታይ ቆይቶ የሚከተለውን  ውሳኔ አስተላልፏል።

## ውሳኔ

አቃቤ ህግ ከአይን እማኞችና ከተለያዩ ምርመራዎች የተገኙ ማስረጃዎችና መረጃዎች ተጠናክሮ የቀረበለትን ማስረጃ በመያዝ ለአዊ ዞን ብሄረሰብ ፍትህ መምሪያ ከፍተኛ ፍርድ ቤት አቅርቧል። ተከሳሹም የመከራከር መብቱን ተጠቅሞ የተለያዩ ክስ ማቅለያዎችን ቢያቀርብም ተቀባይነት አላገኘም፡፡ በመጨረሻም  ፍርድ ቤቱም ግራ ቀኙን አይቶ ያለውን መረጃና ማስረጃ መርምሮ  ተከሳሹ ላይ ውሳኔ ተላልፎበታል።

ግለሰቡ በፈፀመው በሀሰተኛ ሰነድ መገልገልና በሰው ህይወት የማጥፋት ወንጀል በአስራ አንድ ዓመት ጽኑ እስራትና በብር 5 ሺህ እንዲቀጣ ተወስኗል።

መዝናኛ

# ማረፊያ/ ትዝብት

## የእረፍት ቀናትና የአዕምሮ ሰዓት

ደበል ከሳ

ዛሬ ጠጣር ጉዳዮችን ለጊዜው ተወት አድርገን ቀላል የሚመስሉ ግን ዋጋቸው ትልቅ የሆኑ የሕይወት ክፍሎቻችን እያነሳሳን እረፍት እናደርጋለን። በእርግጥ የሥነ አዕምሮና ሥነ ልቦና ሊቃውንት እንደሚመክሩን እንደጭንቀት፣ ድብርትና ከመሳሰሉ ሌሎችም የአዕምሮ በሽታዎች ለመዳን ተመራጩ መንገድ ሁልጊዜ ራሳችንን ሥራ ውስጥ መደበቅ ነው። ይሁን እንጂ "ሰውም ገደብ(ሊሚት) አለው" እንዳለው ጓድ መንግስቱ ኃይለማርያም ድካም የተፈጥሮ ባህሪያችን ነውና እረፍት ማድረግም ከሥራ እኩል ለጤና አስፈላጊ መሆኑን መገንዘብ ይገባል። ምክንያቱም ሁሌም ያለምንም ሥራ ሁሌም በእረፍት ላይ መኖር ለጭንቀትና ድብርት መንስኤ እንደሚሆነው ሁሉ ያለእረፍት መሥራትም ከሰው ተፈጥሯዊ ባህሪ ተቃራኒ በመሆኑ ከጥቅሙ ጉዳቱ ያመዝናልና።

ታዲያ እውነታው ይህ ከሆነ እርስዎ ሳምንቱን ሙሉ በሥራ ተጠምደው ሰንብተው ቅዳሜና እሁድ ሲመጣ በሥራ የዛለ አካልዎትን ዘና ለማድረግ ወደ የት ነው የሚሄዱት? ለምሳሌ ከጓደኞችዎ ጋር ሰብሰብ ብለው ሻይ ቡና እያሉ ጥሩ ጊዜ ሊያሳልፉ ወደሚችሉባቸው መናፈሻ ቦታዎች ሊያመሩ ይችላሉ። አልያም ከከተማ ወጣ ብለው ነፋሻማውን አየር ተመግበው፤ ጋራ ሸንተረሩን ቃኝተው፣ የዛፎቹ ጥላ ሥር አርፈው የወፎቹን ዜማ አዳምጠው፣ በአበቦች መዓዛ ረክተው ተፈጥሮን በማድነቅ ራስዎን አዝናንተው ሊመለሱ ይችላሉ።

ምናልባትም እርስዎ መጠጣት ላያስደስትዎት ይችላል(መጠጣት ሲባል ውሃ አለመሆኑ ልብ ይባልልኝ፤ ያችን ሞቅ የምታደርገንንና የሆድ የሆዳችንን የምታስወራንን የመጠጥ ቤቷን ውሃ ማለቴ ነው)። መጠጣት የሚያዝናናቸው ግን ብዙ ሰዎች አሉ። ብቻ መዝናናት ወይም መዝናኛ እንደየሰው ፍላጎትና ስሜት ይለያያል። እርስዎን የሚያዝናናዎ ሌላውን ላያዝናናው ይቻላል። እናም መዝናናት ልክ እንደ ውበት ነው። ውበት እንደ ተመልካቹ፤ መዝናኛም እንደ ተዝናኙ ነው።

በዚህም ሆነ በዚያ መዝናናት ሲባል ብዙውን ጊዜ ቀድሞ ወደ አዕምሯችን የሚመጣው ግን በሥራ የደከመ አካላችንን ዘና የሚያደርግልን ነገር ነው። ይሁን እንጂ በዕውቀት ወይንም በሳይንስ የተደገፈ ሳይሆን በዘልማድ የምናደርገው፣ አግባብነትም የሌለው ልማዳዊ አመለካከት ነው። ምክንያቱም በሥራ የሚደክመው አካላችን ብቻ አይደለም። ያለምንም እረፍት በርካታ ጊዜያትን በሥራ ተወጥረን በምናሳልፍበት ጊዜ አካላችን ብቻ ሳይሆን አዕምሯችንም ድካም ይሰማዋል፤ የምንሠራቸው ሥራዎች ሁሉ የሚሠሩት በአካል ብቻ ሳይሆን በአዕምሮም ጭምር ነውና።

ጉዳዩን በአንክሮ ከመረመርነው እንዲያውም ከአካላችን በላይ አዕምሯችን ነው ብዙ የሚደክመው፣ ብዙ የሚሠራውም እርሱ ነውና። ከዚህም ባሻገር በዘርፉ ሳይንስ እንደሚታወቀው አዕምሯችን ሦስት ዋና ዋና ክፍሎች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ መካከል አንደኛው፤ "በከፊል ያልነቃው" ወይንም በእንግሊዝኛው "Subconscious Mind" በመባል የሚታወቀውና እጅግ አስፈላጊው የአዕምሯችን ክፍል ሃያ አራት ሰዓት ነው የሚሠራው። ቀን ስንሠራ ውለን በተፈጥሮ ሕግ ምክንያት ሌሊት ስንተኛ አካላችን ሲያርፍ እንኳን ይሔኛው የአዕምሯችን ክፍል አያርፍም፤ ሁልጊዜ ያለእረፍት ነው የሚሠራው።

ስለሆነም ከሥራ ተመልሰን በእረፍት ቀናችን እረፍት ስናደርግ ማረፍ ያለበት አካላችን ብቻ ሳይሆን አዕምሯችንም ጭምር መሆን አለበት። በእረፍታችን ሰዓት ስንዝናናም መዝናናት ያለበት አካላችን ብቻ ሳይሆን አዕምሯችንም ጭምር መሆን አለበት። ምክንያቱም ሰው አካላዊም አዕምሯዊም ፍጡር ነውና። ለምሳሌ እርስዎ በሥራ ብዛት የደከሙ ጡንቻዎችዎችን ዘና ለማድረግና እንደገና በአዲስ ኃይል ለመሙላት በእረፍት ቀንዎ ወደማሳጅ ቤት ሄደው ማሳጅ ሊያደርጉ(ሰውነትዎን ሊታሹ) ይችላሉ። አቅም ካልገደብዎት ይህንን ማድረጉ መልካም ነው፣ ጠቃሚም ነው። በእርግጥም በሥራ ብዛት የደከመ አካልዎን ያክማልና።

በሥራ ብዛት፣ የደከመ(የተሰላቸ)፣ በኑሮ ውጣ ውረድ በውጥረት የተጨነቀ አዕምሮዎን ዘና ለማድረግ ቢፈልጉስ ምንድነው የሚያደርጉት? ወዴትስ ነው የሚሄዱት? እንዴትስ ነው ይህንን ማድረግ የሚችሉት? እርስዎ የራስዎ ብልሐት ይኖርዎታል። እኔ በበኩሌ የአካልዎ ብቻ ሳይሆን የአዕምሮ ማሳጅ ቤት ያስፈልግዎታል እልዎታለሁ። አዕምሮ ከድካሙ የሚታደሰውና እንደገና አዲስ ኃይል የሚያገኘው ከመሰልቸትና ከተስፋ መቁረጥ ስሜት ተላቅቆ ስለ ስኬትንና ድል አድራጊነትን ማሰብ ሲጀምር ነው።


አዕምሮን ከድካሙ ለማሳረፍና በኃይል እንዲታደስ ለማድረግ በሕይወት ጉዞ ውስጥ የሚያጋጥሙ ችግሮችን በፅናት ታግሎ አሸንፎ፣ መሰናክሎችን በብቃት አልፎ ከተራራው ጀርባ ከሚገኘው ብሩሃማ ቦታ መድረስ እንደሚቻል ማወቅና ማመን ይህንንም ለአዕምሯችን መንገር ያስፈልጋል። ይህ ነው የአዕምሮ ማሳጅ የሚባለው። ደጉ ነገር ደግሞ የአዕምሮ ማሳጅ ለማግኘት እንደ አካላዊው ማሳጅ ብዙም ከባድ አለመሆኑ ነው። በእርግጥ አካላዊ ማሳጅ ለማድረግ የሚከፈለው ክፍያም ያን ያህል ውድ ሆኖ አይደለም(ለእኔና የእኔ ቢጤ ጓደኞቼ ግን ለማሳጅ የሚከፈለው የወር አስቤዛችን ሊሆን ስለሚችል ነው ከአካላዊው ይልቅ የአዕምሮ ማሳጅ ቤት ይቀላል ያልኩት)።

ጭብጤን በደንብ ለማስረዳት ወይም ለማለት የፈለግኩት የአዕምሮ ማሳጅ ለማድረግ በእርግጥም ብዙ የሚያስወጣ አይደለም ነው። በተለይ መረጃ እጅግ እየቀረበን መጥቶ በሁላችንም እጅ መዳፍ ላይ በሆነበት በአሁኑ ዘመን አዕምሮዎን ለማዝናናትና በአንዳች ደስ የሚል የአሸናፊነት ስሜት ለመሙላት "አነቃቂዎች" ጋር መሄድ አይጠበቅብዎትም።

ይህን ለማድረግ ጥቂት ሳንቲሞችን ብቻ አውጥተው ስለስኬት የተጻፉ መጽሃፎችን ማንበብ(በተመሳሳይ እጅዎ ላይ የሚገኘውን ተንቀሳቃሽ ስልክዎንም ለዚህ ተግባር ሊጠቀሙበት ይችላሉ)። አለያም ጥቂት ሳንቲሞችን ብቻ ከፍለው እጅዎ ላይ ባለው ሞባይል ትልቅ ፋይዳ ያላቸው ሙያዊና ሳይንሳዊ ንግግሮችንና ቪዲዮዎችን ከበይነ መረብ አውርደው ሊያዳምጡና ሊመለከቱ ይችላሉ።

ከእርስዎ የሚጠበቀው ፍላጎት ብቻ ነው። ለዚህም እረፍትና መዝናናት የሚያስፈልገው ለአካላችን ብቻ ነው ከሚለው ልማዳዊ የተሳሳተ አስተሳሰብ ባሻገር ማሰብ፣ አዕምሮም እረፍት እንደሚያስፈልገው ማወቅ ፍቱን መፍትሔ ይሆንልዎታል። መልካም እረፍት ይሁንልዎ!

# ዓለም አቀፍ




የዝንጀሮ ፈንጣጣ ክትባት

## ደቡብ ኮሪያ የዝንጀሮ ፈንጣጣ ክትባት ለአፍሪካ ልትሰጥ ነው

በጋዜጣው ሪፖርተር

አዲስ አበባ፡- ደቡብ ኮሪያ ለአፍሪካ ዝንጀሮ ፈንጣጣ ክትባት ልትሰጥ መሆኑን አሶሼይትድ ፕሬስ ዘገበ።

አፍሪካ ለመጀመሪያ ጊዜ የዝንጀሮ ፈንጣጣ ክትባት ከደቡብ ኮሪያ ለመውሰድ መወሰኗን አንድ የአፍሪካ ከፍተኛ የሕዝብ ጤና አገልግሎት ኃላፊ ጠቅሶ አሶሼይትድ ፕሬስ ዘገባው ይፋ አድርጓል።

እንደ ዘገባው ከሆነ 50 ሺህ ዶዝ ክትባት ለአፍሪካ የበሽታ መቆጣጠሪያና መከላከያ ማዕከል የሚሰጥ ሲሆን ክትባቱ በዋናነት ለጤና ባለሙያዎችና በሽታው የተስፋፋበት አካባቢዎች ለሚኖሩት ሰዎች የሚታደል ይሆናል። ነገር ግን ድጋፉ ከደቡብ ኮሪያ ወደ አፍሪካ የሚገባበት ቀነ ቀጠሮው በውል አልተገለጸም።

የዝንጀሮ ፈንጣጣ በሽታ በአፍሪካ እምብዛም የተለመደ ክስተት ባይሆንም በያዝነው ዓመት በአህጉሪቱ 202 ሞት መመዝገቡንና በ13 የአፍሪካ አገራት የሞት መጠንም 19 ነጥብ 3 በመቶ መድረሱ ተገልጿል።

ይሁን እንጂ የአፍሪካ የጤና ባለሥልጣናት በሽታው የተከሰተባቸው በተለይ ሀብታም ከሆኑ ከምዕራባውያን አገሮች ስለ ወረርሽኙ በቂ መረጃ ለማግኘት ለወራት ያህል ጥረት ሲያደርጉ ቆይተዋል።

የሲዲሲ ተጠባባቂ ዳይሬክተር አህመድ አግዌል ባለፈው ሳምንት በኮንጎ 51 አዳዲስ የዝንጀሮ ፈንጣጣ ምልክቶች መታየታቸውን ጠቅሰው፤ ጋና እና ናይጄሪያ ደግሞ በጣም የተጠቁ ወገራት መሆናቸውን ተናግረዋል።

## ጆ ባይደን የዩክሬን ጦርነት ለማቆም ከፑቲን ጋር ለመነጋገር ዝግጁነታቸውን ገለጹ

በጋዜጣው ሪፖርተር



አዲስ አበባ፡- ፕሬዝዳንት ባይደን የዩክሬንን ጦርነት ለማቆም ከሩሲያ አቻቸው ፕሬዚዳንት ቭላድሚር ፑቲን ጋር ለመምከር ዝግጁ መሆናቸውን ተናገሩ። ፕሬዝዳንት ጆ ባይደን ከፈረንሳይ አቻቸው ጋር በዋሽንግተን ተገናኝተው መምከራቸው ተገልጿል።

የሩሲያ እና ዩክሬን ጦርነት፣ የአየር ንብረት ለውጥ፣ የኢኮኖሚ ማሻሻያ እና ሌሎች ጉዳዮች ደግሞ የሁለቱ አገራት ፕሬዝዳንቶች የተወያዩባቸው አጀንዳዎች እንደሆኑ ሮይተርስ ዘግቧል።

ፕሬዝዳንት ባይደን የዩክሬንን ጦርነት ለማቆም ከሩሲያ ፕሬዝዳንት ፑቲን ጋር ለመምከር ዝግጁ መሆናቸውን ተናግረዋል።

ይሁንና ፕሬዝዳንት ፑቲን ጦርነቱን ለማቆም ፍላጎት እንዳላሳዩ የተናገሩት ፕሬዝዳንት ባይደን "ይሄን ጦርነት ለማቆም ብቸኛው መፍትሄ ሩሲያ ጦሯን ከዩክሬን ማስወጣት ብቻ ነው" ሲሉም አክለው ገልጸዋል።

ፕሬዝዳንት ፑቲንን በአካል ማግኘት እፈልጋለሁ የሚሉት ፕሬዝዳንት ባይደን ከፑቲን ጎን ቁጭ ብዬ አዕምሮው ውስጥ ምን እንዳለ እና ምን እንደሚያስብ ማወቅ እፈልጋለሁም ብለዋል።

የፈረንሳይ ፕሬዝዳንት ኢማኑኤል ማክሮን በበኩላቸው፣ በግዛታቸው እና በአገራቸው ጉዳይ መወሰን እና መደራደር የሚችሉት ዩክሬናዊያን ብቻ መሆናቸውን አስምረውበታል።

በዩክሬን ጉዳይ ግንኙነታቸው ወደተባባሰ ሁኔታ የተቀየረው ሩሲያ እና አሜሪካ ባለስልጣናት በያዝነው ሳምንት በኑክሌር ጦር መሳሪያ ቁጥጥር ዙሪያ በግብጽ መዲና ካይሮ ተገናኝተው ለመምከር ቀጠሮ ይዘው የነበረ ቢሆንም ሩሲያ በመድረኩ እንደማትሳተፍ ማስታወቋ ይታወሳል።

ሩሲያ በዚህ መድረክ ላይ ለመሳተፍ ይዘው የነበረውን ቀጠሮ የሰረዘችው አሜሪካ ጸረ ሩሲያ የሆኑ ድርጊቶችን ባለማቆሟ እና ይህንን የካይሮ ውይይት መድረክ ለራሷ በሚጠቅም መንገድ ለመፈጸም በማሰቧ እንደሆነ ገልጻለች።

የሁለቱ አገራት የደህንነት ኃላፊዎች ከሁለት ሳምንት በፊት በተርኪየ የኢኮኖሚ መዲና ኢስታንቡል ተገናኝተው በተመሳሳይ ጉዳይ ላይ መምከራቸውም ይታወሳል።

# መጋቢ አዕምሮ

# ከዓለም ዋንጫ እስከ ዓለም ዋንጫ!

**በአገልጋይ ዮናታን አክሊሉ**

የሸቀጥ ሱቅ ውስጥ እናትና ልጅ ይገኛሉ። በጠባቦ የሸቀጥ ሱቅ ውስጥ ብዙ ነገር አለ። መርፌ፣ ክብሪት፣ ሻማ፣ ሳሙና፣ እርሳስ፣ ከረሜላ፣ ዘይት ወዘተ በትንሿ ሱቅ ውስጥ ከሚገኙት መካከል ናቸው። የተከፈተው ሬዲዮ የዓለም እግር ኳስ ዋንጫን እየዘገበ ነው። እንደ ጨዋታው ሁኔታ የጨዋታው አስተላላፊ ጋዜጠኛ ድምጹን ከፍ ዝቅ እያደረገ አየሩን ተቆጣጥሯል። እናት በሱቁ ውስጥ ያሉትን እቃዎች የት እንደተቀመጡ ያውቃሉ። ታዳጊው ልጃቸው ደግሞ በእቃዎቹ ላይ የተጻፈበትን አንብቦ በመረዳት ከእርሳቸው የተሻለ ነው።

የበዙት እቃዎች መነሻቸው ቻይና መሆኑን ታዳጊው ልጃቸው ያውቃል። አልፎ አልፎ ደግሞ የሌሎች አገራት እቃዎችም አሉ። ጋዜጠኛው የሚጠራውን አገር ስም ልጃቸው የሚረዳው ከአገራቸው በሚመጣው እቃ ነው። ቻይና በዓለም እግር ኳስ መድረክ ላይ ስሟ ከፍ ብሎ አለመጠራቱን ልጃቸው እያሰበ ንግድና ስፖርት ሁለቱም ውድድር እንደሆነ ያብሰለስላል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ የሆነው ልጅ እናቱን፤ እማዬ ስፖርት እና ንግድ አንድ መሆኑን ታውቂያለሽ ብሎ ይጠይቃቸዋል። እናትም እንዴት አልክ ልጄ ሲሉ ይመልሳሉ። ልጅም እግር ኳስ ላይ ከምድባቸው አልፈው ወደ ቀጣይ ደረጃ ለመግባት እና በመጨረሻም ዋንጫው ላይ ለመድረስ ነው ይህን ያክል የሚለፉት፤ በንግድም እኮ ያመረቱት ምርት ገበያ እንዲያገኝ ድንበር ተሻግሮ ውጤታማ እንዲያደርጋቸው ነው የሚሰሩት። ለምሳሌ እኛ ሱቅ ውስጥ ባለው እቃ አሸናፊው ቢለይ ቻይና እንደ አገር አሸናፊ ናት ምክንያቱም የቻይና እቃ ሱቃችንን የሞላው ስለሆነ። ኳስም ወደ ዋንጫው ለመድረስ የሚደረግ ፉክክር ነው ንግድ ደግሞ ገበያውን ለመቆጣጠር የሚደረግ ፉክክር ነው። ሲል ማብራሪያውን ሰጠ። እናትም የልጃቸውን ማብራሪያ በጥሞና ካዳመጡ በኋላ እርሱስ ልክ ነህ ልጄ ሕይወት በጥቅሉ በፉክክር ውስጥ የተቃኘች ናት። እኛም በአቅማችን አጠገባችን ካለው ሱቅ ጋር ተፎካክረን ገበያ ለማግኘት ፈልገን አይደል የምንደክመው። ሁሉም የሚለፈው ተፎካክሮ ወደ ውጤት ለመድረስ ነው። ፉክክሩ ግን የራስን ጥቅም ለማስከበር በሚል በሌላው ላይ ወንጀል በመስራት የሌላውን መብት በመደፍጠጥ አይደለም። እግር ኳስ ሜዳው ውስጥ ዳኛው ባይኖር ምን ሊፈጠር እንደሚችል እስኪ አስበው። ተጫዋቾች ሊደባደቡ ሁሉ ይችላሉ። ፉክክር መኖሩ እንዳለ ሆኖ ረጅሙ መንገድ ፍሬያማ እንዲሆን ከመነሻው እስከ መድረሻው ፍትሐዊ የሆነ አሰራር አስፈላጊ ነው። ወደ ዓለም ዋንጫ መጥቶ ለመወዳደር በየደረጃው የሚደረገው ውድድር ፍትሃዊ ባይሆን፤ ዳኞች ጨዋታውን በፍትሃዊነት እንደሚዳኙ ተስፋ ባይደረግ፤ ወዘተ ውድድሩ ሊደረግ አይችልም። በማለት ልጃቸው በጀመረው መስመር ገብተው መልእክታቸውን አስተላለፉ።

ልጃቸው የእናቱን ሃሳብ በማድመጥ ላይ እያለ በምናቡ ከአንድ የዓለም ዋንጫ እስከ ቀጣዩ የዓለም ዋንጫ ድረስ ያሉትን አራት አመታት አሰባቸው። በአራት አመት ውስጥ ዛሬ ከምድባቸው የወደቁ በቀጣይ ወደ ውድድር መድረኩ ተመልሰው ፍሬያማ ስራ የሚሰሩበት፤ ዛሬ ዋንጫ የበላ በሚቀጥለውም ለመድገም ጥረት የሚያደርግበት፤ በዓለም ዋንጫው መሳተፍ የሚፈልጉ ነገር ግን እድሉን ያላገኙ በቀጣይ ወደ መድረኩ ለመምጣት የሚሰሩበት ወዘተ አራት አመታት ናቸው። ተጫዋቾች ደግሞ በየክለቦቻቸው በሚያደርጉት ተሳትፎ ውጤታማነት ለብሄራዊ ቡድን ለመጠራት ብዙ የሚሰሩበት ነው። ከአንድ የዓለም ዋንጫ እስከ ቀጣዩ የዓለም ዋንጫ ውስጥ እጅግ ብዙ ስራዎች ይሰራሉ። ተረኛው የዓለም ዋንጫ ደጋሽ አገር የሚነሳበትን ማናቸውም ጥያቄዎች እየመለሰ ድግሱን አከናውኖ በድል ለመጨረስ ጥረት ያደርጋል። ታላቅ ድግስ ነውና።

**ድግስን ባሰብን ጊዜ፤-**

**1. ዝግጁ መሆን**

አንዳንዱ ነገር በእቅድና በስራ የሚመጣ ነው። አንዳንዱ ነገር ሳይታቀድ ድንገት የሚሆን እና መሰረታዊ በሚባል ደረጃ የሕይወታችንን አቅጣጫም የሚቀየርም ነው። በሕይወት ላይ ያልተጠበቀ ሊሆን እንደሚችል በማሰብ አስቀድሞ ዝግጅት የሚያደርግ ሰው ምን ያህሉ ይሆን? ሰዎች በሰዎች የሚጎዱበት ዋናው ምክንያት የማይጠብቁ በመሆናቸው ነው። የሚጠብቁ ቢሆኑ አይጎዱም፤ ያልጠበቁት በሚሆንበት ሁኔታ ግን ለጉዳት ይዳረጋሉ። በኮቪድ ወቅት የነበረው አስቸጋሪ ነገር በሽታው ብቻ አልነበረም፤ በሽታውን ተከትሎ የመጡ ያልተጠበቁ ነገሮችም ይገኙበታል።

አርሶ አደሩ ወደ እርሻው ስፍራ ሲሄድ ግብ የሚያደርገው ያቀደውን ምርት ከማሳው ላይ መሰብሰብ ነው። ተማሪው ከትምህርት ቤት ሲሄድ ወደቤቱም ሲመለስ፤ ከመጽሐፍት ጋር ጊዜን ሲያሳልፍ ያለመውን ውጤት የራሱ ለማድረግ ነው። ነገር ግን በተጨባጭ የታሰበው ሳይሆን ሲቀር ሕይወት ላይ ጥሎ የሚያልፈው ጠባሳ ከባድ ይሆናል። አንዳንዴም በመነሻችን ላይ እንዳገኘነው ታሪክ እስከ ወዲያኛው የሕይወትን በር መዝጋት ይሆናል።

በመሆኑም በሌሎች ሰዎች ላይ የደረሰው አንድ ቀን በእኔ ሕይወት ውስጥ ቢደርስ ምን አደርጋለሁ ብሎ ራስን እየጠየቁ መኖር እጅግ ማትረፍ ነው። ዛሬ መልካሙን ለመያዝ ፍጠን፤ ነገር ግን ሕይወት ባልተጠበቀው አቅጣጫ መንገድን ሰርታ ብትጠብቀህ ወደ መልካሙ አቅጣጫ ሕይወትን ለመውሰድ አንድ እርምጃ ወደ መፍትሔው ለመቅረብ እንድትችል ያልተጠበቀው ቢሆን የሚል ዝግጁነት ይኑርህ።

መልካሙን ወይንም ምርጡን መጠበቅ እንዳለ ሆኖ ነገር ግን በተቃራኒው አስከፊው ሊመጣ እንደሚችል በማሰብ ዝግጁ መሆን ይገባሃል። 'የምበላው አጣ ይሆን?' ብለህ አስበህ በማታውቅበት ወቅት ወይንም ጓዳህ ተትረፍርፎ ባለበት ወቅት ሕይወት በተቃራኒው አቅጣጫ ሄዳ የምትገኝበት ጊዜ መጎዳት እንዳይሆን ሁሌም ለማንኛውም ነገር ዝግጁ መሆን አትራፊነት ነው።

**መነሻው አንድ ነው**

የጊዜ ቀለበት መነሻው ሁለት አይደለም፤ አንድ ነው። መነሻው አመታት አይደለም ሽርፍራፊ ሰከንድ ነው። አንድ ብለን መቁጠር ጀመርን። አንድ ብለን መቁጠር ከጀመርንበት ጊዜ አንስቶ ወደኋላ በምናብ ብንሄድ ወራቱና ቀናቱ ትዝታ ሆነው ከኋላችን ናቸው። የዘመናችንን ታሪክ ለመስራት የተገለጡ አዳዲስ ቀናት ደግሞ ከፊታችን። በውስጣዊ ሰውነት በአዲስነት ለሚቀበለው ትርጉም የሚሰጥ። የለውጥ መንገድን የራሱ ላደረገ ሰው ትርጉም የሚሰጥ የጊዜ ቀለበት።

በዘመን መለወጫ ወቅቶች በአመቱ ውስጥ ሽልማት የተገባቸውን ለይቶ እውቅና የመስጠት ባህል እየተለመደ ያለ ባህል ሆኗል። በዘርፉ ላይ ጎላ ብለው የወጡና አስተዋጽኦ ያደረጉትን መርጦ የመሸለም ተግባር በአገራችንም በመላው ዓለምም የተለመደ ተግባር ነው። ሰዎች በአደባባይ የሚሸልሟቸው ወደ ደረጃው ከመውጣታቸው በፊት ራሳቸውን የሸለሙ መሆናቸውን አስበን እናውቅ ይሆን? ለራሳችን ከራሳችን በላይ የሚቀርብ ስለሌለ ራሳችንን ለመሸለም ማንም ሊቀድመን አይገባንም ብሎ የሚያምን ሰው የሚያደርገው። ለራስ ትርጉም በመስጠት የሕይወት ቅኝት ውስጥ የሚመዘዝ ሰበዝ።

አዲስ አመትን ለማብሰር የሰፈሩ ልጃገረዶች አበባይሆሽ ይላሉ። በየቤቱ ደጃፍ ሄደው እየቆሙ ዜማቸውን አሰምተው የሚሰጣቸውን እየተቀበሉ ከአንድ ቤት ወደ ሌላ ቤት የሚደረግ፤ ሁሌ የማይደረግ በልጅነት ወራት በጊዜ ቀለበት ውስጥ የሚሆን። ለልጃገረዶቹ ቤት ያፈራው ሲቀርብ እነርሱም በዜማ ምስጋናቸውን ያቀርባሉ። በጊዜ ቀለበት ውስጥ ከአንድ ምዕራፍ ወደ ሌላኛው ምዕራፍ ለመሸጋገር ቆሞ ማመስገን የተገባ ነው።

**በምን አወቅናቸው?**

በዓለማችን ውስጥ አዎንታዊ አስተዋጽኦ አድርገው ያለፉ ሰዎችን በምን አወቅናቸው ብለን እንጠይቅ። እከሌን በእዚህ አወቅኩት፤ እከሊትን በእዚህ አወቅናት ስንል የምናነሳው ተጨባጭ ውጤት አለ። ጋንዲን በሰብዓዊ መብት አወቅነው ለዊንስተን ቸርችልን ስለ ነጻነት በሄዱበት ርቀት፤ ማርቲን ሉተር ኪንግ ስለ እኩልነት በጉልህ የፊት ለፊት ሰው ሆኖ በከፈለው ታላቅ መስዋእትነት፤ ቢልጌት በቴክኖሎጂ አብዮተኛነቱ አወቅነው። እንዲህ እያልን ሌሎችንም መጥቀስ እንችላለን። እነዚህ ግለሰቦች አንድ ግለሰብ ሆነው ሳለ ለዓለም ባበረከቱት አስተዋጽኦ የታወቁ ሆነው አገኘናቸው። እይታቸው ይዟቸው ከወጣበት ከፍታ ላይ ቆመው ዓለም አያቸው፤ ወደ ከፍታው ለመድረስ ያለፉበት መንገድ ትልልቅ መጽሐፍ ይወጣዋል።

ዛሬ ሰዎች እንዲያውቁን ከመድከም የጠራ እይታ ኖሮን፤ ተፈጽሞ ልናይ የምንወደው ሆኖ እንድናይ እንመላለስ። ዛሬ በማህበራዊ ሚዲያ ዘመን የሚከተሏቸውን ሰዎች ለማብዛት ትኩረት ሳቢ በሆነ እንቅስቃሴ የተጠመዱ ሰዎችን እናገኛለን። እኛም ከእነርሱ አንዱ ሆነን እንደሆነ በፍጹም አንድከም፤ ስራችን ስለ እኛ መናገር ሲጀምር ሰዎች እንዲከተሉን ሳንጠይቃቸው የሚከተሉን ሆነው እናገኛቸዋለን።

የጠራ እይታ በያዝን፤ በያዝነው እይታ መሰረት በግለት ለመልካም ስራ በተጋን ቁጥር ለውጥ እናመጣለን። የምናመጣው ለውጥ ውስጣችን በተቀጣጠለው እሳት ልክ በተሰማራንበት ዘርፍ ውስጥ ወደፊት ለፊት ይዞን ይወጣል። የተቀጣጠለው እሳትም ነዳጅ ሆኖን ልንሆን ያሰብነው ጋር እንድንደርስ ያግዘናል። ወደ ውስጣችን ብንመለከት በአንዳች ጎልቶ በወጣ ነገር ውስጣችን ሲቀጣጠል ልናገኘውም እንችላለን።

በታሪክ መዝገብ ውስጥ ስለ ሰው ልጆች መልካም ይሆን ዘንድ በብዙ የተጋደሉ ሰዎች መደበኛ ሕይወት ኖረው ካለፉ ሰዎች በተጨባጭ የሚለዩ ናቸው። ይህ በሁሉም ዘርፍ ተመሳሳይ ነው። ጠንካራ የውስጥ ፍላጎት የጠራ እይታን ሰጥቷቸው በጠራ እይታ ወደ ተራራው የደረሱ። ደካማ ፍላጎት ደካማ ውጤት ነው የሚያመጣው። ትንሽ እሳት ትንሽ ሙቀት እንደሚፈጥር ማለት ነው። ትልቁ የውስጥ እሳት ግን አንዳንዴ በትንሽ ነገር እንዳይጋረድ ጥንቃቄን በሚሻ አካሄድ።

**ትንሿ ሳንቲምና የተራራው ምሳሌ**

ወደ ትልቁ ተራራ የሚደረገውን ጉዞ መገዳደር በተመለከተ የትንሿ ሳንቲምና የተራራው ምሳሌ በአስተውሎት እንመልከት። ተራራው ገዝፎ የሚታይ እሩቅ ሆኖ እይታ ውስጥ መግባት የሚችል ነው። ከእርቀት የሚታየውን ተራራ ግን ትንሿ ሳንቲም ወደ አይናችን ባስጠጋን ቁጥር እየጋረደችው ትመጣለች። ሳንቲሙ ወደ አይናችን አብዝቶ ከተጠጋ አብዝቶ የተራራው ምስል እየደበዘዘ ይመጣል።

እይታ በትንሽ ነገር ከተጋረደ ትልቁን ምስል ማየት የማንችልበት ደረጃ ላይ እንደርሳለን። ትልቁ ምስል ከተጋረደ እለታዊ እንቅስቃሴያችን ትንሽ ይሆናል፤ አይናችንን በቀረበው ነገር ልክ ይያዛል። ዛሬ ከእይታ ውስንነት የተነሳ እንቅስቃሴያችን በሰፊው የተገደበ እንደሆነ እናስተውላለን። የፖለቲካ ስሪታችን እንዲሁም አጠቃላይ ማህበረሰባዊ ጉዟችን የሚገነባ ሳይሆን የሚያፈርስ ሆኖ ይታያል። በመቀራረብ አቅምን አሰባስቡ ድምር ውጤቱ ሁሉንም አሸናፊ ከሚያደርግ ጉዞ ይልቅ ሁሉም በጋራ ተሸናፊ የሚሆንበት መንገድን የመረጥን ይመስላል። ተቃርኖው መቆሚያው የት እንደሆነ እርግጠኛ ባንሆንም የእይታ ልክ ግን የሚሰራው ስራ ስለመኖሩ አንዳች ጥርጥር የለንም። ትንሿን ሳንቲም ከአይን ላይ አንስቶ የሚሆን እይታ።

የአይን ህክምና ሰዎች የአይንን የማየት አቅምን ተመልክተው የእይታ ደረጃችን ላይ አስተያየት እንደሚሰጡ በአገራችን እየተገበርናቸው ባሉት ፖሊሲዎችና መሰል ተግባራት እይታችንን በመመርመር ወደ መፍትሔ መራመድ አለብን። ትንሿ ሳንቲም የገራደችውን ተራራ ተመልክቶ ወደ ተራራው የሚደረገውን ጉዞ ከማደናቀፍ በተራራው ስር ያለውን ሃብት አውጥቶ መጠቀም ተገቢነት እንዳለው አምኖ እይታን ማስተካከል።

በትንሿ ሳንቲም የሚወከል እይታችንን የጋረዱትን ነገሮች ለማንሳት ብንሞክር የምናገኛቸው እውነታዎች በዙሪያችን ያለውን ሁኔታ አግዝፈን በማየት አልቻልም ማለታችን፤ በዙሪያችን ያሉ ተስፋ አስቆራጭ ድምጾችን አድምጠን መቆማችን፤ ትላንት ሞክረው ያልተሳካለቸው ሰዎችን ምክር ሰምተን ከጉዞ መታቀባችን፤ ደጋግመን



አንኳኩተን ያልተከፈተውን በር አጥብቀን ከማንኳኳት መመለሳችን፤ ከእለት ወደ እለት እየደቀቀ ያለ ኢኮኖሚ የሚፈጥረው ተስፋቢስነት ህልማችንን እንደ ቅዠት መቁጠራችን ወዘተ ናቸው።

አንባቢው እንዲረዳው የሚያስፈልገው ነገር በመነሳሳት ወይንም በተቀጣጠለ ልብ ውስጥ አንዳች ነገር ለማሳካት የሚነሱ ሰዎች ተቀምጠው ተግዳሮትን ከሚያወሩ በየትኛውም መንገድ የተሻሉ መሆናቸው ነው። ዛሬ በልባችን ውስጥ ያለውን ድምጽ በሚገባ አድምጠን መሄድ ወደምንፈልገው አቅጣጫ መራመድ እንድንችል ከልብ መነሳሳት ያስፈልገናል። ከሁኔታው በላይ መራመድ የሚያስችለን አቅም ከውስጣችን ፈልገን ከፈጣሪ ጋር ለመነሳት የእይታ ምልከታችን ወሳኝነት አለው።

በእይታችን ልክ የምንወርሰውን ተራራ እንመልከት። ተራራው ግዙፍ ነው፤ ተራራው በመካከል ካለው የትኛውም ተግዳሮት በላይ ልናየው የተገባም ነው፤ ተራራው ላይ ደርሰን ከፍታውን በተቆጣጠርን ጊዜ አካባቢውን በሚገባ መቃኘት የምንችልበትም ስፍራ ነው።

**ከተራራው ማዶስ**

እይታውን ተራራው ላይ አድርጎ ጉዞን የጀመረ ሰው ከተራራው ጋር ሲደርስ ስኬቱን ያከብራል። በጉዞው የገጠሙትን ተግዳሮቶች እንዴት በድል እያሸነፈ እንደ ዘለቀ ከትዝታው ማህደር እያወጣ ደስታውን ያጣጥማል። ተራራው ጫፍ ጋር ደርሶ መቆም አንድ አመራጭ ሲሆን ሌላው አማራጭ ከተራራው ጫፍ ተነስቶ ሌላኛውን ተራራ ጫፍ መመልከት ነው። ወደ አዲስ ተራራ፤ ወደ በለጠው ከፍታ። ሁኔታ በተግባር ሕይወት ውስጥ ቀላል አይደለም፤ ነገር ግን የእይታ ሰዎች መገለጫ ነው።

በኢኮኖሚክሱ የሰው ልጅ ፍላጎት በቀላሉ የማይረካ መሆኑን እንረዳለን። በምድር ላይ ያለው ሃብት ውስን ቢሆንም የሰው ልጅ ፍላጎት ግን የሚቀጥል ነው። አንድ ሰው በሕይወት ጉዞ ውስጥ ራሱን ሲያገኝ ከአንድ ደረጃ ወደ ሌላ ደረጃ በሚያደርገው ጉዞ ውስጥ እሴትን መያዝ አለበት። ከአንድ ተራራ ወደ ሌላ ተራራ በጽናት የመጓዝ በስተመጨረሻም በአሸናፊነት ማማ ላይ ለመድረስ።

ከተራራው ማዶ ሌላኛውን ተራራ መመልከት ውስጥ ጽናት አለ። እይታን አጥርቶ የመጓዝ ጽናት። ልጆች ማሳደግ ምን ያህል አስቸጋሪ መሆኑን ልጆችን በማሳደግ ሕይወት ውስጥ ያለፉ ያውቁታል። ሰዎችን መምራት ምን ያህል አስቸጋሪ መሆኑን በመሪነት ውስጥ ያለፉ ሰዎች ይናገራሉ። አንዳንዱ ወደ ግራ እንሂድ ሲል ሌላው ወደ ቀኝ ሲል በመካከል በሚፈጠረው መሳሳብ አማካኝነት የሚሆን አስቸጋሪነት። ከተራራው ማዶ የሚያዩ ሰዎች የተግዳሮቱ ምንጭ ምንም ይሁን እያንዳንዱን ቀን በእሴት የተሞላን ኑሮን በመኖር ወደ ውጤት ይደርሳሉ።

በሕይወት ጉዞ ውስጥ ከአራቱም አቅጣጫ የሚመጣውን ተግዳሮት ተቋቁሞ ወደ ውጤት መድረስ እንዲቻል የእይታ ልክ ወሳኝነት አለው። ነገሮችን በልካቸው ማየት፤ ያየነውን ትልቁን ምስል ጠብቀን መራመድ፤ በብርቱ መነሳሳት።

ኢኮኖሚ

# ስኬት

# የሸንኮራ አገዳው ንግድ ጣፋጭ ፍሬዎች

**ፍሬሕይወት አወቀ**

የንግድ ሥራን ከተቀላቀሉ ከሁለት አስርት ዓመታት በላይ ሆኗቸዋል። ለሥራው ያላቸው ከፍተኛ ፍላጎት የሁለተኛ ደረጃ ትምህርታቸውን አቋርጠው ንግዱን እንዲቀላቀሉ አድርጓቸዋል። ‹‹ወጣትነት ትኩስ ኃይል ነው›› እንደሚባለው በድፍረትና በይቻላል ስሜት የ9ኛ ክፍል ትምህርታቸውን አቋርጠው የንግድ ሥራቸውን በሸንኮራ አገዳ አሀዱ ብለው ጀመሩ።

አፍላው የወጣትነት እድሜያቸው ከልብ ከመነጨው የንግድ ሥራ ፍላጎታቸው ጋር ተደምሮ የንግድን ጣዕም ለመለየት ጊዜ አልወሰደባቸውም። ሥራው በባህሪው ፈታኝና ውስብስብ ቢሆንም፣ የሸንኮራ አገዳ ንግዳቸው እንደ ሸንኮራው ጣዕም ጣፋጭ ሆነላቸው። በሸንኮራ አገዳ ንግድ ጀምረው በንግዱ ዘርፍ ስኬታማ ለመሆን የበቁት የዛሬው የስኬት አምድ እንግዳችን አቶ ዲና ገዛኸኝ፣ የዲና ኢንቨስትመንት ግሩፕ ኃላፊነቱ የተወሰነ የግል ድርጅት መስራችና ባለቤት ናቸው።

አቶ ዲና፤ ተማሪ እያሉ ጀምሮ ለንግድ ሥራ ልዩ ምልከታ እንደነበራቸው ያስታውሳሉ። በሸንኮራ አገዳ የጀመሩትን የንግድ ሥራ በወጉ መምራትና ማጣጣም በመቻላቸው ዛሬ በተለያዩ የንግድ ዘርፎች በመሰማራት ስኬታማ መሆን ችለዋል። የሸንኮራ አገዳ ንግዱ የወለዳቸው የንግድ ስራዎች አንዱ ሌላውን እየወለደ የተለያዩ የንግድ ሥራዎችን በቀላሉ ማቀላጠፍ እንዲችሉ በር እንደከፈተላቸውም ይናገራሉ።

በኦሮሚያ ክልል በቀድሞ አጠራሩ ባሌ ክፍለ ሀገር ጋሰራ ወረዳ ሸለል በምትባል ቀበሌ ገበሬ ማህበር ተወልደው ያደጉት አቶ ዲና፤ በአካባቢያቸው ከሚዘወተሩ ትናንሽና ትላልቅ የንግድ አይነቶች መካከል የሰንጋ ንግድ አንዱ እንደነበር ያስታውሳሉ። በወቅቱም በርካታ የጋሰራ ወረዳ ሰዎች በሰንጋ ንግድ ይታወቁ ነበር። ይህ ብቻ አይደለም፤ በሰንጋ ንግድ ዘርፍ የተሰማሩ ግለሰቦች በማህበረሰቡ ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው፤ አንቱ የተባሉና በትክክለኛው የሕይወት መስመር ውስጥ ያሉ ስለመሆናቸውም ይታመን ነበር። እንደ አብዛኞቹ የአካባቢው ማህበረሰብ አባላት አመለካከት እርሳቸውም ለሰንጋ ነጋዴዎች ልዩ ምልከታ ነበራቸውና ልባቸው ሰንጋ ነጋዴ መሆንን አጥብቆ ተመኘ።

ምኞታቸውን እውን ለማድረግ ጊዜ ያልፈጁት አቶ ዲና፤ በሸንኮራ አገዳ ያጣጣሙትን ንግድ በአካባቢው ትልቅ ቦታ በሚሰጠው የሰንጋ ንግድ ሊደግሙት አሁንም አሀዱ ብለው ተነሱ። ይሁንና ሸንኮራ አገዳ ቸርችረው ያጠራቀሟት ትርፍ ሰንጋ መግዛት አልቻለችም፤ በዚህ ተስፋ አልቆረጡም፤ ወደ ሰንጋ ንግድ ሊያሸጋግረኝ ይችላል ያሉትን የበግና ፍየል ንግድ ጀመሩ። ‹‹ቀስ በቀስ እንቁላል በእግሩ ይሄዳል›› እንዲሉ ሆነና ይህ የበግና ፍየል ንግዳቸው ውጤታማ ሆነና በሕይወታቸው ትልቅ ቦታ የሰጡትን የሰንጋ ንግድ መጀመር አስቻላቸው። በወቅቱ እርሳቸውን ጨምሮ የአካባቢው ማህበረሰብ በሙሉ ትልቅ ግምት በሰጠው የሰንጋ ንግድ ሲሰማሩ የተሰማቸው ደስታ ጥልቅ እንደነበር ያስታውሳሉ።

ወደ ሰንጋ ንግድ ያደሉት አቶ ዲና፤ ጥቂት የማይባሉ ውጣ ውረዶችን አልፈው እንዳሰቡት ሁሉ በሰንጋ ንግድም ውጤታማ መሆን ችለዋል። በአንድ ሺ 520 ብር መነሻ ካፒታል የተጀመረው የሰንጋ ንግድ በብዙ ትጋት፣ ጥረትና ቁርጠኝነት የስንዴ ዱቄት ንግድን ጨምሮ ወጪ ገቢ ንግድንም ማዋለድ አስቻላቸው።

አቶ ዲና፤ የመጀመሪያውን የቁም እንስሳት ንግዳቸውን የጀመሩት በአካባቢያቸው እጅግ የተጎዱ ከብቶችን ከአርሶ አደሮች በመግዛት ነበር። በወቅቱ የገዟቸውን ሰባት ከብቶች ጥሩ ጥሩ መኖ በማቅረብ ነብስ ዘሩባቸውና የሰንጋ ንግዱን ተያያዙት። በወቅቱም ያ ጅምራቸው ትርጉም ያለው ለውጥ ሊያመጣ እንደሚችል ይታያቸው ነበር። ሰባቱን የደለቡ ከብቶች ይዘው ከሰላሌ ወደ አዳማ እጅግ አድካሚና አሰልቺ ጉዞ አድርገዋል።

ያኔ ሰንጋ የሚሸጠው አዳማ እንደነበር በማስታወስ ከብቶቹን እየነዱ ከሰኞ እስከ ሰኞ ይጓዙ እንደነበር ያስታወሱት አቶ ዲና፤ ጉዞው በእግርም በመኪናም እንደነበርም አጫውተውናል። ከሰላሌ አዳማ በትንሹ 330 ኪሎ ሜትር የሚያህለውን መንገድ በብዙ ትጋትና ጥልቅ ፍላጎት ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ተመላልሰው ነግደዋል። እጅጉን የሚመኙትንና የታላላቅ ሰዎች መለኪያ ነው ብለው ያመኑትን የቁም እንስሳት ንግድ መጀመር በመቻላቸው እጅግ ደስተኛ የነበሩት አቶ ዲና፤ ያሳለፉት ውጣ ውረድ ይበልጥ ብርታት ሆኗቸዋል።

ጥልቅ በሆነ ጉጉትና በከፍተኛ ድካም ለአንድ ዓመት ተኩል ያህል ተመላልሰው የነገዱት አቶ ዲና፤ ከአንድ አመት አጋማሽ በኋላ ለእንስሳት ንግዱ ምቹ በሆነችው አዳማ ከተሙ። ለሥራው በነበራቸው ከፍተኛ ጉጉት ተግተው መሥራት በመቻላቸው በወቅቱ ጥሩ ከብት አድላቢ ከሚባሉት ተርታ መሰለፍ ችለዋል። የእንስሳት ቁጥሩንም ከጊዜ ወደ ጊዜ በማበራከት 20፣ 30፣ 40 እያሉ ጥሩና ቀዳሚ የቁም እንስሳት ነጋዴ መሆን ችለዋል።

ንግድ ማለት ምን እንደሆነ የተረዱት አቶ ዲና፤ የሥራ ዘርፋቸውን በማስፋት ከቁም እንስሳት ንግድ ጎን ለጎን የእንስሳት መኖ አቅራቢ ሆኑ። ከራሳቸው አልፈው ለሌሎች ከብት አድላቢዎች የእንስሳት መኖ በማቅረብም ቀዳሚ የእንስሳት መኖ አቅራቢ ሆነዋል። በወቅቱ የቁም እንስሳት ንግዳቸው ጠንካራ መሰረት የጣለ በመሆኑ ለላኪዎች ያቀርቡ የነበረውን የቁም እንስሳት እርሳቸው በቀጥታ ወደ ውጭ ገበያ ማቅረብ ጀመሩ። በወቅቱም በአገሪቱ አሉ ከሚባሉ የቁም እንስሳት ላኪዎች መካከል አንዱ እርሳቸው እንደነበሩም ያስታውሳሉ።

የቁም እንስሳት ንግዱን አጠናክረው በመቀጠልም የውጭ ገበያውን በስፋት የመተዋወቅ ዕድል አገኙ። የተለያዩ ምርቶችን ወደ አገር ውስጥ በማስገባት የገቢ ንግዱንም መተዋወቅ ቻሉ። ወደ አገር ውስጥ ያስመጧቸው ከነበሩ ምርቶች መካከልም መኪና፣ የመኪና መለዋወጫና ሌሎችም ይገኙበታል። የወጪና ገቢ ንግዱን መስመር ማስያዝና ማጠናከር የቻሉት አቶ ዲና፣ ሌላ የንግድ ዘርፍ ማማተርን ደሞ ተያይዙት። የንግድ ዘርፉን በማጥናት ትኩረታቸውን ወደ ማኑፋክቸሪንግ በማድረግ ዲና የምግብ ማቀነባበሪያ ድርጅትን አቋቋሙ። ድርጅቱ የተቋቋመው የስንዴ ዱቄትን ጨምሮ ፓስታ፣ ማካሮኒና ብስኩቶችን ለማምረት ቢሆንም፣ ለጊዜው ዱቄት ብቻ እያመረተ ይገኛል።

ዲና የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ በአዋሽ መልካሳ በ70 ሺ ካሬ ሜትር ስፋት ላይ ያረፈ ሲሆን፤ አራት የተለያዩ ዘመናዊ ማሽኖችንም ይዟል። ከአራቱ ማሽኖች መካከልም ሁለቱ ስንዴ የሚፈጩ ሲሆን፣ ቀሪዎቹ ደግሞ በቆሎና ጤፍ መፍጨት የሚችሉ ናቸው።

‹‹ወደ ማኑፋክቸሪንግ ዘርፍ የተሰማራሁት የቁም እንስሳት የወጪ ንግዱ እጅግ ፈታኝና ለኮንትሮባንድ የተጋለጠ በመሆኑ ነው›› የሚሉት አቶ ዲና፤ ለእንስሳት ልዩ ክብር ያላቸው በመሆናቸው ብቻ በርካታ ውጣ ውረዶችን እየታገሉ ላለፉት አስር ዓመታት ቀዳሚ ከሆኑት የቁም እንስሳት ላኪዎች መካከል አንዱ ሆነው ቆይተዋል።

ዘርፉ አሁንም ድረስ እጅግ ፈታኝ ችግሮች እንዳሉበት በመጥቀስ፣ የአገሪቱን የቁም እንስሳት ከአረብ አገራት ባለፈ ለአውሮፓ ገበያ ማቅረብ እንዳልተቻለ ይጠቁማሉ። አውሮፓውያኑ በሚፈልጉት ደረጃ እንስሳቱን ማቅረብ ባለመቻሉ ገበያው በአረብ አገራት ብቻ ተወስኗል የሚሉት አቶ ዲና፣ በአረብ አገራት ያለው የገበያ ሁኔታም በኮንትሮባንድ የተዋጠ መሆኑን ይገልጻሉ። የአረብ ሀገሮች እንስሳቱ በህጋዊ መንገድም ሆነ በኮንትሮባንድ መቅረባቸው ግድ የማይሰጣቸውና ሚዛን ውስጥ የማያስገቡ መሆናቸውን ይናገራሉ። የኮንትሮባንድ ንግዱ በህጋዊ መንገድ የሚነግደውን ነጋዴ ከማዳከም አልፎ እያሸነፈው መሆኑን ጠቅሰው፣ እሳቸው ሌሎች አማራጮችን ማሰብ እንዳስፈለጋቸው



አቶ ዲና ገዛኸኝ

ነው ያጫወቱን።

አቶ ዲና የቁም እንስሳት ንግዱ እጅጉን የፈተናቸው ቢሆንም፣ ከእንስሳቱ መለየት አልፈቀዱም። ስለእንስሳት ንግዱና እንስሳት በቂ ግንዛቤ ያላቸው በመሆናቸው ዘርፉን በማስፋት ስጋ ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ እየተዘጋጁ ስለመሆናቸው ይጠቁማሉ። እንስሳት እያረቡ፣ እያደለቡ እሴት ጨምረው ስጋ ለውጭ ገበያ ለማቅረብ በዝግጅት ላይ ናቸው፤ በአሁኑ ወቅትም ቄራ እየገነቡ መሆናቸውን ይገልፃሉ።

የእንስሳት መኖ አቅራቢ እንደመሆናቸውም ቃሊቲ ላይ በቀን 120 ቶን ወይም አንድ ሺ 200 ኩንታል የማምረት አቅም ያለው የእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ ገንብተዋል። ከእርሳቸው ባለፈም የእንስሳት መኖን ለሌሎች ያቀርባሉ።

እንደ አገር በቁም እንስሳት ከፍተኛ መጠን ያለው የውጭ ምንዛሬ ማስገኘት ይቻላል የሚሉት አቶ ዲና፤ መንግሥት በዘርፉ ያለውን ችግር ለመፍታት በተለያየ ጊዜ ጥረት ሲያደርግ እንደነበር ያስታውሳሉ። ህገወጥ ንግዱ መቶ በመቶ ገበያውን ተቆጣጥሮት መቆየቱ ጠቅሰው፣ ችግሩን ለመፍታት ቀላል አልሆነም ይላሉ። አሁን ባለው የገበያ ሁኔታም እንስሳቱን በቁሙ ለውጭ ገበያ ከመላክ ይልቅ ስጋውን መላክ የተሻለ እንደሆነ በማመን ነው ቄራ ወደ ማቋቋም የገቡት።

የቁም እንስሳት ንግድ በአግባቡ መመራት ከቻለ ለአገሪቱ ከፍተኛ የዶላር ምንጭ መሆን እንደሚችል ጠቅሰው፣ መንግሥት ለዘርፉ ትልቅ ትኩረት ሊሰጠው እንደሚገባም ያስገነዝባሉ። በተለይም ህገወጥ የቁም እንስሳት ንግድን ለመቆጣጠር መንግሥት የተለያዩ አማራጮችን መከተል እንዳለበት ይጠቁማሉ።

እንደ አቶ ዲና ገለጻ፤ በቁጥጥሩ ሂደት አንደኛ ህገወጥ ንግድ አገርን የሚጎዳ ስለመሆኑ ግንዛቤ መፍጠር ያስፈልጋል፤ ሁለተኛ የእንስሳቱን እንቅስቃሴ መገደብና መከታተል፤ ሶስተኛ የቁጥጥርና የክትትል ስርዓቱን ዘመናዊ በማድረግ ህገወጦችን ከመስመር ማስወጣት ይገባል። ይህን ማድረግ ሲቻል አገሪቷ ከዘርፉ ማግኘት የሚገባትን ጥቅም እንድታገኝ ያስችላል።

በቀን 2000 ኩንታል የስንዴ ዱቄት በሚያመርተው ዲና የምግብ ማቀነባበሪያ ፋብሪካ፣ በእንስሳት እርባታና ማደለብ እንዲሁም በእንስሳት መኖ ማቀነባበሪያው በድምሩ ለ333 ዜጎች የሥራ ዕድል የፈጠሩት አቶ ዲና፤ በቀጣይም ይህን ቁጥር ለማሳደግ እየሠሩ መሆናቸውን ይገልጻሉ።

ማህበራዊ ኃላፊነትን በመወጣት በአሁኑ ወቅት በአዋሽ መልካሳ አካባቢ ደረጃውን የጠበቀ ትልቅ ትምህርት ቤት እያስገነቡ ይገኛሉ። ከዚህ ባለፈም በተለያዩ ችግሮች ውስጥ ለሚገኙ የማህበረሰብ ክፍሎች ቁሳዊና የገንዘብ ድጋፍ የሚያደርጉት አቶ ዲና፤ በተለይም መንግሥት ለሚያቀርባቸው ማንኛውም ጥሪዎች ምላሽ ለመስጠት ወደኋላ የማይሉ መሆናቸውን ይናገራሉ። በዚህም የተለያዩ የምስክር ወረቀቶችን አግኝተዋል።

በቀጣይም የተጀማመሩ ሥራዎችን ከፍጻሜ ለማድረስ እተጋለሁ የሚሉት አቶ ዲና፤ በተለይም ከብቶችን ከማርባትና ከማደለብ ከፍ በማለት ስጋ ወደ ውጭ ገበያ ለመላክ እንዲሁም ስንዴን ከዱቄት ባለፈ ወደ ፓስታ፣ ማካሮኒና ብስኩት ማሳደግ እና የጤፍና የበቆሎ ዱቄትንም እንዲሁ እሴት በመጨመር ለማምረት አቅደው እየሰሩ ይገኛሉ። በሆቴል ኢንቨስትመንት ለመሳተፍ ፍላጎትና ዝግጁነት እንዳላቸውም ይናገራሉ።

‹‹በንግድ ሥራ ውስጥ እጅግ ፈታኝ የነበሩ ወቅቶችን በመቋቋም ዓላማዬን ማሳካት ችያለሁ›› የሚሉት አቶ ዲና፤ ማንም ሰው ጠንካራ፣ ታታሪና ትጉህ ከሆነ ምንም ነገር ቢጎረብጠው የተነሳበትን ዓላማ ማሳካት ይችላል በማለት ሃሳባቸውን ቋጭተዋል።

ኢኮኖሚ

# መሠረተ ልማት

## የብረታ ብረት እጥረት - የኮንስትራክሽን ዘርፉ ፈተና

መላኩ ኤሮሴ

የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪ ዘርፈ ብዙ ፋይዳ ያለው ዘርፍ ነው። ይህ ዘርፍ የኢኮኖሚ እና የማህበራዊ መሰረተ ልማት አውታሮች፣ ፋብሪካዎች እና መኖሪያ ቤቶችን በመገንባት እንዲሁም ሰፊ የሥራ እድል በመፍጠር ለአገሪቷ ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የጎላ ድርሻ እንዳለው ይታወቃል። ኢንዱስትሪው ከግብርና ቀጥሎ ከፍተኛውን የሰው ሀይል የያዘና ለሌሎች ተያያዥ ዘርፎች ዋነኛው አንቀሳቃሽ ነው። በከተሞች የሰው ሀይል በመቅጠር ረገድ ከሆቴል እና ሬስቶራንት ቀጥሎ ከፍተኛውን ቦታ የያዘ ዘርፍ ስለመሆኑም መረጃዎች ያሳያሉ።

ከፌዴራል መንግሥት ካፒታል በጀት ውስጥ ከ55 እስከ 60 በመቶ የሚሆነው ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው እንደሚውል መረጃዎች ይጠቁማሉ። ዘርፉ ከእያንዳንዱ ዜጋ የዕለተ ተዕለት ሕይወት ጋር በከፍተኛ ሁኔታ የተቆራኘ መሆኑን ከላይ የተጠቀሱ መረጃዎች አመላካች ናቸው።

ይህ ዘርፍ ካለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ስር የሰደዱ ህመሞች አጋጥመውታል። በግንባታ ግብዓቶች እጥረት ምክንያት የኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ከባድ ችግር ውስጥ ወድቋል። በግንባታ ግብዓቶች ላይ የተፈጠረው ችግር ዘርፉን ከመጉዳት ባሻገር በማህበራዊ እና ኢኮኖሚያዊ ልማቶች ላይም የራሱ የሆነ አሉታዊ ጫና አሳድሯል። ከከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር የተገኙ መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ በኮንስትራክሽን ግብዓት እጥረት ምክንያት በርካታ ፕሮጀክቶች እየተጓተቱ ይገኛሉ፤ የተቋረጡም አሉ።

በኮንስትራክሽን ዘርፉ ላይ ከፍተኛ ጫና እያሳደሩ ካሉት የግብዓት ችግሮች መካከል አንዱ የብረት እጥረት ነው። ለኮንስትራክሽን ሥራ ከፍተኛውን ድርሻ ከሚይዙት መካከል ብረት አንዱ ነው። የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር መረጃዎች እንደሚያሳዩት፤ እስከ 2013 ዓ.ም ድረስ 13 የብረት ፋብሪካዎች ነበሩ። ሆኖም በነዚህ ፋብሪካዎች የሚመረተው የብረት ምርት የዘርፉን ፍላጎት ሊያሟላ አይችልም።

በቅርቡ በኮንስትራክሽን ዘርፍ በሚስተዋሉ ችግሮች ዙሪያ በተካሄደው አውደ ጥናት ላይ ከፍተኛ ትኩረት ከተሰጣቸው ጉዳዮች አንዱ የመሰረታዊ ብረታ ብረት ጉዳይ ነው። በኮንስትራክሽን ግብዓቶች ዙሪያ የተካሄደ የጥናት ውጤት ያቀረቡት አቶ ዘሪሁን ዘገየ እንደሚሉት፤ መሰረታዊ ብረታ ብረት ፌሮ፣ የቤት ክዳን ቆርቆሮ የስቲል ቱቦላሪ እና የመሳሰሉትን ያካትታል።

በኢትዮጵያ ውስጥ የሚገኙ 13ቱ ፋብሪካዎች እያመረቱ ያሉት በዓመት ከሚጠበቅባቸው የብረት ምርት ውስጥ ስምንት በመቶውን ብቻ እንደሆነ ያብራራሉ። ይህም ከፍተኛ የብረት ምርት እጥረት መኖሩን ያመለክታል። አሁን ባለው ወቅታዊ መረጃ መሰረት የአርማታ ብረት ፍላጎት ከፍተኛ ቢሆንም፣ የብረት ኢንዱስትሪዎች እያመረቱ ያሉት በጣም አነስተኛ ነው። ከምርት አቅርቦት እጥረት ጋር ተያይዞ ከፍተኛ የብረት ዋጋ መናር ይስተዋላል። የዋጋ ንረቱ እየተባባሰ በመምጣቱም በኮንስትራክሽን ዘርፉ ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ እያሳደረ ነው።

በአገር ውስጥ የሚመረተው ብረት ከፍላጎት ጋር የማይመጣጠን በመሆኑ ከፍተኛ መጠን ያለው ብረት ከውጭ አገራት ይገባል። በዚህ ምክንያት አገሪቱ ካላት የውጭ ምንዛሬ ውስጥ ቀላል የማይባለው መጠን ለብረት ግዥ እንደሚወጣ ይናገራሉ። በዓመት ከአንድ ቢሊየን ዶላር በላይ የውጭ ምንዛሬ ለብረት ግዥ እየወጣ እንደሚገኝም ጠቁመው፣ ስለዚህ ብረት ወደ አገር ውስጥ ለማስገባት የሚወጣውን የውጭ ምንዛሬ ማዳን ቢቻል ብዙ ተቋርጠው ያሉ ፕሮጀክቶችን የማስጨረስ አቅም መፍጠር ይቻላል። በዚህ ረገድ ሰፊ የቤት ሥራ እንደሚጠበቅ ችግሮቹ ያመላክታሉ ሲሉ ያብራራሉ።

አቶ ዘሪሁን እንደሚያብራሩት፤ የብረት እጥረት እንዲከሰት የተለያዩ ተግዳሮቶች በምክንያትነት ይጠቀሳሉ። ከእነዚህ ተግዳሮቶች መካከል የብረት ፋብሪካዎች የሚጠቀሟቸው ጥሬ እቃዎች ከውጭ አገራት የሚያስገቡ በመሆኑ ነው። የብረት ፋብሪካዎቹ ብረትን ለማምረት 85 በመቶው የሚሆነውን ግብዓት ከውጭ አገራት ያስገባሉ። ከውጭ የሚገባው ጠገራ ብረት ከፍተኛ የውጭ ምንዛሬን ይጠይቃል፤ በመሆኑም ፋብሪካዎች



ብረት በሚፈልጉት መጠን ለማግኘት ይቸገራሉ። ችግሩ ፋብሪካዎች በሙሉ አቅማቸው እንዳያመርቱ እንቅፋት ሆኗል።

በአገር ውስጥ ቁርጥራጭ ብረቶችን አቅልጦ ብረት የመስራት ጅምር ሥራዎች ቢኖሩም ቁርጥራጮቹ የሚሰበሰቡበት መንገድ ችግር ያለበት ነው። በብልሹ አሰራሮች የተሞላ ነው። ቁርጥራጩ በአግባቡ ለአምራቾች በተመጣጣኝ ዋጋ እየቀረበ አይደለም። በአቅራቢዎች እና በአምራቾች መካከል ጤናማ ያልሆነ የገበያ ትስስር አለመኖር ችግሩን አባብሶታል ሲሉ አቶ ዘርይሁን ያብራራሉ።

አቶ ዘሪሁን በብረት ፋብሪካዎች ላይ የሚደርሰው የኃይል አቅርቦት መቆራረጥም ሌላው የዘርፉ ተግዳሮት መሆኑን ጠቅሰዋል፤ የኃይል መቆራረጡ የፋብሪካዎቹን የማምረት አቅም ከመፈታተኑም ባሻገር በብዙ የውጭ ምንዛሬ የተገዙ ማሽነሪዎችን ለብልሽት እየዳረገ እንደሚገኝ ነው የጠቆሙት። ዘርፉን ከተግዳሮቶች ለማላቀቅ የፋብሪካዎቹን የኃይል እጥረት ችግር መቅረፍ ወሳኝ ነው ይላሉ።

ጥናት አቅራቢው እንደሚሉት፤ በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል በበቂ ሁኔታ አለመኖር፣ በቂ የፋይናንስ አቅርቦት ያለመኖር፣ የፋይናንስ ስርዓት ወጥነት የጎደለው መሆንና የተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት አለመኖሩ እንደ ዋና ችግር ይጠቀሳል።

ችግሩን ለመቅረፍ የአጭር የረጅም እና የመካከለኛ ጊዜ እቅዶችን ነድፎ መንቀሳቀስ አስፈላጊ መሆኑን አቶ ዘርይሁን ይጠቁማሉ። ችግሩን በአጭር ጊዜ ለማቃለል የግንባታ ፕሮጀክትን ነባራዊ ሁኔታ መሰረት በማድረግ ለአንድ ህንጻ ወይም ግንባታ ፕሮጀክት የሚያስፈልግ የብረት መጠን በማፅቀፍ ግዥ ለፕሮጀክቱ ተደራሽ እንዲሆን ማስቻል ያስፈልጋል ይላሉ።

በአገሪቱ ያለውን የውጭ ምንዛሬ እጥረትን ያገናዘበ መሰረታዊ የብረታ ብረት ስትራቴጂክ ምርቶች የውጭ ምንዛሬ እንዲመደብ ትኩረት እንዲሰጠው ማድረግ፣ ህገ ወጥ ንግድ እና ኮንትሮባንድ ንግድን ለመከላከል የተለያዩ ዘመናዊ ስልቶችን መዘርጋት፣ በአገር ውስጥ ያለው የማዕድን ክምችት መሰረት በማድረግ የጥሬ ብረት ማዕድን ልማት ሥራን ወደ ትግበራ ለማስገባት ከክልል መስተዳደር፣ ከፋይናንስ እና ከማዕድን ሚኒስቴር ጋር በቅንጅት መስራት ያስፈልጋል ሲሉም አቶ ዘሪሁን ያስገነዝባሉ።

እንደ እሳቸው ገለጻ፤ ብረትን ጨምሮ ሌሎች የኮንስትራክሽን ግብዓቶች ጥራትና ምርታማነትን ማሳደግ፣ ከውጭ አገራት የሚገባውን በአገር ውስጥ መተካት፣ የገበያ ትስስር እንዲፈጠር ጥረት ማድረግ፣ ግብይቱ በአገር ውስጥ የግንባታ የገበያ ትስስር ውስጥ እንዲካተት ማድረግ ዘርፉን ካለበት ችግር ለማላቀቅ ተጨማሪ መፍትሄዎች ናቸው።

ባለፈው ዓመት የአማካሪዎች የሥራ መመሪያን ሚኒስቴር መስሪያ ቤት ማጸደቁን ያስታወሱት አቶ ዘሪሁን፣ በዚህ ውስጥ ከተቀመጡት መካከል በስፔስፊኬሽን ውስጥ የአገር ውስጥ ምርቶች መጠቀስ አለባቸው የሚል ተካቶበታል። የአገር ውስጥ ምርቶች ካልተጠቀሱ ስፔስፊኬሽኑ ውድቅ መሆን አለበት። ይህ የአገር ውስጥ የብረት ምርትን ለማበረታታት ከተያዙ አቅጣጫዎች አንዱ ነው።

ምርቶቹ በአገር ውስጥ የማይመረቱ እና ሊገኙ የማይችሉ ከሆኑ ብቻ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ እውቅና ሲሰጠው ብቻ ከውጭ በመጠን ምርት መስራት ይቻላል የሚል መመሪያ ውስጥ እንዲካተት ተደርጓል። በእነዚህ ህጎች ዙሪያ ለኮንትራክተር እና ኮንሰልታንት ሰፊ ግንዛቤ ተሰጥቶ ወደ ውጭ የሚወጣውን የዶላር ፍሰት መቀነስ ይቻላል፣ የአገር ውስጥ ምርትም ማበረታታት ይቻላል ተብሎ ተስፋ ተጥሎበታል።

የአገር ውስጥ ምርት ሲበረታታ ፋብሪካዎቹ ስለሚጠናከሩ የግንባታ ማጠናቀቂያ ችግሮችን ከመቅረፍ ባሻገር የሥራ እድል መፍጠርም ያስችላል። አሁንም ለእነዚህ ሥራዎች ተገቢው ትኩረት ተሰጥቶ መሰራት አለበት። ለተፈጻሚነቱም ሁሉም አካል ርብርብ ማድረግ ይጠበቅበታል።

በዚህ ዘርፍ የሚስተዋለው ሌላኛው ችግር የቴክኖሎጂ ሽግግር ችግር ነው። በዘርፍ ያሉ ማሽነሪዎችን የሚያንቀሳቅስ የሰለጠነ በቂ የሰው ኃይል እጥረትን ለመፍታት የውጭ እና የአገር ውስጥ አምራቾች በጆይንት ቬንቸር የሚሰሩበት መመሪያ ወጥቷል። በዘርፉ የሰለጠነ የሰው ኃይል ለማግኘት፣ ቴክኖሎጂ ለማሸጋገር ጆይንት ቬንቸር ወሳኝ ነው። ከውጭ የሚመጡ ኩባንያዎች ቴክኖሎጂውን የማምጣት እድል አላቸው፣ አገር ውስጥ ያለው ደግሞ የራሱን ማምረቻ መሰረተ ልማቶችን ማቅረብ ይችላል። ሁለቱ በመተጋገዝ ምርትን ማሳደግ ይችላሉ። ይህን ማድረግ ከተቻለ በአሁኑ ወቅት በተለያዩ ምክንያቶች ሥራ ያቆሙ የብረት ፋብሪካዎችን ጨምሮ ሌሎች የግንባታ የማጠናቀቂያ እቃዎች ማምረቻ ፋብሪካዎችን ወደ ምርት ማስገባት ይቻላል ሲሉ አመልክተዋል።

ዘርፉን እያጋጠሙ ያሉ ቁልፍ ችግሮችን ለመቅረፍ መወሰድ ካለባቸው ቁልፍ የተለያዩ የመፍትሄ እርምጃዎች መካከል ብረታ ብረት የሚገኝባቸውን የመንግሥት ድርጅቶችን በመለየት ያገለገሉ ብረታ ብረቶች ለአምራች ኢንዱስትሪዎች እንዲሰራጩ የሚደረግበት አሰራር መዘርጋት ችግሩን ለመቅረፍ ቁልፍ አማራጭ መሆኑን አቶ ዘሪሁን ጠቁመዋል።

የከተማና መሰረተ ልማት ሚኒስትር ዴኤታ ኢንጂነር ወንድሙ ሴታ ጉዳዩን አስመልክቶ በቅርቡ ከኢፕድ ጋር በነበራቸው ቃለ ምልልስ፤ በአገሪቱ ያሉትን ቁርጥራጭ ብረቶችን በመሰብሰብ ለነዚህ ፋብሪካዎች ግብዓት እንዲሆኑ በማቅረብ ፋብሪካዎቹ እያጋጠማቸው ያለውን የግብዓት ችግር ለመቅረፍ ጥረት እየተደረገ መሆኑን ጠቁመዋል። ጥረቱ ተጠናክሮ የሚቀጥል እንደሆነም አረጋግጠዋል።

ለፋብሪካዎች የብድር አቅርቦትን ማመቻቸት፣ ፋብሪካዎች የአቅማቸውን ያህል እንዲያመርቱ ድጋፍና ክትትል ማድረግ፣ የብረት ፋብሪካዎችን ጨምሮ ሌሎች የግንባታ ግብዓት አምራች ፋብሪካዎች ወደሥራ ሲገቡ እናመርታለን ብለው ያስቀመጡትን እቅድ ያህል እያመረቱ ነው ወይስ አይደለም በሚለው ላይ ጥብቅ ክትትል ማድረግ ያስፈልጋል ሲሉ አስገነዝበዋል። እያመረቱ ካልሆነ ደግሞ ማምረት ያልቻሉበትን ምክንያት እንዲያቀርቡ ማድረግ አስፈላጊ ነው ብለዋል።

ከመድረኩ ተሳታፊዎች እንደተጠቆመው፤ ዘርፍን በሚመለከት ከዚህ በፊት የነበሩ ህጎችን ማስፈጸም ያስፈልጋል። ህጎቹ እንዳይፈጸሙ የሚያደርጉ ችግሮች ካሉ መፈተሽ አለበት። የግንዛቤ ችግር ካለ የግንዛቤ ችግር መፈታት አለበት። በግንባታ ዘርፍ ውስጥ በሚሳተፉ አካላት ላይ የግንዛቤ የማሳደግ ስራዎች ከተሰሩ ችግሩን ማለፍ ይቻላል። ችግር ፈቺ አዳዲስ ህጎችን እስከ ማውጣትም መሄድ ያስፈልጋል።

ለኢትዮጵያ የፋይናንስ ስርዓት ወጥ እና የተጠናከረ የቁጥጥር ስርዓት ማበጀት፣ የኮንስትራክሽን ዘርፍ ችግር የሚፈቱ የምርምር እና የጥናት ተቋማትን ማጠናከር፣ የአገር ውስጥ ምርትን ለማበረታታት እየተሰሩ ያሉ ጥናቶችን መደገፍ ከተቻለ ዘርፉ አሁን ካለበት አስቸጋሪ ሁኔታ ከመውጣት ባሻገር ኢኮኖሚውን የማረጋጋት እድል ይፈጠራል።

የመድረኩ ተሳፊዎች እንዳሉት፤ በፖሊሲ የተደገፉ የኮንስትራክሽን ዘርፍን የሚደግፉ የተለያዩ የፋይናንስ አማራጮችን ማመቻቸት ያስፈልጋል። በአሁኑ ወቅት ለኮንስትራክሽን ኢንዱስትሪው ዋና ችግር እየሆነ ያለው የፋይናንስ አማራጭ እጦት ነው። የኮንስትራክሽን ዘርፉን ለመደገፍ አማራጭ የፋይናንስ ተቋማት መኖር አለባቸው። በኮንስትራክሽን ዘርፍ ያሉ ማሽነሪዎችን ሊዝ ማድረግ የዘርፉን ችግር ይፈታል። ነገር ግን በአሁኑ ወቅት የልማት ባንክ ሊዝ ፋይናንስ እየሰራ ያለው በግብርና ዘርፍ ብቻ ነው።

በአጠቃላይ በአገሪቱ ውስጥ እየተመዘገበ ያለው የኢኮኖሚ እድገት አስተማማኝ እና ቀጣይነት ያለው ለማድረግ የግንባታ ሥራዎች በታቀደላቸው ጊዜ፣ ጥራትና ወጪ መጠናቀቅ እንዲችሉ ለግንባታ ወሳኝ የሆነው የግንባታ ብረቶች እና ሌሎች ግብዓቶች አቅርቦት ለማሳደግ መሥራት የሁሉንም ርብርብ ይጠይቃል፤ ሁሉም የበኩሉን ሊወጣ ይገባል። መንግሥት የብረትን ጨምሮ የሌሎች የግንባታ የግብዓት ችግሮችን ለመቅረፍ የእሳት ማጥፋት አይነት ሥራ ላይ መጠመድ የለበትም። ጥናት ላይ ተመስርቶ ችግሩን በመሰረታዊነት መቅረፍ የሚያስችሉ ርምጃዎችን መውሰድ አለበት። መንግሥት ምርት ማከፋፈል ላይ ትኩረት ከማድረግ ይልቅ በቂ ምርት እንዲመረት ምቹ ሁኔታ መፍጠር ይጠበቅበታል። በቂ ምርት እንዲኖር ከማስቻሉም ጎን ለጎን ገበያውን ለማረጋጋት የተለያዩ ርምጃዎችን መውሰዱን መቀጠል አለበት።

# ርዕሰ አንቀፅ

## የግብርናው ዘርፍ ስኬት የብሄራዊ ክብራችን ምንጭ ነው!

የኢትዮጵያ ኢኮኖሚ በግብርና ላይ የተመሰረተ ከመሆኑ አንጻር ዘርፉን ማዘመን ዋንኛ አገራዊ አጀንዳ ነው። ከዚህ በመነሳትም መንግስት ከለውጡ ማግስት ጀምሮ ለዘርፉ ተገቢውን ትኩረት በመስጠት ተስፋ ሰጭ ውጤቶችን በተጨባጭ ማስመዝገብ ከጀመረ ውሎ አድሯል ።

በአንድ በኩል የገበሬውን የአስተራረስ ስርአት በመለወጥ / ኩታ ገጠም የአስተራረስ ዘዴን በማላመድ /ምርታማነትን በማሳደግ በሌላ በኩል ፤ የመስኖ እርሻዎችን በማስፋት አገር እንደ አገር የምግብ እህል ፍላጎቷን ማሟላት በሚያስችላት አዲስ ጅማሬ ውስጥ ገብቷል።

ይህ አዲስ ጅማሬ በዘመናዊ ቴክኖሎጂዎች እንዲታገዝ ለማድረግ ለገበሬው ዘመናዊ የእርሻ መሳሪያዎችን /ትራክተሮችን እና ኮምባይነሮችን/ በብድር ከመስጠት ጀምሮ የምግብ እህል አምራች ለሆኑ ክልሎች እርሻ መሳሪያዎች በርዳታ እንዲደርሳቸው እያስቻለ ይገኛል ።

ከዚህም ባለፈ በምግብ እህል ምርት በብዙ ባልተሰራባቸው እንደ ሶማሌና አፋር ባሉ ክልሎች ትላልቅ የስንዴ ማሳዎችን በማዘጋጀት ወደ ስራ እንዲገቡ እየተሄደበት ያለው መንገድ በቀደመው ዘመን "ኢትዮጵያ የአፍሪካ የዳቦ ቅርጫ ነች " የሚለውን አባባል ለማስታወስና ተስፋ ለማድረግ ዕድል የፈጠረ ነው።

በረሃማ አካባቢዎችን በመስኖ የማልማቱና ምርታማ የማድረጉ የመንግስት ስትራቴጂ በአሁኑ ወቅት በስንዴው ዘርፍ ያስገኘው ስኬት ዓለም አቀፍ እውቅና ከማግኘት ባለፈ አገሪቱ የቱን ያህል ሕዝቦቿን መመገብ የሚያስችል እምቅ አቅም እንዳላት በቀላሉ ማሳየት ያስቻለ ተጨባጭ ክስተት ሆኗል።

ይህ ክስተት ባለፉት ሁለት ዓመታት አገር እንደ አገር ከገባችበት ችግርና ችግሩ ከፈጠረው ማህበራዊ ምስቅልቅል እንድትሻገር እንደ አንድ አቅም ሆኖ አገልግሏል፤ አቅሙን ቀድሞ መፍጠር ባይቻል ኖሮ ችግሩ የቱን ያህል ግዝፈት ሊኖረው እንደሚችል ለመገመት የሚከብድ አይሆንም።

ከደቡብ አፍሪካው የፕሪቶሪያው የሰላም ስምምነት ማግስት የዕለት ምግብ ችግር ውስጥ ያሉ የትግራይ ወገኖቻችንን ለመታደግ እየተደረገ ባለው አገራዊ ጥረት በዘርፉ የተመዘገበው ውጤት እያበረከተ ያለውን አስተዋጽኦ በነጻ ህሊና ለሚመለከት ደግሞ የዘርፉ ስኬት ምን ያህል ለአገራዊ መረጋጋቱ አቅም መሆን እንደቻለ ለመመስከር የሚከብደው አይሆንም ።

መንግስት የግብርናውን ዘርፍ ምርታማነት በማሳደግ አገራዊ ኢኮኖሚው የተሻለ አቅም እዲኖረው የጀመረው በፖሊሲ የተደገፈ አገራዊ ርብርብ በቀጣይ የሰላም ወቅቶች ከዚህ የተሻለ አህገራዊ ትሩፋት ይዞ ሊመጣ እንደሚችል ይታመናል።

በተለይም የግል ባለሀብቱ ከፍ ባሉ የሜካናይዝድ እርሻዎች የተሳታፊነቱ ድርሻ እያደገ ሲሄድ፤ ዘርፉ በተሻለ ቴክኖሎጂ እንዲበለጽግ ከማድረግ ባለፈ ለዜጎች ሰፊ የስራ እድል በመፍጠር ለአገሪቱ ኢኮኖሚ እድገት የሚኖረው ፋይዳ የላቀ ይሆናል።

ይህ የመንግስት የዘርፉን ምርታማነት የማሳደግ ጥረት " የሌማት ትሩፋት" በሚል መንግስት ከጀመረው አገራዊ ንቅናቄ ጋር ተቀናጅቶ ዜጎች ቢያንስ የዕለት የተመጣጠነ ምግባቸውን ማግኘት የሚችሉበትን የተሻለ እድል መፍጠር ያስችላል።

ከዚህ አልፎ ምርቶችን በብዛትና በጥራት ለውጪ ገበያ በማቅረብ ለተጀመረው አገራዊ ብልጽግና አቅም ሊሆን እንደሚችል ይታመናል። አሁን አሁን በስንዴ ላይ እየታየ ያለው ተስፋ ሰጭ እንቅስቃሴም ለዚህ ተጨባጭ ማሳያ ሊሆን ይችላል።

ዘርፉ በጀመረው ተስፋ ሰጭ መንገድ በስኬት እንዲጓዝ የዘርፉ ተዋንያን በተለይም የምርምር ተቋማት ዘመናዊ ቴክኖሎጂዎችን ጨምሮ የተሻሻሉና ምርታማነትን የሚያሳድጉ አሰራሮችን በምርምር ከማፍለቅ እና ከማለማመድ ጀምሮ ውጤታማነታቸውን በመከታተል የመንግስትን ጥረት ማገዝ ይጠበቅባቸዋል።

በቀደሙት ዘመናት የአገርን ገጽታ ሲያበላሽ የኖረውን በምግብ እህል አቅርቦት ራስን ያለመቻል ፈተና በአሸናፊነት ለመወጣትና በዚህ ምክንያት የተበላሸውን አገራዊ ገጽታችንን ለማደስ ሁሉም ዜጋ ለዘርፉ ስኬት በተቻለው ሁሉ ሊንቀሳቀስ ይገባል!


# አዲስ ዘመን

ግንቦት 30 ቀን 1933 ዓ.ም ተቋቋመ

**የኢትዮጵያ ፕሬስ ድርጅት ዋና ስራ አስኪያጅ**

ስልክ ቁጥር - 011-126-42-22

**ዋና አዘጋጅ**

አንተነህ ኃ/ብርሃን ወ/መድህን

**አድራሻ**

ንፋስ ስልክ ላፍቶ ክ/ከ

ወረዳ 06

የቤት ቁጥር 319

ኢሜይል - anteneh.hailebirhan@press.et

ስልክ ቁጥር - 011-1-26-42-40

**የአዲስ ዘመን ማኔጂንግ ኤዲተር**

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ስልክ፡- 011 126 4240

Email:- wendweson.shimelis@press.et

wendwesonshimelis@gmail.com

**የአዲስ ዘመን ምክትል ዋና አዘጋጆች**

- ወርቁ ማሩ
- ኃይሉ ሣህለድንግል
- አልማዝ አያሌው
- እስማኤል አረቦ

**የገበያ ልማትና ፕሮሞሽን ዘርፍ**

ኢሜይል - etpresspromotion@gmail.com

ስልክ - 011-126-43-41

ፋክስ - 011-811-13-15

**የማስታወቂያ መቀበያ ክፍል**

ስልክ ቁጥር - 011-156-98-73

ፋክስ - 011-126-58-12

**የማስታወቂያ ሽያጭ ማስተባበሪያ**

ስልክ - 011-1-26-43-39

**ማከፋፈያ**

ስልክ ቁጥር - 011-157-02-70


ነፃ ሃሳብ

ይህ አምድ በተለያዩ ፖለቲካዊ ኢኮኖሚያዊና ማህበራዊ ጉዳዮች ዙሪያ ዜጎች ነፃ ሀሳባቸውን የሚሰጡበት ነው፡፡ በዓምዱ ላይ የሚወጡ ጽሁፎች የዝግጅት ክፍሉን አቋም አያመለክቱም፡፡

## የሰላም ትሩፋቱ ያልተዋጠላቸው …

**ሰላማዊት ውቤ**

በመንግስትና በሕወሓት መካከል በደቡብ አፍሪካ ፕሪቶሪያ የተደረሰበት የሰላም ስምምነት ዜና ከተሰማ ማግስት ጀምሮ አገርና ህዝብ በአዲስ ተስፋና የታሪክ መንገድ ላይ ናቸው። ስምምነቱም የፈጠረው ደስታ በቀላሉ የሚታይ አይደለም ። ጥቅማችንን ያሳጣናል ብለው ከሚያስቡ ጥቂቶች በስተቀር ሁሉንም ኢትዮጵያዊ የገዛ ነው።

እሰየው! አሁን ላይ ያለፉትን ሁለት ዓመታት ችግሮቻችንን መቀልበስ በሚያስችል መግባባት ላይ ደርሰናል። ይሕ በአንድ አገርና በአንድ መንግስት ሥር ለሚተዳደሩ ወንድማማች ሕዝቦች እጅግ አስፈላጊ ነው። ለቀጣይ እጣ ፈንታቸውም ወሳኝ አቅም ነው ።

የችግሩ ግንባር ቀደም ገፈት ቀማሽ ከመሆን ባለፈ የከፈለውም አላስፈላጊ ዋጋ ለግምት የሚከብድ በመሆኑ፤ የሰላም ስምምነቱ ብዙ ቱሩፋቶች ይዞ ስለመምጣቱ ለህዝባችን ማብሰር የሚያስፈልገው አይደለም ።

ዛሬ ላይ ኑሮውን በማያባራ ግጭትና ሁከት ውስጥ አድርጎ በጭንቀት ይመራ የነበረው የትግራይ ሕዝብ ሰላም በመውረዱ ከጭንቀት ወጥቷል። ተረጋግቶ ወደ መኖርም እያመራ ነው። ስምምነቱን ተከትሎም መንግሥት ወደ ትግራይ ክልል ሰብዓዊና ቁሳዊ ድጋፍን በስፋት ተደራሽ ሲያደርግ እያስተዋልንም እንገኛለን።

ተደራሽ እያደረጋቸው የሚገኙ የምግብና የጤና ቁሳቁሶች እለት እለት እየጨመሩ ነው። ይህ ደግሞ የእለት ምግብ አቅርቦት ችግር ውስጥ ለነበረው ለትግራይ ወንድሞቻችን ምን ማለት እንደሆነ መናገር የሚችሉት እነሱ ናቸው።

ከዚህም ባለፈ በጦርነቱ ተቋርጠው የነበሩ አገልግሎቶችን ማስጀመር፤ ፈራርሰውና ከጥቅም ውጪ ሆነው የነበሩ የአገልግሎት ተቋማትን መገንባትና መጠገን ቀጥሏል። ሩቅ ሳንሄድ የጦር አውድ በነበረችው አላማጣ ከተማ ያለውን ብናይ በጦርነት ውስጥ ማስቀጠል ያልተቻሉ አገልግሎት የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ ማስቀጠል እየተቻለ ነው።

በከተማዋ ተዘግተው የነበሩ የንግድ ተቋማት ተከፍተዋል ለሕብረተሰቡ አገልግሎት እየሰጡ ነው። ሌሎች በርካታ ማህበራዊ አገልግሎቶችም ወደ ሥራ እየገቡ ነው። የጤናና የትራንስፖርት አገልግሎቶች ሕብረተሰቡን ወደ ማገልገሉ ተመልሰዋል።

የከተማዋ ነዋሪዎች በሚያስተማምን ሁኔታ የንፁሕ መጠጥ ውሃ አገልግሎት እያገኙ ነው። እንደውም የሁለት ጂ እና የሶስት ጂ የኢንተርኔት አገልግሎትም ተጀምሯል። የኢንተርኔት አገልግሎቱን ፈጣን ለማድረግ በጦርነት የተበጣጠሱ ፋይበሮችን የመጠገኑ ሂደት እየተፋጠነ ነው።

የሰላም ስምምነቱን ተከትሎ የኢትዮጵያ አየር መንገድም ወደ ትግራይ ክልል አቋርጦት የነበረውን በረራ ዳግም ለመጀመር ሰፊ ዝግጅት እያደረገ መሆኑም እየተሰማ ነው። በዚህም ለህዝቡ የሰብዓዊ አቅርቦት ድጋፎችን በስፋት ለማድረስ ታስቦ እየተሰራ ነው።

የአየር መንገዱ የስራ ኃላፊ ሰሞኑን ሲናገሩ እንደተደመጠው፤ በክልሉ ከሚገኙ ኤርፖርቶች መካከል የመቀሌ እና የሽሬ አየር ማረፊያ ተቋርጦ የነበረውን በረራ ዳግም ለማስቀጠል ምቹ በሆኑበት ደረጃ ላይ ይገኛሉ። በአንፃሩ የአክሱም አየር ማረፊያ በግጭቱ የደረሰበት ጉዳት መጠነ ሰፊ በመሆኑ ለበረራ በሚመች መልኩ የማስተካከሉን ሥራም የመሥራቱ ጉዳይ ታሳቢ መሆኑን ጠቁመዋል።

በሰላም ስምምነቱ ትግበራ አኳያ በመንግሥት በኩል በየትኞቹም መገናኛ ብዙሃን ግጭት ቀስቃሽ መልዕክቶች እንዳይተላለፉ ከማድረግ ጀምሮ እንዲህ የሚያበረታቱ የትግበራ ጥረቶች የመኖራቸውን ያህል በሕወሓት በኩል ያለውም እጅግ የሚደነቅና የሚበረታታ እንደሆነ ማየት የሚያስችሉ ብዙ አመርቂ እንቅስቃሴዎች ይታያሉ። በሕወሓትም በኩል የሚታየው አበረታች ነው።

ይህም ሆኖ ግን አንዳንድ ወገኖች ምን አልባትም ከውጭም/ከአገር ውስጥም ያሉ ግለሰቦች ይሄ የሁለቱ ወገኖች ስምምነት የወለደው የሰላም ቱሩፋት የተዋጠላቸው አይመስሉም። እነዚህ ጥቂት ወገኖች ወይም ግለሰቦች ከግጭት አንዳች የሚያተርፉት ነገር ያላቸው ሊሆኑ እንደሚችሉ አያጠራጥርም/የግጭት ነጋዴዎች /።

"አውቆ የተኛ ቢቀሰቅሱት አይሰማም "እንዲሉ ለነዚህ ክፍሎች ስለ ሰላም ፋይዳ እየነገሩ ግንዛቤ ማስጨበጡ ድንጋይ ላይ ውሃ የማፍሰስ ያህል ከንቱ ነው። ዕውቁ ኒውሮሳይንቲስት፣ ሳይኮሎጂስትና ሳይኪያትሪስት የአንጎል ሳይንቲስት ፕሮፌሰር ድሪው ዌስተን እንደሚለው፤ እንዲህ ዓይነት ግለሰቦች ወይም ክፍሎች አእምሯቸው የስምምነትና የሰላም ሀሳቡን እንዳይቀበል አደንዝዘውታል።

የሚታያቸው ግጭቱ፤ ተከትሎት የሚከሰተው ብጥብጥና ሁከት እነሱ ከዚህ ሊያተርፉ የሚችሉት ጥቅም ብቻ ነው። ‹‹You can't teach an old dog a new trick›› ወይም በአማርኛው ሲተረጎም "ያረጀን ውሻ አዲስ ሙድ" አታስተምረውም እንዲሉት ዓይነቱ የቆየ አባባል ካረጁ ካፈጁ ወዲህ ጭንቅላታቸው አዲስ ዓይነት ልምምድን በፍፁም በጄ ብሎ አይቀበልም።

በዓመታት ተመሣሣይ የአስተሳሰብ መንገድና ያንን መንገድ መቀየር እንደሌለበት በተግባር ተሞክሮ እንደተረዳ የሚያምንን እንደ ጉቶ የደነደነን የጎልማሳ ወይ የአዛውንት ሰው አዕምሮ፣ ከሚያውቀው የተቃረነ ወይም አዲስ ነገርን ላስተምርህ ብንለው ቢፈልግም ጭንቅላቱ በጄ አይለውምና መከራው ብዙ ነው።

ውሻውን በቡችልነቱ አግኝተን የፊት እግሩን አንስቶ እጃችንን እንዲጨብጥ፤ በኳስ እንዲጫወት፤ ሽኮኮ እያደነ እንዲደሰት፤ የሰርከስ ትርዒት አክሮባቲስት እንዲሆን፣ ወይ ቀላል የመደመርና የመቀነስ ስሌቶችን እንዲሰራልን፤ አልያም የተቀበረ ፈንጅ እንዲያነፈንፍ አስተምረነው ቢሆን ኖሮ ለመቀበል የሚያዳግተው እንደማይኖር ሁሉ የነዚህ የሰላም ስምምነቱ ያልተዋጠላቸው ሰዎች ነገርም እንዲሁ እንደ ቡችላው መሆን ነበረበትና አይገርምም።

ፕሮፌሰር ድሪው ዌስተን፤ እኛ ሰዎች ፖለቲካ-ነክ መረጃዎችን እና የህግ-ነክ መረጃዎችን እንዲሁም ከቆየ አስተሳሰባችን ወጣ ያሉ አዲስ አስተሳሰቦችን የምንቀበልበትንና ‹‹ፕሮሰስ›› የምናደርግበትን (የምናሰላስልበትን ወይም የምናብላላበትን) መንገድ ያጠናበትን መጥቀስ አስፈላጊ ይመስለኛል።

ፕሮፌሰሩ ከ20 ዓመት በላይ በተለያዩ ሰዎች አንጎል ላይ ተመራምሮ እንዳገኘው ግኝት የፈለገውን ያህል ፊደል የቆጠሩ የፖለቲካ ደጋፊዎች - የሚደግፉትን የፖለቲካ ፓርቲ - ወይም የሚከተሉትን ፖለቲከኛ ግድፈቶች - ወይም ግልጽ ያሉ የተቃረኑ አቋሞች - የሚያየውን የአንጎላቸውን ክፍል አደንዝዘውታል። ምንም እንከኖችን እንዳያይ፣ እንዳይሰማ፣ አዳፍነውታል።

በዚህ ምክንያት የሰላም ስምምነቱ ሀሳብ ሳይዋጥላቸው ቢቀር አይጭነቀን። ሆኖም አንጎላቸውን የመለወጥ ጥረታችንን ሳናቋርጥ ስምምነቱን አእምሯችን የተቀበለልን ሁሉ ለሰላም ለስምምነቱ ትግበራ በየፊናችን እንትጋ!።


Website - www.press.et Email - addiszemen@press.etFacebook - Ethiopian Press Agency

የዝግጅት ክፍል ፋክስ - 251-011-1-56-98-62

ማህበራዊ

# እንዲህም ይኖራል

ሕይወት ፈርጀ ብዙ ገጽታዎች አሏት፤ መውጣት እንዳለ ሁሉ መውረድም ይኖራል። ከመውረድ ውስጥም በትጋት መውጣት ይቻላል። አግኝቶ ማጣት እንዳለ ሁሉ አጥቶም ይገኛል። ይህ የሕይወት እውነታ ነው፤ በጥቂቶች የህይወት መውጣትና መውረዶች ውስጥ ብዙዎች ይማራሉ። የህይወትን ፈተናዎችም ያውቃሉ። በከፍታ ውስጥ የሚገኙት ‹‹እንዲህም ይኖራል እንዴ?›› ብለው ራሳቸውን ይጠይቃሉ። ስተቸገሩት ያዝናሉ፤ ካላቸው ቀንሰው የሌሎችን ችግር ይካፈላሉ፤ በተጨማሪም ችግር ብልሃትን ያስተምራል እንዲሉ ከችግር ጋር ተላምዶ ከመኖር ይልቅ ለመፍትሄ የሚታትሩትንም ያበረታታሉ። በመሆኑም ‹‹እንዲህም ይኖራል›› ብለን በከፈትነው አምዳችን ህይወትን በየፈርጁ ታስተውሉበት፤ ˆእስተውላችሁም ትማሩበት ዘንድ ጋበዝናችሁ። ስአስተያየቶቻችሁ፤ ለመሰል ታሪኮች ጥቆማችሁ እንዲሁም ለድጋፋችሁ የዝግጅት ክፍላችን አድራሻ ትጠቀሙ ዘንድ ጋበዝናችሁ።

## ‹‹ልጄን ትፈጠር ብዬ ተውኳት››

### - እናት ጥሩ ማዕድ አስፋው

መልካምሥራ አፈወርቅ

ጥንዶቹ የመልካም ትዳር ተምሳሌት ናቸው። በመዋደድ፤ በመተሳሰብ፤ ያድራሉ። ቤት ይዘው ጎጆን ማሰብ ከጀመሩ ወዲህ የሁለቱም ባሕርይ በአንድ ሲጓዝ ኖሯል። ‹‹አንተ ትብስ ፣ አንቺ ›› ይሉት እውነት ገብቷቸዋል። አንዳቸው ለሌላቸው ጥላ ከለላ፤ አጋር መከታ መሆናቸውን ያያቸው ሁሉ ይመሰክራል።

ጥሩ ማዕድ አስፋው ትዳሯን ታከብራለች፤ ባሏን ትወዳለች። እሱ ስራ ውሎ እስኪገባ ዓይኗን አታምነውም። ደጅ ደጁን እያየች፤ መምጫውን ትናፍቃለች። ቤት ሲደርስ ከድካሙ እንዲያርፍ፤ የቀን ውሎውን እንዲረሳ ከቡናው፤ ከእራቱ እያለች ጎኑ ታመሻለች። የባሏ ስራ ጉልበት ፈታኝ አድካሚ ነው። ያጋጠመውን ትጠይቃለች፤ የዋለበትን ያወጋታል። ቤቱ በሳቅ ሁካታ ደምቆ ያመሻል።

ጥሩ ማዕድ ስለባለቤቷ በጎነት መስካሪ ነች። መልካምነቱን ስትገልጽም ቃላቶች ያጥሯታል። ሁሌም ከአድናቆት ጋር ምስጋናን መሸለም ልምዷ ነው። የባጃጅ ሹፌሩ አባወራ ስለሚስቱ ክብር አለው። ከልቡ ይወዳታል። ከመውደድ ባለፈ ደግሞ አጋርነቷን ያምናል። ጥሩ ማዕድ ሚስቱ ብቻ አይደለችም። የችግሩ መፍትሄና መላ ነች። የሕይወቱ ቅመም ጭምር።

ባልና ሚስቱ ትዳር ይዘው ጎጆ ማቅናት ከጀመሩ ዓመታት ተቆጥረዋል። በእነዚህ ጊዜያት ክፉ ደጉ የጋራቸው ሆኖ አልፏል። ኑሮ ቢከብዳቸውም ለራሳቸው አያንሱም። የመጀመሪያ ልጃቸውን በስስት እያዩ በፍቅር ያሳድጓታል። ሁሌም ስለእሷ ነገና ስለእነሱ የወደፊት ሕይወት ያስባሉ። መተሳሰባቸው ሕይወት፤ ኑሯቸውን አቅንቷል። ሰላማቸውን ጠብቋል።

#### አዲስ እንግዳ

አሁን ጥሩ ማዕድ ሁለተኛ ልጇን ነፍሰጡር ናት። ድንገት ባወቀችው እርግዝና አልተከፋችም። የራሴ ትለው መኖሪያ ቤት ባይኖራትም የተሰጣትን ልትቀበል ተዘጋጅታለች። ባተሌው ባሏ የቤተሰቡ ኑሮ ያሳስበዋል። ተቀጥሮ በሚሰራበት ውሎ ያገኘውን ይዞ ቤቱን ይሞላል። አሁን የልጅ ቁጥር በአንድ ሊጨምር ነው። ይህን ሲያስብ ስለ ሕይወት ይጨነቃል ፣ ባለቤቱንና ራሱን እየደመረ ስለነገው ያቅዳል። ዘወትር እረፍት የለሽ ነው። ማልዶ ይሮጣል፤ መሽቶ ይገባል። ጠዋት ወጥቶ ማታ ሲመለስ ድካም ልፋቱን በሚስቱ፤ በልጁ ፈገግታ ይረሳል።

ጥሩ ማዕድ ጊዜዋን ለልጇና ለባሏ ታውላለች። በአባወራዋ ትከሻ የሚያድረው ቤት ብዙ ያሻዋል። እሷ ጎዶሎን ለመሙላት የአንድ ሰው እጅ ብቻ እንደማይበቃ ታውቃለች። የባጃጅ ስራ ተባረው፤ ተናጥቀው የሚያድሩበት ነው። ለአሰሪው በእለት የሚጠበቀውን ማስገባት ግድ ይላል። እንዲህ ሲሆን እንደሱ ተቀጥሮ ለሚሰራ ይከብዳል። ያም ሆኖ በእነሱ ቤት ችግር አልገባም። ያላቸውን እያብቃቁ ፣ የእጃቸውን አመስግነው ያድራሉ።

ጥሩ ማዕድ እርግዝናዋ እየገፋ ነው። እንደቀድሞው ተሯሩጣ ባታድርም ለቤት ጎጆዋ አላነሰችም። አባወራዋን ለስራ ሽኝታ የሚጠብቃትን ትከውናለች። ልጇም ብትሆን በእሷው ሀላፊነት ትውላለች። የሚያሻትን፤ እየሞላች፤ የጠየቀችውን እየሰጠች የልቧን ትሞላለች። ወይዘሮዋ በየወሩ የእርግዝና ክትትል አላት። ከጤና ባለሙያዎች ምክር እየወሰደች፤ የተባለችውን ትሰማለች። ባለሙያዎቹ ዘወትር ማለዳ ብዙሃንን ከማስተማር አይቦዝኑም።

ነፍሰጡር ሴት በእርግዝና ጊዜዋ ማድረግ ስላለባት ጥንቃቄ፤ ስለአመጋገብ ፣ ጤንነቷ፤ ስለአኗኗሯ ደኅንነቷ ቁምነገር ያስጨብጣሉ፤ ያስተምራሉ። ጥያቄ እየጠየቁ ምላሽ ይሰጣሉ። ምላሽ እየሰጡ፤ በምሳሌ ያስረዳሉ። ጥሩ ማዕድ ከሌሎች ጎን ሆና ሁሉን ትሰማለች። ቤት ስትደርስ የሰማችው ይረሳታል፤ ስለምግቧ አስባ፤ ተጨንቃ አታውቅም። ቤት ካፈራው ያማራትን ትጋራለች።

#### ዘጠነኛው ወር

ወይዘሮዋ መከረሚያዋን ጉድ ጉድ እያለች ነው። የመውለጃ ወሯ ገብቷል። ለአራስ ቤቷ የሚበጃትን እያሟላች ፣ ቤቷን ታሳምራለች፤ ጓዳዋን ታዘጋጃለች። ለ‹‹እንኳን ማርያም ማረችሽ ጥየቃ ለሚመጡ እንግዶቿ የአቅሟን ማድረግ አለባት፤ ካላት ቆጥባ ያስቀመጠችውን ለመስተንግዶው ታውላለች። ወልዳ ስትገባ ጠያቂ ወዳጅ ዘመድ አይጠፋም። ይህን እያሰበች በሀሳብ ትርቃለች። ከራቀችበት ስትመለስ የጎደለውን ትሞላለች፤ ያሰበችውን ታደርጋለች።

አንድ ማለዳ ጥሩ ማዕድ የተለየ ህመም ተሰማት። ያዝ ለቀቅ የሚያደርጋት ስሜት ምጥ መሆኑ አልጠፋትም። ሰሞኑን ከሀኪም ቤት ስትመላለስ በቅርብ እንደምትወልድ ተነግሯታል። በሚሆነው አልደነገጠችም። ይህን እውነት በመጀመሪያ ልጇ ታውቀዋለች። ጥርሷን ነክሳ ለሚሆነው ሁሉ ተዘጋጀች።

ብቻዋን አይደለችም። ከጎኗ ባለቤቷና የቅርብ ሰዎች አሉ። ከሀኪም ቤት ስትደርስ ወደ አንድ ክፍል ገብታ ምርመራ ተደረገላት። ሀኪሙ በእጁ ያለውን የህክምና ካርድ ደጋግሞ ያነባል። አንዳንድ ጉዳዮችን እየጠየቃት ነው። ስሜቱ ምጥ መሆኑ እንዳረጋገጠ ወደ ማዋለጃ ክፍል እንድትሄድ አዘጋጃት።

#### በማዋለጃው ክፍል

አሁን ጥሩ ማዕድ የሆስፒታሉ ልብስ ተሰጥቷት ወደ ማዋለጃው እያለፈች ነው። የጀመራት ህመም በርትቷል። ስሜቱን ልትቋቋም ጥርሷን ትነክሳለች። ለአፍታ አስጨንቆ ለቀቅ ሲደርጋት ‹‹እፎይ›› ትላለች። ይህ እረፍት እንደማይቀጥል ታውቀዋለች። ቀጣዩ ጭንቀት ፈታኝ እንደሚሆን እያሰበች ራሷን ታበረታለች።

ጥሩ ማዕድ ከማወለጃው ገብታ እንደቆየች ጥቂት ሀኪሞች ወደእሷ ቀርበው ከበቧት። በፊታቸው የሚነበበው ጭንቀት ሌላውን ያስጨንቃል፤ በክፍሉ የገባችውን ወላድ ለማነጋገር ቸኩለዋል። ጥሩ ማዕድ የእነሱን ገጽታ ያስተዋለች አይመስልም። ገፍቶ የመጣውን ምጥ ለማሸነፍ ከራሷ ትግል ገጥማለች።

ሀኪሞቹ ከአጠገቧ ደርሰው አንድ ጉዳይ አነሱባት። ጉዳዩ ለጥሩ ማዕድ አዲስ ባይሆንም ክፉኛ ደነገጠች፤ ልቧ ያለማቋረጥ ደጋግሞ ሲመታ ተሰማት። ይህ ለእሷ የሞትና ሕይወት ትግል ነው። ዕንባዋ በጉንጮቿ እየፈሰሰ በዓይኖቿ ተማጸነች። እየተሰማት ያለው ህመም ከምጡ አይሎባታል። መተንፈስ እየተሳናት ነው። ሁኔታዋን ያዩት ሀኪሞች ፈጥነው ከእጇ መለኪያ አደረጉ። ደሟ ቀድሞ ከነበረው በእጥፍ ጨምሯል። ዓይኖቿን ጨፈነች፤ ገለጠች። ከቀናት በፊት ስለሰማችው እውነት ደጋግማ አብሰለሰለች። ጥልቅ ሀሳቧ ወደኋላ አጠንጥኖ መለሳት።

#### ከቀናት በፊት

ጥሩ ማዕድ ዘጠነኛ ወሯ እንደገባ የመጨረሻውን አልትራሳውንድ ተነሳች ። በወቅቱ ውጤቱ ከእጃቸው የደረሰ ሀኪሞች ወይዘሮዋን ሊያነጋግሯት እንደሚሹ አሳወቋት። እንደተባለችው ከሀኪም ፊት ቀርባ የምትባለውን ጠበቀች። ሀኪሙ በእርጋታ፤ በጥንቃቄ እያስረዳ የሆነውንና ማድረግ የሚገባትን አሳወቃት። የምርመራው ውጤት በተረገዘው ልጅ ወገብና ጭንቅላት ላይ ውሃ ስለመኖሩ ያመለክታል።

ይህ ችግር በእርግዝና ወቅት በነርቭ ዘንግ ላይ የሚያጋጥም ክፍተት ነው። የህክምና አጠራሩም ‹‹ ስፓይና ቢፊዳ ኤንድ ሀይድሮ ሴፋለስ ›› ይባላል። የህብለ ሰርሰር በአግባቡ ያለማደግና በጭንቅላት ውስጥ ከመጠን ያለፈ ፈሳሽ መኖር በቅድመ ወሊድ ጊዜ ሊያጋጥም የሚችል የጤና ችግር ነው። የነርቭ ዘንግ ክፍተት ከመጀመሪያዎች የእርግዝና ሳምንታት አንስቶ የሚከሰት ቢሆንም ችግሩ የሚታወቀው ግን በመጨረሻዎቹ የመውለጃ ሳምንታት ላይ ነው። የዚህ ችግር መነሻ በእርግዝና ወቅት የፎሊክ አሲድን በአግባቡ አለመጠቀም መሆኑ ይታወቃል።

ወይዘሮዋ እንደ እናት ልጇን ወልዳ መሳምን ናፍቃለች። ሀኪሞቹ ግን ይህ ከመሆኑ በፊት በልጇ መኖር አለመኖር ላይ ፈጥና እንድትወስን እየጠበቋት ነው። እያለቀሰች ምክንያቱን ጠየቀች። ሀኪሞቹ በአግባቡ ሊያስረዷት ጊዜ ወሰዱ። ልጁ ከነችግሩ ከተወለደ የመኖር ህልውናው ያሰጋል ተባለች።

እንዲህ አይነት ልጆች፤ በየጊዜው ጭንቅላታቸው



ያድጋል፤ ለመንቀሳቀስ፤ ራሳቸውን አውቀው ለመጸዳዳትና በወጉ ለመኖር ይሳናቸዋል። የወገብ ላይ ክፍተቱም ፓራላይዝድ የመሆን ዕድላቸውን የሚያሰፋ ነው። በዓይን በአዕምሮና በጤናቸው ላይ የሚኖረው ጉዳት የከፋ መሆን ያለ ሌሎች እገዛ ሕይወታቸውን እንዳይቀጥሉ ያስገድዳል። ይህ አይነቱ ችግር ከወሊድ በፊት በታወቀ ጊዜ በህክምና ጽንሱ እንዲወገድ ይወሰናል።

#### ውሳኔ

አሁን ጥሩ ማዕድ እውነታውን አውቃለች። ዘጠኝ ወር ሙሉ ያረገዘችው ልጅ ጤናው የተጓደለ፤ የመኖር ህልውናው በእጅጉ የሚያሰጋ ሆኗል። ከእንግዲህ ከነችግሩ ልጇን መቀበልና ሀኪሞች እንዳሏት ፅንሱን ማስወገድ የግል ውሳኔዋ ይሆናል። ወይዘሮዋ ከራሷ ተጨቃጨቀች፤ በሀሳብ ሽቅብ ቁልቁል ወረደች፤ በጭንቀት ተወጥራ ክፉ ከደግ አሰበች።

እሷ ልጇን ፈጽሞ ማጣት፤ አትሻም። እንደተባለችው ብትፈጽም ሀጢያት መሆኑ አሳሰባት። ‹‹እሺ፣ እምቢ›› ሳትል ከራሷ ሞገተች፤ እነሱ እንደሚሏት ማድረግ፤ መፈጸም አልሆነላትም። የተረገዘችው ሴት መሆኗን አውቃለች። ልጇ ምንም ብትሆን የፈጣሪዋ ስጦታ ናት። ደግማ ደጋግማ አሰበች። በቃ! ልጇን ከነህመም፤ ከነችግሯ ትቀበላታለች። ወሰነች። ለሀኪሞቹ ‹‹ልጄን ተውልኝ ትፈጠር›› ስትል አሳወቀች። ቃሏን ተቀበሉ፤ ውሳኔዋን አከበሩ።

#### ስጦታ

እነሆ ትንሽዬዋ ህጻን ከእናቷ አቅፍ ገብታለች። ጥሩ ማዕድ ያመነችበትን፤ ውስጧ የነገራትን ማድረጓ አላስቆጫትም ። የተሰጣትን ልትቀበል ፈቅዳለችና ለሚሆነው ሁሉ ራሷን አዘጋጀች። ልጇን መባ/ስጦታ /ብላ ስትሰይማት በምክንያት ነው። ስጦታዋን አልጣለቻትም ፈጽሞ አላፈረችባትም። ሕይወት ዘርታ እስትንፋሷን ከሰጠቻት ቀን ጀምሮ ፈተናዋ ፈተና ሊሆን ከጎኗ ሆናለች።

በመጀመሪያዎቹ ቀናት እናት ልጇን ታቅፋ ወደ ዘውዲቱ ሆስፒታል አቀናች። ለሰባት ወራትም አልጋ ይዛ በህክምናው ቆየች። የህጻን መባ ጸጋዬ ጤንነት አስቀድሞ እንደተባለው ሆነ። አዲሷ ጨቅላ ቀዶ ህክምና ተደረገላት። ጥቂት ቆይቶ ግን አካሏ ኢንፌክሽን ፈጠረ። የህጻኗ ለስላሳና ስስ ሰውነት በቁስል ስቃይ ተፈተነ።

ህክምናው በተጀመረ አራት ወራት ውስጥ የጭንቅላቷ ውሃ መጨመሩ ተነገራት። ጭንቅላቷ ለሁለት ጊዚያት ቀዶ ህክምና ተደርጎለት ‹‹ሻንት›› የተባለ መሳሪያ እንዲገባላት ሆነ። እናት ከሆስፒታል ሳትለይ ስለልጇ ሕይወት ታገለች። አንዳንዴ የወገብ ላይ ቁስሏ አንስታ ለማቀፍ ያስቸግራታል፤ እንዳሻት ለማጥባትና እንደልጅ ለማገላበጥ ህመሙ ፈታኝ ነበር። ይህ ባጋጠማት ቁጥር ጥሩ ማዕድ በትካዜ ትቆዝማለች፤ የልጇ ህመምና ስቃይ ውስጧ ዘልቆ ይሰማታል።

#### በጎ ምክር

አንድ ቀን ወይዘሮዋ የአንዲት ልበ ደግን ነርስ ምክር ከልቧ አዳመጠች። ቃሏ ለማንነቷ ትርጉም ሰጠው። ነርሷ ጠንካራና ጎበዝ እናት ከሆነች የልጇን ጤና መጠበቅ እንደሚቻላት ነገረቻት። ምክሯ ውስጧን አረሰረሰው። ያለቻትን ልትሆን፤ በጽናት ልትቆም ራሷን አሳመነች፤

ህጻን መባ አሁን አንድ ዓመት ከአምስት ወር ሆኗታል። የጭንቅላቷ ዕድገት ባለበት ቢገታም ከወገቧ በታች አትንቀሳቀስም። እንደ ዕድሜ እኩዮቿ መዳህ፤ መንፏቀቅ አትችልም፤ ዕቃ ይዛ ልትቆም አትሞክርም። በየጊዜው የህክምና ክትትል አይለያትም።

እናት ጥሩ ማዕድ ሙሉ ጊዜዋን ለልጇ ሰጥታለች። ስራ በመስራት ባሏን ለማገዝ፤ ጓዳዋን ለመሙላት አልተቻላትም። ልዩ ትኩረት የምትሻው መባ ከትከሻዋ ሳትወርድ ትውላለች። ድንገቴ ጉዳይ ቢገጥማት፤ ለጎረቤት፤ ወዳጅ ዘመድ ‹‹አደራ›› ብላት አትወጣም። የእሷ ሕይወት ‹‹እሷና እሷ›› ብቻ ነች።

አንዳንዴ በተስፋ መቁረጥ ውስጧ ይፈተናል፤ ይከፋታል፤ ታለቅሳለች። ይህኔ ልበ በጎው ባለቤቷ ከጎኗ ሆኖ ‹‹አይዞሽ፣ አለሁሽ ›› ይላታል። የህጻኗ መልካም ባህርይ ደግሞ ሁሉን ያስረሳታል። አንዳንዴ የቤቷን ስራ ለመከወን መባን ከትከሻዋ አውርዳ ታስተኛታለች። ጉዳይዋ በበዛ ጊዜም ከአልጋ ማስተኛቱ ይደጋገማል። እንዲህ ሲሆን የህጻኗ ጀርባ ይላጣል፤ ቁስል ያላጣው አካሏ ሰበብ ፈልጎ ይቆጣል።

እናት ጥሩ በእርግዝናዋ ጊዜ ከሀኪም የተሰጣትን ምክር አትረሳም። የፎሊክ አሲድን የምግብ ይዘት በአግባቡ እንድትጠቅም ተነግሯት ነበር። በወቅቱ ይህን አለማድረጓ ለችግር እንደዳረጋት ታምናለች። ያም ሆኖ ልጇ እንድትወለድ በመፈቀዷ አትቆጭም።

ስለነገዋ መባ ታላቅ ተስፋን ባትሰንቅም የተቻላትን ለማድረግ አትቦዝንም።፤ ልጇ ለእሷ ሕይወቷ ነች። ወደዚህች ምድር እንድትመጣ፤ እንድትኖር እስትንፋስ ሆናለች። ቀኝ እጅ የሆናት ባለቤቷ ቤት ጓዳቸውን ለመሙላት ከቀድሞው በባሰ ይሮጣል፤ ይተጋል።

በቤት ኪራይ ኑሮን መግፋት፤ ሕይወትን መምራት ፈታኝ ነው። አንዳንዴም የአንዳንድ ሰዎች በጎነት የጎደለው እይታ ችግሩን ከተሸከመው በላይ ጫና የሚፈጥር ይሆናል። ወይዘሮዋ በአንድ ወቅት የቤት አከራይዋ የልጇን ህመም በማሳበብ ክፉ ብላታለች። ከቤት አስወጥታለች። በርካቶች እንደሷ ባለመሆናቸው ግን ቅስሟ አልተሰበረም። ሁሉን ለፈጣሪዋ ትታ በብርታቷ ቀጥላለች።

አሁን የምትኖርበት ቤት ክፍያው ቢበዛም ሰዎቹ መልካም ናቸው። ችግሯን ይረዳሉ። እናት ጥሩ ቁጭ ማለቱን አትወድም። የሚያግዝ፤ የሚደግፋት ቢኖር ለልጆቿ ሰርታ መግባትን ትሻለች። ባለችበት አካባቢ በሴፍቴኔት ተጠቃሚ ለመሆን ያደረገችው ጥረት አልተሳካም። ዛሬም የቤተሰቡ ብቸኛ አማራጭ የአባወራው ትከሻ ነው። ነገ ህጻን መባ ከዛሬ የተሻለ ያስፈልጋታል። በአንድ ሰው አቅም ብቻ የቆመው ቤተሰብ በቤት ኪራይና በኑሮ ውድነት እየተፈተነ ነው።

#### ምክር

ወይዘሮዋ የሀኪሞች ምክር የገባት ቆይቶ ነው። በእርግዝናዋ ጊዜ ትኩረት ያልሰጠችው ጉዳይ ዋጋ አስከፍሏታል። ዛሬ ወዳና ፈቅዳ ወደዚህች ምድር ላመጣች ልጅ ታላቅ ሀላፊነት ተሸክማለች። ሌሎች እናቶች ግን በእሷ መንገድ አልፈው፣ ተመሳሳይ ዋጋ እንዳይከፍሉ አበክራ ትመክራለች። ‹‹ለእርግዝናችሁ ትኩረት ስጡ፤ የምትባሉትን ፈጽሙ›› ስትል።

# ስፖርት





# የዓለም ቻምፒዮኑ የቫሌንሲያ ማራቶንን ክብረወሰን ለማሻሻል ይሮጣል

ቦጋለ አበበ

ከወራት በፊት በኦሪገን በተካሄደው የዓለም አትሌቲክስ ቻምፒዮና የማራቶን ባለ ድል የሆነው ኢትዮጵያዊ አትሌት ታምራት ቶላ ነገ በስፔን ቫሌንሲያ ማራቶን ይወዳደራል።

ታላላቅ የዓለማችን የማራቶን አትሌቶች በሚፎካከሩበት የቫሌንሲያ ማራቶን የዓለም የርቀቱ ቻምፒዮን ትልቅ የአሸናፊነት ግምት የተሰጠው ሲሆን የቦታውን ክብረወሰን ለማሻሻል እንደሚወዳደርም ታውቋል። ከዓለም ቻምፒዮና ድሉ በኋላ የመጀመሪያ የማራቶን ውድድሩን የሚያደርገው ታምራት በርቀቱ የዓለም አምስተኛው ፈጣን ሰዓት ባለቤት ሲሆን 2020 ላይ የተመዘገበውን 2:03:00 የሆነ የቫሌንሲያ ማራቶን ክብረወሰን ያሻሽላል ተብሎ ይጠበቃል።

ታምራት በርቀቱ የዓለምን አምስተኛ ፈጣን ሰዓት ያስመዘገበው የዓለም ቻምፒዮን ከመሆኑ ከአንድ አመት በፊት አምስተርዳም ማራቶን ላይ ሲሆን ሰዓቱም 2:03:39 ነበር። የዓለም ቻምፒዮን ከመሆኑ በፊት በመምና አገር አቋራጭ ውድድሮች አጭር ጊዜ ቆይታው ስኬታማ መሆን የቻለው ታምራት በኦሊምፒክና በዓለም ቻምፒዮና የብርና የነሐስ ሜዳሊያዎችን በማራቶን ማጥለቅ እንደቻለ ይታወሳል።

ነገ በቫሌንሲያ ማራቶን በሚያደርገው ፉክክርም ከአሸናፊነት በዘለለ የውድድሩን ክብረወሰን እንዲሁም የራሱን ፈጣን ሰዓት ለማሻሻል እንደሚሮጥ ተስፋ አድርጓል። "የለንደን ማራቶንን ለመወዳደር ካልቻልኩኝ በኋላ በቫሌንሲያ እንድሮጥ የቀረበልኝን ጥሪ በደስታ ነው የተቀበልኩት" በማለት ለመገናኛ ብዙሃን አስተያየቱን የሰጠው ታምራት ባለፈው ለንደን ማራቶን መወዳደር ያልቻለበትን ምክንያት እንዲህ ሲል ያስረዳል "ከዓለም ቻምፒዮናው ድል በኋላ ለ15 ቀን ማገገም ነበረብኝ፣ ይህ ማለት ደግሞ በ60 ቀናት ውስጥ በለንደን ማራቶን ለመወዳደር መዘጋጀት አለብኝ፣ ይህ ደግሞ ለንደን ላይ ጥሩ ውድድር ለማድረግ በቂ ነው ብዬ አላምንም"።

የቫሌንሲያ ማራቶን በርቀቱ ፈጣን ሰዓት የሚመዘገብበት እንደሚሆን ያለውን እምነት የገለጸው ታምራት በውድድሩ ላይ ነገሮች ጥሩ ከሆኑ የራሱን ፈጣን ሰዓትና የውድድሩን ክብረወሰን ለማሻሻል ጥረት እንደሚያደርግ አስረድቷል።

በዓለም አትሌቲክስ የወርቅ ደረጃ ከተሰጣቸው የጎዳና ላይ ሩጫዎች መካከል አንዱ በሆነው በዚህ የሩጫ ውድድር ላይ በወንዶች መካከል በሚደረገው ፉክክር ከታምራት በተጨማሪ ሌሎች የርቀቱ ከዋክብት ብርቱ ፉክክር ያደርጋሉ ተብሎ ይጠበቃል፡፡ ርቀቱን ከ2 ሰዓት ከ05 ደቂቃ በታች የሮጡ ሰባት ያህል አትሌቶች ተፎካካሪ እንደሚሆኑ በሚጠበቀው በዚህ ውድድር ፈጣን ሰዓት ያለው ሌላኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት ጌታነህ ሞላ ነው፡፡ በርቀቱ ያለው ፈጣን ሰዓት 2:03:34 ሲሆን በዚህ ዓመት በተካሄደው የቶኪዮ ማራቶንም ሶስተኛ ደረጃን በመያዝ ማጠናቀቁ ይታወቃል፡፡ 2:04:27 የሆነ ሰዓት ያለው ሌላኛው ኢትዮጵያዊ አትሌት ዳዊት ወልዴ ደግሞ ሶስተኛውን ፈጣን ሰዓት ይዞ በነገው ውድድር ተፎካካሪ ይሆናል፡፡

በተመሳሳይ በሴቶች መካከል በሚካሄደው ውድድርም ኢትዮጵያዊት የ10ሺ ሜትር የዓለም ቻምፒዮን በርቀቱ ለመጀመሪያ ጊዜ እንደምትወዳደር ቀደም ብሎ ተዘግቧል፡፡ በ5 ሺ እና 10ሺ ሜትር



የዓለም ቻምፒዮኑ አትሌት ታምራት ቶላ በቫሌንሲያ ማራቶን ፈጣን ሰዓት ያስመዘግባል ተብሎ ይጠበቃል፣

እንዲሁም በ15 ኪሎ ሜትር የዓለም ክብረወሰን ባለቤት የሆነችው ለተሰንበት ግደይ በስኬታማነት ከምትታወቅበት የመም ውድድር ወደ ማራቶን ፊቷን ያዞረችበት የመጀመሪያው ውድድር ሆኗል፡፡ ባለፈው ዓመት በዚሁ የቫሌንሲያ ግማሽ ማራቶን ሮጣ 1:02:52 በሆነ ሰዓት በማግባት የርቀቱን የዓለም ክብረወሰን በእጇ ያስገባችው ለተሰንበት፣ አሁን ደግሞ በረጅሙ ርቀት የማራቶን ውድድር ልታደርግ መዘጋጀቷን ግሎባል ስፖርት ኮሙዩኒኬሽን የተሰኘው የስልጠና ቡድኗ አስቀድሞ ማሳወቁ ይታወሳል፡፡ ይህንን ተከትሎም የአትሌቷ አሰልጣኝ ኃይሌ እያሱ ከለተሰንበት ጋር ከዓመታት በፊት በ5ሺ ሜትር እና 10ሺ ሜትር እስከ ማራቶን የዓለምን ክብረወሰን መስበር የሚል እቅድ እንደነበራቸው ገልጿል፡፡ በዚህ መሰረት አትሌቷ አሁን በደረሰችበት ማራቶን ብቃት አዲስ ነገር ልታስመለክት ትችላለች በሚል ትጠበቃለች፡፡


## ኦሮሚያ ክልል

የባለንብረቱ ስም አቶ ነስሩ አህመድ የሰሌዳ ቁጥር 1 - A01086 ኦሮ የሊብሬ ቁጥር 0295750 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት ሊብሬ ለአቶ ነስሩ አህመድ ጠፋብን ብለው በቀን 12/03/2015 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ ስለሆነም የባለቤትነት ደብተር /ሊብሬ/ ወድቆ ያገኘ ወይም በሌላ ምክንያት ይዤዋለሁ የሚል ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማስረጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን በተባለው ጊዜ ገደብ ውስጥ ካላቀረቡ ለአመልካቹ ተለዋጭ ሊብሬ የምንሰጥ መሆኑን እናስታውቃለን፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር የምስራቅ ሐረርጌ ዞን ትራንስፖርት ኤጀንሲ ጽ/ቤት**

የባለንብረቱ ስም ወ/ሮ ትደነቂያለሽ ሳራ የተሽከርካሪው ዓይነት የሕዝብ የሰሌዳ ቁጥር 3-09836 ኦሮ የነ የሻንሲ ቁጥር 38925 ሞተር ቁጥር 3545 ሲ የሆነ የመኪና ሰሌዳ ጠፋቶብኛል በማለት በ12/03/2015 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ሰሌዳውን ወድቆ፣ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**በኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት መስተዳድር የሰበታ ከተማ ትራንስፖርት ኤጀንሲ**

## ሲዳማ ክልል

የባለንብረቱ ስም ይልማ ሀይለ የሰሌዳ ቁጥር 1ደሀ-13281 የተሽከርካሪ ዓይነት ት/ሣ ሞዴል Blue-GS 4T የሻንሲ ቁጥር 12865 ሞተር ቁጥር 4282355 የሊብሬ ቁጥር 0086963 ከላይ የተጠቀሰው የተሽከርካሪ ባለንብረት የተሽከርካሪ ሰሌዳ ጠፋብኝ በለው በ28/02/2015 ዓ.ም. አመልክተዋል፡፡ በዚሁ መሠረት ሰሌዳውን ወድቆ፣ተሰርቆ ወይም በሌላ ተሽከርካሪ ላይ ተለጥፎ ያገኘ ይህ ማስታወቂያ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በ15 ቀን ውስጥ የፍ/ቤት ማሳገጃ ትዕዛዝ እንዲያቀርቡ እያስታወቅን ይህ ባይሆን ግን ለአመልካቹ ተለዋጭ ሰሌዳ የምንሰጥ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

**የሲዳማ ብሔራዊ ክልላዊ መንግሥት ትራንስፖርትና መንገድ ልማት ቢሮ**

## አዲስ አበባ አስተዳደር

በከሳሽ/አመልካች ወ/ሮ በለጡ በዛወርቅ በተከሳሽ አቶ አምደብርሃን ዱባለ መካከል ስላለው የፍ/ብሔር ክርክር ጉዳይ ተጠሪ/ተከሳሽ አቶ አምደብርሃን ዱባለ በፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት ክስ የተመሰረተባቸው መሆኑን አውቀው በ6/4/2015 ዓ.ም በ4፡00 ሰዓት ላይ በችሎት እንዲቀርቡ የማይቀርቡ ከሆነ ጉዳዩ በሌሉበት የሚታይ መሆኑን አውቀው እንዲቀርቡ የፌ/መ/ደ/ፍ/ቤት አዲስ ከተማ ምድብ 2ኛ ቤተሰብ ችሎት አዟል፡፡

**የፌዴራል የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት**

## Development Bank of Ethiopia
## Invitation for National Competitive Bid (NCB)
## Bid Ref. No. DBE/NCB/IT/003/2022/23

Development Bank of Ethiopia has invites interested bidders for the procurement of the Corporate Email System.

1. Interested bidders are required to submit together with their bid documents:
i. Renewed Trade license
ii. TIN Certificate
iii. Suppliers Registration Certificate from PPA
iv. VAT Registration
v. Tax Clearance Certificate
2. Interested bidders may purchase a complete set of bidding documents beginning from December 03, 2022 upon the non-refundable fee of Birr 200.00 (one hundred birr) to customer Accounts Transaction Services office, Tower II, Ground Floor & Collect the bid documents by softcopy through your Email or by flash disk from Procurement Team at Tower II, 5th floor.

| No | Type of Services | Bid Security | Type of Securing |
|---|---|---|---|
| | Corporate E-mail System | 10,000.00 (Ten Thousand birr) | Unconditional Bank Guaranty |

3. Bids shall be submitted in to the bid box prepared for this purpose on or before December 19, 2022 at 10:00 A.M at Development Bank of Ethiopia Head office Tower I, Ground Floor.
4. Bids shall be opened in the above mentioned address, on December 19, 2022 at 10:05 A.M. In the presence of bidders and/or their authorized person.
5. Interested bidders may obtain further information from DBE Head office, Property & Facility Management Directorate procurement Team, Tower II, 5th floor, Tel. 251 115 24 40 42; and +251115506020 Fax +251 115 53 79 82.
6. Bidders should present their Financial & Technical documents separately in sealed envelope.
7. The language of the tender shall be English.
8. DBE reserves the right to accept or reject any or all bids.

**Development Bank of Ethiopia**